# ያለአንዳች አድልዎ የተሳሳተውን እንገስጽ!

## ከግብዝነት በራቀ አክብሮት፥ ድፍረት፥ ትሕትና እና ፍቅር ተባብረን ከግላዊ ጥቅምና ወገናዊነትም ተላቀን፥ በእውነት ላይ ጸንተን በመቆም የተሳሳተውን እንገስጽ፡፡-


**ይበቃል ያረጋል**

**በካንሳስ ሲቲ ካንሳስ፥ የደብረ ሣሕል መድኃኔዓለም**
**የኢትዮጵያ ኦርቶዶከሰ ተዋሕዶ ቤ/ክር**
**ምእመን**


**ጥር ፳፩, ፪ሺ፪ ዓ.ም**

# ማውጫ


መግቢያ-------------------------------------------------------------3

የአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ጥንተ አብሶ (Original Sin)----------------------------------5
በኦርቶዶክሳዊያን አባቶቻችን ግንዛቤ

በመሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ በተጻፈ ጽሑፍ፥---------------------------------------------11
በጽሑፉ መግቢያ ላይ ስላሰፈሩት ስሕተት የተሰጠ ምላሽ

በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ይመራ የነበረው----------------------------------18
የኢ.ኦ.ተ. ቤ\ክር የሊቃውንት ጉባኤ የወሰነው ውሳኔ
ያስከተለው የሃይማኖት ቀውስ

በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ: በተለያዩ ወቅቶች---------------------------------23
የተጻፉት መጽሐፍቶች ስለ አዳም የውርስ ኃጢአት፥
(ጥንተ አብሶ) ምን ይላሉ?
- የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት
- ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ
- ምልጃ፥ እርቅና ሰላም
- ዜና ሕይወት ዘቅድስት ቅዱሳን እመ አምላክ

መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ ነገረ ሃይማኖትን በተመለከተ--------------------------------------40
የፈፀሙት ስሕተት

በጽሑፍ ለትውልድ እንዲተላለፍ የተቀመጠን እውነታ:---------------------------------45
እንደሌለ አድርጎ ለመካድ የተሞከረ ሙከራ

"መድሎተ አሚን" ምን ይላል??------------------------------------------------47

ማሳሰቢያ------------------------------------------------------------50

ማጠቃለያ------------------------------------------------------------51

# መግቢያ

ውድ አንባቢያን ሆይ!! ይህችን አጠር ያለች ጽሑፍ ለመጻፍ የተነሳሁበት ዋነኛ ምክንያት: በሰሜን አሜሪካ: በካንሳስ ከተማ በምትገኘው፥ በደብረ ብርሃን ኪዳነምሕረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተነሰቶ በነበረው የነገረ ሃይማኖት ውዝግብ ሳቢያ: በቅርብ ሰሞን: በተለያዩ የሕዝብ መወያያ ድህረ ገፆች ላይ: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርሰቲያን፥ እመቤታችን ቅድሰት ድንግል ማርያምን በተመለከተ: ከአዳም የተላለፈው የውርሰ ኃጢአት፥ ወይም በዘመኑ አጠራር (ጥንተ አብሶ) ነበረባት ወይንስ አልነበረባትም ትላለች: የሚለውን ጥያቄ አሰመልክቶ፥ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተሰነዘሩትን ጽሑፎች በመመልከቴ ነው።

ከዚህ በመነሳት፥ በዚህ ጽሑፍ ላይ፥ የጌታችን የመድኃኔታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት: እመቤታችን ዘለዓለማዊት ድንግል ቅድስትና ብፅዕት ናት:: ይልቁንም፥ በማሕጸኗ "ቃል ሥጋ" ከሆነበት ቅጽበት ጀምሮ: ቅድስተ ቅዱሳን ሆና ተቀደሰች:: ማደሪያውና መንበሩ ስለሆነች ከልጇ ከጌታችን በታች፥ ከኪሩቤል በላይ አድርገን እናከብራታለን:: ሆኖም ግን: መልአኩ ቅዱሰ ገብርኤል ባበሰራት ጊዜ "አዎ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" ብላ ፈቃዷን ለፈጣሪዋ ባስገዛችበት ወቅት፥ መንፈሰ ቅዱሰ ሥጋዋን አንጽቶ እግዚአብሔር ወልድን እስከጸነሰችበት ሰዓት ድረስ: የአዳም የውርሰ ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) ነበረባት" ብለው ቀሲስ አሰተርአየ ፅጌ የያዙትን ኦርቶዶክሳዊ እምነትና የጻፉትን ጽሑፍ ደግፌ እጽፋለሁ። በተቃራኒው ደግሞ፥ የሮማ ካቶሊክ እምነት የሆነውን በመደገፍ "እመቤታችን ዘለዓለማዊት ድንግል ቅድስትና ብፅዕት: በአምላክ ህሊና ታሰባ ትኖር የነበረች: በእናቷ ማህጸን መንፈሰ ቅዱስ የአዳም የውርስ ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) እንዳይተላለፍባት የጠበቃት ናት በማለት: የቀሲስ አስተርአየን እምነት በመቃወም፥ መኖርያቸው ብሪታንያ የሆኑት መሪጌታ ገ/ሥላሴ: በመስከረም ፲ እና በኅዳር ፮, ፪ሺ፪ ዓ.ም. ተችተው የጻፉትን ጽሑፎቸ በመቃወም ምላሽ እሰጣለሁ።

በተጨማሪም፥ ባለፉት ፳ አመታት ውስጥ: መላው ኦርቶዶክስ የማይቀበለው ይህ፥ (Immaculate Conception) በመባል የሚታወቀው የሮማ ካቶሊክ ቤ/ክር ብቸኛ እምነት: በአጭር ጊዜ ውስጥ: ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ሊያጥለቀልቃት የቻለው: በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ይመራ የነበረው የኢ.ኦ.ተ ቤ/ክር የሊቃውንት ጉባኤ የወሰነው የተሳሳተ ውሳኔ በከፈተው በር መሆኑንም ለማሳየት እሞክራለሁ። ይህ ብቻ ሳይሆን: በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጻፉ መጽሐፍቶች: ለዚሁ ስህተት መሰፋፋት ያበረከቱትን ከፍተኛ አሰተዋፆና፥ በይበልጥ ደግሞ: ክቡርነታቸው ቀደም ሲል ከጻፏቸው መጽሐፍቶችና ከነበራቸው እምነት ጋር የሚጋጩ ስለመሆናቸው: ሰፋ አድርጌ በዝርዝር አሳያለሁ።

አዎ ምን አልባት አንተ ለመሆኑ ማነህ እና ይህንን ለማጻፍ የተነሳህ? ብሎ የሚል ይኖራል። "ማን ያውራ የነበረ: ማን ያርዳ የቀበረ" እንዲሉ፥ ይህ፥

- ብዙ ሰዎችን በአለም ዙርያ ያነጋገረ፥
- አብሮ በአንድነት፥ በፍቅርና በትህትና አምላኩን ያመሰግን የነበረን ሕዝብና ቤተ ክርሰቲያንን የከፈለ፥
- የኦርቶዶክሳዊ ተዋሐዶ ሃይማኖት ተፋለሰ፥ ያላግባብ ካህን ታገደ በማለት: ጉዳዩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክር ቅዱሰ ሲኖዶስ እንዲታይ በአክብሮት ወደ ቅድሰት አገር ኢትዮጵያ ከአምስት አመት በፊት የፍርድ ያለኸ ይግባኝ ሰነድ ተልኮ፥ ፍርድ ሰጪ በማጣት እስከአሁን ድረስ መልስ ያላገኘ፥
- መልስ ሰጪ ከማጣጣት የተነሳ: ሃይማኖት ነውና፥(...ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን...) የሚለውን ጸሎተ ሃይማኖት መሰረት በማድረግ: ከአኀት አብያተ ክርሰቲያናት መካከል አንዷ ወደሆነቸው የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ/ክ የተጮኸው የፍርድ ያለህ ጩኸት መልሰ ያገኘበት፥

ይህ ዛሬ እንደ ፊኛ ተወጥሮ ለአንዴና ለመጨራሻ ጊዜ ለመፈንዳት የተቃረበ የሚመስል

ትልቅ የነገረ ሃይማኖት ጉዳይ የተነሳው: የዚህ ጽሁፍ ጸሐፊ በሆንኩት በእኔ በይበቃል ያረጋል እና በዲያቆን ሳሙኤል ዘርይሁን መካከል በተደረገ የግል ውይይት ላይ በመሆኑ ነው። ስለ ዝርዝር ጉዳዩ እስከአሁን ድረሰ ያላወቀ: ነገር ግን ለማወቅ ለሚፈልግ፥ በወቅቱ ቅዱስ ፓትርያርኩን አቡነ ጳውሎሰን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁኖ በስልክ አነጋግሬአቸው፥ ጉዳዩን ከነዝርዝሩ ጽፋቹህ ላኩ ብለው በአዘዙት መሰረት: በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. በሰሜን አሜሪካ በካንሳስ ሲቲ ካንሳስ በሚገኘው በደብረሣሕል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክር ምዕመናን ተዘጋጅቶ የተላከውን ሰነድ www.medhanialemeotcks.org በመመልከት ለመረዳት ይቻላል።

በመጨረሻም፥ ይህንን ከበድ ያለ የነገረ ሃይማኖት ጉዳይ፥ በይበልጥም ደግሞ ብፁዐን አባቶችን፥ በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ይመራ የነበረውን የሊቃውንት ጉባኤ የወሰነውንም ሆነ፥ በክቡርነታቸው የተጻፉትን መጽሐፍት አስመልክቶ ስጽፍ፥ በፍጹም ትህትናና ከልብ በመነጨ ከበሬታ ነው። ሆኖም ግን፥ እንደነሱ ክህነቱም፥ ማዕረጉም ሆነ እውቀቱም ባይኖረኝ፥ እኔም በዚህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደነሱ ተጠምቆ በሚሊዮን ከሚቆጠረው በውጭ ከተበተነውና ሀገር ቤትም ካለው አንዱ የተዋሕዶ ልጅ ነኝ:: ነገር ግን፥ ከኦርቶዶክሳዊያን ቤተሰቦች በመወለዴ፥ ከቤተ ክርስቲያን አካባቢ ባለመለየት እየቆረብኩ ከማደጌ በቀር: ይህ የነገረ ሃይማኖት ውዝግብ በመካከላችን እስከተከሰተበት ጊዜ ድረስ: ቤተ ክርስቲያኔ ስለምታስተምረው ስለተዋሕዶ እምነቴ: አሁን የተረዳሁትን ጥቂት እውቀትና እውነት ማወቅ ቀርቶ፥ መኖሩንም አላውቅም ነበር:: ይህ ግንዛቤ፥ የኔ ብቻ ሳይሆን: አብረን ያለነው የደብረ ሣሕል መድኃኔ ዓለም የኢ.ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን አባላትም ጭምር ነው። ለዚህም ተጠያቂው *"አስተርአየ ምን አለ ሳይሆን ቅዱሳት መጻሕፍት ምን አሉ በሉ"* እያሉ ከመጽሐፍት ሳይወጡ ሌት ተቀን ያስተማሩን፥ ያገለገሉን፥ በአባቶቻቸው እምነት ጸንተው የቆሙት መምህር አሰተርአየ ጽጌ ናቸው።

አንባቢ ሆይ!!! ይህንን ጽሑፍ አንብባቹህ እውነቱ ላይ ለመድረስ እንድትችሉ፥ መስፈርታቹህ፥ የኔ አላዋቂነትና ተራ ምእመን መሆን ሳይሆን፥ በጽሑፉ ላይ የቀረቡት ነጥቦችና ማሰረጃዎች፥ ቤተ ክርስቲያናችን ጽፋ ባስቀመጠችልን፥ ሊቃውንት አባቶች ባሰተማሩትና በመሰከሩት ተጨባጭ እውነታ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን በትህትና እጠይቃለሁ።

ጽሑፉ፥ ለአንባቢ የበለጠ ግልጽና ለመከተል እንዲያመች:

- ከመሪ-ጌታ ጽሑፎች ላይ የምወሰዳቸውን ሐረጎች በቀይ ቀለም፥
- ከመጽሐፍ ቅዱስ የምጠቅሳቸውን ጥቅሶች ደግሞ በሰማያዊ ቀለም
- ከሊቃውንቱ የምጠቅሳቸውን በጥቁር ቀይ
- በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ከተጻፉት መጽሐፍት ስጠቅስ ደግሞ (Magenta). ቀለም እጠቀማለሁ።

እንባቢ ሆይ!! በዚህ ጽሑፍ ላይ ስለምታገኙት የፊደል ግድፈትና የቃላት ስሕተት: በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየኩኝ፥ በተቻላቹህ መጠን እያረማቹህና እያቃናቹህ በንጹህ አይምሮ እንድታነቡት በትሕትና እጠይቃላሁ።

# የአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ጥንተ አብሶ (Original Sin)
## በኦርቶዶክሳዊያን አባቶቻችን ግንዛቤ

በመግቢያው ላይ እንደገለጽኩት: የዚህ ጽሑፍ ዋና አላማ: መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ በጻፏቸው ሁለት ጽሑፎች ላይ የሚያተኩር ቢሆንም፥ ወደሳቸው ጽሑፍ ከመሄዴ በፊት: በዘመኑ አጠራር "ጥንተ አብሶ" (Orginal Sin) የሚለውን አባባል አባቶቻችን በምን መንገድ እንደሚያዩትና እሱንም ለመግለጽ ይጠቀሙባቸው የነበሩትን ቃላቶቸ (ሐረጎች) ምን እንደነበሩና፥ የኔ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊም ሰለነዚህ ቃላቶቸ ያለኝን ግንዛቤና አመለካከት ከወደዚሁ መግለጹ፥ ለማንኛውም አንባቢ በዚህ ጉዳይ ላይ ከምን ተነሰቼ ምን ማለት እንደፈለኩኝ ለማወቅ ሰለሚረዳ እንደሚከተለው በትህትና አቀርባለው።

በምዕራባዊያን አብያተ ክርሰቲያናት ግንዛቤ የሰው ልጅ ሲወለድ ኃጢአተኛ ሁኖ ነው የሚወለደው በሚል አመለካከት: በሮማ ካቶሊኩ St. Augustin ፍልሰፍና የተጀመረውንና ከሱ በኃላ የነበሩ እንደነ St.Thomas Aquaines የመሳሰሉ የሮማ ካቶሊክ ቤተ/ክ ሊቃውንቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲያርሙትና ሲያሻሽሉት የኖሩት፥ ዛሬ በዘመናቸን አጠራር "ጥንተ አብሶ" የምንለው (Original Sin) ተብሎ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይታወቃል።

በአንጻሩ ደግሞ ኦርቶዶክሳዊያን አባቶቻችን፥ በመጀመርያው ሰው: በአዳም በደል ምክንያት በሰው ዘር ሁሉ ላይ የወደቀውን እዳ ለመግለጽ ይጠቀሙበት የነበረው አባባል: አርዑተ ኃጢአት (የኃጢአት ቀንበር)፥ ቁራኝነት (መያያዝ፥ሰንሰለት) ወይንም የአዳም መርገም በማለት ሲሆን: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በ ፲፱፻፹ዎቹ መጀመርያ አካባቢ፥ በአሁን ሰአት የኢ.ኦ.ተ. ቤተ/ክ ሊቃውንት ጉባኤ አባል በመሆን በማገልገል ላይ የሚገኙት ክቡር መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት እና የካህናት ተልእኮ" በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው ላይ አርዑተ ኃጢአትን ለመግለጽ (ጥንተ አብሶ) የሚለውን ቃል በመጠቀም ካሰፈሩት ባኋላ፥ ይህ ቃል የጥንቱን አባባል በሰፋት እየተካው መጥቷል። ሆኖም ግን፥ ክቡር መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ይህ (ጥንተ አብሶ) የሚለውን አባባል: አባቶቻችን አርዑተ ኃጢአት፥ ቁራኝነት እያሉ ከሚሰጡት ትርጉም ይዘቱን ሳይለቅ ቢጠቀሙበትም፥ አባባሉን ቃል በቃል ለተመለከተው እንደኔ ላለ አላዋቂ፥ ቃሉ የሚያተኩረው: አባታችን አዳም ሰለበደለው በደል ማለትም: ድርጊቱን (ፈጣሪው አትብላ ብሎ ያዘዘውን እጸ በለስ በመብላት መበደሉን) እንጂ፥ በደሉ ስላሰከተለው መዘዝ ማለትም፥ ሞትን የሚገልጽ አይደለም። በአንጻሩ ደግሞ ከላይ የጠቀስኳቸው አባቶቻችን ይጠቀሙባቸው የነበሩትን አጠራሮች: ቃል በቃል ሰንመለከታቸው የሚሰጡን ግንዛቤ፥ ከአዳም በደል የተነሳ የሰው ዘር በሆነ ሁሉ ላይ የወደቀውን፥ ጫና፥ቀንበር እንዲሁም አንደ ሰንሰለት በመሆን የሰው ፍጡር የሆነውን ሁሉ የሚያሰተሳሰረንን ብሎም የማይቀረውን፥ ሆኖም ግን: ክርሰቶሰ በመሰቀል ላይ በከፈለው ዋጋ ትርጉሙ የተቀየረውን፥ አዳም ሰለመበደሉ ፈጣሪው ሰለበደሉ ቅጣት ያወጀበትን ሞት፥ ይገልጻሉ። ስለሆነም፥ ይህ ጥንተ አብሶ የሚለው ቃል: ከሌሎቹ ከላይ እንደጠቀስኳቸው የኦርቶዶክሳዊያን አባቶቻችን አባባልና ይዘት ይልቅ: ለእንግሊዘኛው (Original Sin ) አባባል በይበልጥ ይቀርባል።

አዳም ከበደለ ባኋላ በሰው ሁሉ ላይ የመጣው ይኸ የውርስ ኃጢአት: ሰው በተፈጥሮው የሚወርሰው ሰባዊ ባሕርይ ስለሆነ: እመቤታችንም ሰው ሁና እንደኛው ከእናት እና ከአባት በመፈጠሯ: ጥንተ አብሶ ነበረባት ሲባል በሰዎች እይምሮ ላይ ኃጢአት ያለባት እና ኃጢአተኛ እንደሆነች መሰሎ ሊታይ ይችላል። ይህ ፈጽሞ ትክክል አይደለም። እንኳን የአምላክ እናት እመቤታችን ቀርቶ ማንኛውም ሰው ሲፈጠር ኃጢአተኛ ሁኖ አልተፈጠረም። ለዚህም ነው ክርሰቶስ *"እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን ደግሞ ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም አይተው ገሠጹአቸው። ኢየሱስ ግን ሕፃናትን ወደ እርሱ ጠርቶ። ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተውአቸው አትከልክሉአቸውም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና። እውነት እላችኋለሁ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አለ።(ሉቃ.፲፰፥ ፲፭-፲፯)*

ያለው። ሆኖም ግን በአዳም በደል ምክንያት ሰው ሆኖ በተፈጠረ ሁሉ ላይ ታውጆ የሚያንዣብበው ይህ የሞት እዳ፣ ህጻናትንም ቢሆን እንኳን ተወልደው፥ ገና ሳይወለዱም በእናታቸው ማህፀን ውሰጥ እያሉ ይቀሰፋቸዋል። ይህ ለማንም የማይቀር ቀንበር የሞት እዳ፣ ህጻን አይል አዋቂ፣ ጻድቅ አይል እርጉም፥ አንዱንም የማይተው፥ ዘለዓለማዊት ድንግል ንጽኀት ቅድስት እና ብፅዕት የአምላክ እናት የሆነችውን እመቤታችንንም ቢሆን፡ እንደኛው ሰው ሁና በመፈጠሯ አልዘለላትም። ለዚህ ነው ቅዱስ ያሬድም *"ሞትስ ለመዋቲ ይደሉ ሞታ ለድንግል የአጽብ ለኩሉ" "ሞትስ ለሟች ይገባዋል፡ ሁሉን የሚያስደንቀው ግን የድንግል መሞት ነው።"* ብሎ ያለው። ይህን ደግሞ ማንም ሊክደው የማይገባ እውነት ነው።

አዎ አንዳንዶች እንዲህ ከሆነማ፣ ክርስቶሰም የሞተው የሰው ዘር በመሆኑ በአዳም መርገም የተነሳ ነው ማለት ነውን? ይላሉ። ይህ ፍጹም ስህተት ነው። በመጀመርያ ደረጃ የጌታችንና የመድኃኔታችን የእየሱስ ክርሰቶሰ አወላለዱም ሆነ አሟሟቱ ከሰው ልጆች ሁሉ የተለየ ነው። ይሄውም፥ አዳምን ከልጅ ልጅህ ተውልጄ አድንኀለው ባለው መሰረት፥ በእርሱ ፈቃድ በአባቱና በመንፈስ ቅዱሰ ፈቃድ ከሰማይ ወርዶ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት ተወለደ። እንደዚሁም፥ የፈጠረውን ሰው ለማዳን ሰአቱ በደረሰ ጊዜ፥ አባት ሆይ ነፍሴን ተቀበላት ብሎ በራሱ ፈቃድና ስልጣን ነፍሱን ከሰሥው ለየ። *"ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።" (ዮሐ, ፲፥ ፲፯-፲፰)*

እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው አዳምን ሲፈጥረው ከሌሎች ፍጥረታት በሙሉ ለይቶ (እብልጦ) በአምሳሉ ፈጠረው። *"እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካቸን፥ እንደ ምሳሌአችን፥ እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን እንሳሳትንና በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴትም አድርጎ ፈጠራቸው። ዘፍ. ፩፥ ፳፮-፳፯ "* ይህም ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲህ አብልጦና ቀድሶ የፈጠረውን ሰው ወስዶ በገነት አኖረው። *"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወሰዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው። ዘፍ. ፪፥ ፲፭"* ከዚህ በመቀጠል እግዚአብሔር ይህንን በአምሳሉ የፈጠረውን ሰው በዔድን ገነት ሲያኖረው ከአንድ የማሰጠንቀቂያ ትእዛዝ ጭምር ነበር። ይሄውመ ትእዛዝ፥ *"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፥ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፡ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያሰታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ። ዘፍ. ፪፥ ፲፮-፲፯"*

እንግዲህ ከዚህ ከላይ ካየነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የምንረዳው፥ እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር ካቀደበት ጀምሮ፡ በዔድን ገነት እሰካኖረው ጊዜ ድረስ፡ የሚከተሉትን አምስት አበይት ነጥቦች እንገነዘባለን። እነዚህም

፩ኛ. ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ
፪ኛ, ሰው ሲፈጠር መምረጥ እንደሚችል ሆኖ መፈጠሩ
፫ኛ. እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የመምረጥ እድልን የሚሰጥ መሆኑን
፬ኛ. እግዚአብሔር ፈጣሪ በመሆኑ እንደሚያዝና እንደሚቀጣ
፭ኛ. የእግዚአብሔርም ቅጣት ሞት እንደሆነ
፮ኛ. ገነተ ውሰጥ ሞት አለመኖሩ ናቸው።

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው የሰው ልጅ ለፈጣሪው ታዛዥ ሆኖ እግዚአብሔር ያዘዘውን ትእዛዝ እሰከጠበቀ ድረሰ ሞት የሚባለው አሰከፊ ቅጣት እንደማይደረሰበትና በዔድን ገነት በደሰታ እንደሚኖር፥ ፈቃዱም ከፈጣሪው ፈቃድ ያልዋጣ እንደሚሆን ሲሆን፡ በተቃራኒው ደግሞ የፈጣሪውን ትእዛዝ ሳያከብረ ፈቃዱን ከፈጣሪው ፈቃድ ያቃረነ ከሆነ ያለምንም ማወላወል እንደሚሞት በእግዚአብሔር ተነግሮታል።

እንግዲህ እዚህ ላይ አዳም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባይጠብቅ የሚደርስበት ይህ ሞት

የሚባለው ቅጣት ምንድነው? የሚለውን ከባድ ጥያቄ ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈውን እንመልከት። አዳም የፈጣሪውን ትእዛዝ አፍርሶ አትብላ የተባለውን እፀ በለስ እንደበላ ሲፈጠር የነበረው የእግዚአብሔር ክብር ከላዩ ላይ ተገፈፈ። በነፃነት በዔድን ገነት ይመላለሰ የነበረ አዳም እራቁቱን እንደሆነ አወቀ በአፍረት ተጨማደደ። የእግዚአብሔር ክብርና ፍቅር ከእርሱ እንደተለየ እግዚአብሔር ሳይነግረው ህሊናው አወቀ ሰለዚህም: ከፈጣሪው ፊት እራሱን ደበቀ። የኃጢአት ግድግዳ በእግዚአብሔርና በሰው መሐል ተተከለ።

*"እባብም ለሴቲቱ አላት። ሞትን አትሞቱም፤ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ። የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፥ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ።እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ። ዘፍ. ፫፥ ፮-፰"*

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "...ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ብሎ በተናገረው መሰረት የሚከተለውን ቅጣት ከእባብ በመጀመር ወሰነ፥ *"እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው። ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፤ በሆድህም ትሄዳለህ፥ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ። በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ። ዘፍ. ፫፥ ፲፬-፲፭"* በመቀጠልም፥ *"ለሴቲቱም አለ። በፀነስሽ ጊዜ ጭንቀሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጂለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል። ዘፍ. ፫፥ ፲፮"* በመጨረሻም ከአፈር አበጅቶ የፈጠረውንና ቀጥተኛ ትእዛዙን የሰጠውን *"መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ"* ያለውን አዳም የሚከተለውን ቅጣት ወሰነበት፥ *"አዳምንም አለው። የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና። ዘፍ. ፫፥ ፲፯-፲፱"*

እዚህ ላይ ልናሰተውል የሚገባው ነገር በአዳም በደል ምክንያተ እባብ: ሴቲቱ እና አዳም ለየብቻ የተወሰነባቸውን እርግማንና ቅጣትን ነው ይሄውም፥

፩ኛ. የእባብ ከእንስሳትና ከምድር አራዊት ሁሉ ተለይቶ መረገም
፪ኛ. በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በሆዱ እንዲሄድና አፈርን እንዲበላ
፫ኛ. በእባብ ገላ ተሰውሮ አዳምን ባሳተው ዲያቢሎሰ እና በሴቲቱ መካከል ጠላትነትን ማድረግ
፬ኛ. በዘሩና በዘሯ መካከል ጠላትነትን እንደሚኖርና ክርሰቶሰም የሠይጣንን እራሰ እንደሚቀጠቅጥ ሠይጣንም እንደሚታገለው
፭ኛ. ሴት በእርግዝና ወራቷና በመውለጃዋ ጊዜ ጭንቅ እንዲበዛባት
፮ኛ. ከዚህ ሁሉ ጭንቅ በኃላ ወደ ባሏ እንድትመለሰና እንዲገዛት
፯ኛ. ምድር ከአዳም ኃጢአት የተነሳ እንደተረገመች
፰ኛ. ምድር እሾህንና አሜከላን እንድታበቅል መሆን
፱ኛ. አዳም በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በልፋትና በድካም እንዲኖርና
፲ኛ. ከአፈር እንደተሰራ ሁሉ ወደ አፈር እንዲመለስ

እዚህ ላይ የሚያሰደንቀውና የሚያሰገርመው ነገር: ሠይጣን አዳምን ሊያሳስት አንደበቱንና ሥጋውን የተጠቀመበትን እባብ፥ እግዚአብሔር አፈር እንዲበላ ሲረግመው በሌላ በኩል ደግሞ ፈቃዱን ለሰይጣን ያሰገዛውን አዳም ወደ ተሰራበት አፈር መለሰው። በተዘዋዋሪ የእባብ ቀለብ (ምግብ) አዳም መሆኑ ነው።

እንግዲህ በጥቅሉ፡ አዳም (የመጀመሪያዎቹ ሰዎች) ስለሰሩት በደልና ስለደረሰባቸው ቅጣት ከገለጽኩ በኋላ ወደሚቀጥለው ነጥብ እገባለው። ይሄውም፡ በኦርቶዶክስ እምነት ከነዚህ ውስጥ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ከዘር ወደ ዘር የሚተላለፍ አለ ወይ? የሚተላለፍ ካለስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለሰው ልጅ ሲል የከፈለው መስዋትነተ የሚተላለፈውን አቁሞታል ወይ? የሚሉትን ጥያቄዎች አቅሜ እንደፈቀደ ለመመለስ እሞክራለው።

ለአዳም ትልቁና ዋነኛው ጥፋቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ረግጦ ፈቃዱን ለሰይጣን ማስገዛቱ ነው። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርም ፊቱን ከአዳም አዞረ። ከዚህም የተነሳ ዘላለማዊ ሆኖ እንዲኖር የተፈጠረው አዳም፡ በነፍሱም በሥጋውም ሞት ተፈረደበት። ይሄም ማለት መሬት(አለም) በመረጋጊ ምክንያት እንደ ዔድን ገነት ለሰው ልጅ ምቹ ባለመሆኗ፥ የሰው ልጅ ሲኖርባት በምትፈጥርበት ውጣ ውረድ የተነሳ ከተወለደ ጀምሮ በግዳጅ ወደማጣበት መሬት በሞት እስከሚመለሰበት ድረስ፡ በለበሰው ሲጋ መከራውን ያያል። ይሄም ብቻ ሳይሆን፡ ፋቃዱን ለሰይጣን በማስገዛቱ አይምሮውና ምኞቱ ለኃጢአት የተጋለጡ ሆኑ። ነፍሱም ከሥጋው ስትለይ፥ ከላይ እንደገለጽኩት ሥጋው ወደ አፈርነት ሲመለስ ነፌሱ ግን በሲኦል ለዘላለም በፍዳ ትያዛላች። ይሄን አባቶች "ሞተ ነፍስ ሞተ ሥጋ" ይሉታል። ሴት ደግሞ፡ አዳም ፈቃዱን ለሰይጣን እንዲያስገዛ ምክንያት በመሆኗ፡ ፈቃዷን ለባሏ የማስገዛት ባሕርይ ሲጫንባት፥ በተጨማሪም፡ በስቃይ እንድትወልድ ለሚያደርጋት ምጥና ጭንቀት ተጋለጠች።

ከዚህ በመነሣት፡ ኦርቶዶክሳዊያን አባቶች የሚሉት፥ አዳም በሰራው ኃጢአት ምክንያት ሲፈጠር የነበረውን የዘላለማዊነቱን ፀጋ ተገፈፈ። በነፍሱም በሥጋውም ሞት ታወጀበት። ይህ የታወጀበት ሞት በእርሱ የሚቆም ሳይሆን፡ ቅዱስ ጳውሎስ *"በበደሉትም ባልበደሉትም ደረሰ" (ሮሜ ፭:፲፪-፲፬)* እንዳለው፥ የአዳም ዘር በሆነ ላይ ሁሉ የሚደርሰ ሆነ። ይህ የማይለቅ ሰው በሆነ ሁሉ ሰብአዊነቱ ውስጥ የተቀበረ ጊዜውን ጠብቆ በሁሉም ላይ የሚፈነዳ የሞት እዳ አርዑት (ቀንበር)፥ አዳምን፥ ከእርሱ የሚመነጨውን ሁሉ ሰብአዊ ዘር የሚያቆራኝ የሞት ሰንሰለት ወይንም ቁራኝነት ተባለ። ሆኖም ግን፡ ይህ በአዳም በደል ምክንያት በሰው ልጆች ሁሉ ላይ የታወጀው ዘላለማዊ ሞት፥ *"ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና።፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥፳፪"* ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው፥ ጌታችንና መድኃኒታችን እየሱሰ ክርሰቶሰ በቀራንዮ መሰቀል ላይ በከፈለው ካሣ ተበጠሰ፥ በክርስቶስ አምነውና ተጠምቀው ለሚሞቱ ሁሉ የሞት ትርጉም ተለውጦ ጊዜያዊ እረፍት ተባለ። *"ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና።፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥፳፩" ተባለ::*

ከዚህ በመቀጠል በክርሰቶሰ ሞት በአዳም ላይ ታውጆ የነበረው የሞት ካሳ ከተከፈለ ታዲያ አሁንሰ ለምን እንሞታለን? የሚል ተገቢ ጥያቄን ያሰነሳል። ሆኖም ግን ለዚህ መልሱ፡ ክርሰቶሰ በመሰቀል ላይ በራሱ ፈቃድ የሞተው፥ የፈጠረውን አምላክ በድሎ ፈቃዱን ለሠይጣን ያሰገዛውን አዳም መልሶ ፈቃዱን ለአምላኩና ለፈጣሪው እንዲያሰገዛ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን የኃጢአት ግድግዳ፥ አርዑት (ቀንበር) በጣጥሶ እድሉን በድጋሚ ሊሰጠው ሰለወደደ ብቻ ነው። ይህም ማለት፥ *"እሱ ቀድሞ ሰውን በንጽሐ ጠባይዕ ፈጥሮ በወደደው ሥራው ተወው። ትእዛዙን ትጠብቅ ዘንድ ሃይማኖቱንም ታጸና ዘንድ ብትወድ ግን ፈቃዱ ነው። እጅህን በመረጥኸው ትጨምር ዘንድ እነሆ እሳትና ውኃን አኖረልህ። ጽድቅና ኃጢአትን። (ሲራክ ፲፭፥ ፲፬-፲፯)* ብሎ ሲራክ እንደተናገረው፥ እግዚአብሔር አዳምን በዔድን ገነት ሲያኖረው፡ ያዘዘውን ትእዛዝ አፍርሶ ዘላለማዊ ሞት እንዳይሞት ምርጫ እንደሰጠውና አዳምም ምርጫውን በማበላሸቱ ቢወድቅም፥ ታዳጊና ርኅሩህ ፈጣሪው አሁንም አልተዎውምና በአብ በወልድ በመንፈሰ ቅዱሰ ሰም አምኖና ተጠምቆ ዘላለማዊነቱን እንዲያገኝ (እንዲያስመልስ) በድጋሚ ምርጫ ሰጠው።

እዚህ ላይ ልንረዳው የሚገባው፥ ዋና ነገር፡ በአብ በወልድ በመንፈሰ ቅዱሰ ሰም የምንጠመቀው በአዳም በደል ምክንያት በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል ያለውን የሞት ግድግዳ፥ የሞት ቀንበር ወይም ቁራኝነት ለማሰወገድና እንደገና ለመወለድ ማለትም አዳም በዔድን ገነት ፈቃዱን ለአምላኩ እንዲያሰገዛ ምርጫ እንደተሰጠው ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈሰ ቅዱሰ ሰም

የምንጠመቀው ከማንኛውም ኃጢአት ነጽተን ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር በፍፁም እምነት መልሰን በመስጠት በጥምቀቱ የፈጸመልንን ጽድቅ በመጎናጸፍ፥ የእግዚአብሔርን መንግሰት ለመውረሰ ነው። ለዚህም ነው ክርስቶስ፥ " *አሁንስ ፍቀድልኝ፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና... ማቴ. ፫፥፲፭)* ሲል የተናገረው ቃል: የጥምቀትን ዋነኛነትና አስፈላጊነት አጉልቶ የሚያሳይ መሰረት ነው። ከዚህም ጋር አያይዞ እራሱ ጌታችን *"ኢየሱስም መልሶ። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው። ኒቆዲሞስም። ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው። ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ዮሐ. ፫፥ ፫-፭"* ሲል ነግሮናል። ሆኖም ግን: በጥምቀት ያገኘነውን የመምረጥ እድል ተጠቅመን: ምድራዊ የህይወት ዘመናችንን ሁሉ በፍጹም እምነትና ንሰሐ ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር ካላሰገዛን፥ ተመልሰን ወደዘላለማዊ ሞት ልንገባል እንደምንችል መዘንጋት የለብንም።

በአዳም ላይ ታውጆ የነበረው ዘላለማዊ ሞት፥ በክርሰቶሰ ሞት እና ትንሳኤ ትርጉሙ ተቀየረ። የክርሰቲያን ሞት: ከዚህ አለም ውጣ ውረድ ማረፍ እንጂ፥ ዘላለማዊ ሞት መሆኑ ቀረ። ለምንመኘውና ለምንናፍቀው በሰማያዊ አለም ለመወለድ: ዛሬ በሞት ተጸነስን እንደማለት ነው። ሆኖም ግን የክርሰቶሰ ሞት የቀየረው፥ በአዳም በደል ምክንያት በሰው ሁሉ ነፍሰ እና ሥጋ ላይ የታወጀውን አሰከፊ ፍጻሜ፥ ማለትም፥ የሥጋችን ወደ አፈርነት መመለሰንና የነፍሳችን ለዘላለም በዳያቢሎስ መያዝን እንጂ፥ የነፍሰና የሥጋን ጊዚያዊ መለያየት አልቀየረውም። ምክንያቱም፥ አሁንም ቢሆን ሥጋችን እና ነፍሳችን ያለ ውድ: በግዴታ ለጊዜውም ቢሆን በሞት ይለያያሉና። ይህም ብቻ ሳይሆን: ሴት ደግሞ፥ አዳም ፈቃዱን ለሰይጣን እንዲያስገዛ ምክንያት በመሆኗ፥ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል። ተብሎ የታወጀባት እዳ፥ አሁንም ቢሆን አልቀረላትም። በአዳም በደል ምክንያት የተረገመችው ምድርም፥ እሾህ አመኬላ ማብቀሏን ጨመረች እንጂ አላቆመችም። በጥቅሉ: የክርስቶስ ሞት፥ አዳም በዔደን ገነት እያለ በመረጠው ምርጫ: ሞትና እሮሮ የሞላባትን መሬት እንደወረሰ ሁሉ፥ አሁን ደግሞ የሰው ልጅ፥ በክርሰቶስ ሞት መሬት ላይ እያለ ምርጫውን አሰተካክሎ ከሞት በኋላ ያለውን ዘላለማዊ ሕይወት የሚገኝበትን መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ ነው። ክርሰቶሰ በሰልጣኑ ሞትን ድል አድርጎ በሥጋው እንደተነሳ ሁሉ፥ ክርሰቲያንም በክርሰቶሰ እንደምንነሳና ዳግመኛ ሞት የሌለበት ዘላለማዊ ሕይወት እንደሚኖረን እናውቃለንም እናምናለንም። ሰለዚህም ነው በጸሎተ ሃይማኖታችን ላይ እንዲህ የምንለው፥ *"....የሙታንንም መነሳት ተሰፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለም አሜን።"* መጽሐፍ ቅዱሰም ይኸንን አጉልቶ ሲነግረን እነዲህ ይላል፥ *"ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣም፤ ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ። ፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥ ፲፮-፲፯"*

በመጨረሻም ላማሳሰብ የምፈልገው: የጌታችንና የመድኀኒታችን የእየሱስ ክርሰቶስ ሞት ከእኛና ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሞት ጋር ፈጽሞ እንደማይገናኝ ነው። ክርሰቶሰ በራሱ ፋቃድ የኛን ሞት የሞተው የአዳም ዘርን ከተጣለበት የዘላለም ሞት ለማዳን ብቻ እንጂ: እንደማንኛውም ሰው በአዳም በደል ምክንያት በመጣበት የመሞት ግዳጅ አይደለም። እንዳንድ ሰዎች እንደሚሉትም: የክርሰቲያን ሞት፥ ክርሰቶሰን በሞቱ ለመምሰል ነው ማለት ፈጽሞ ሰህተተ ነው። ምክንያቱም የሞታችን ምሳሌዎች አዳምና ሔዋን ሲሆኑ፥ ከእነሱም ይልቅ ለእነርሱ የተነገረውን የሞትን ትርጉም በተግባር ያዩበት የመጀመሪያው ሟች የልጃቸው "የአቤል ሞት" እንጂ የክርስቶስ ሞት አይደለም::

ቅዱሰ ጳውሎስ የጥምቀትን ነገር ሲገልጽ: ከክርሰቶሰ ሞት ጋር በንጽጽር እንዲህ ሲል አቀረበው እንጂ፥ የእኛን ሞት ከክርሰቶሰ ሞት ጋር ፈጽሞ አላመሳሰለውም። *"እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር*

*ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንዝሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። ሮሜ ፮፥፩-፬"*

እንግዲህ ከላይ ሰፋ ባለ መንገድ በአባታችን በአዳም በደል ምክንያት በሰው ዘር በሆነ ሁሉ ላይ የታወጀውን ሞት፥ አባቶች እንዴት ብለው እንደሚገልጹትና ይህ የሞት ግዴታ ከክርሰቶሰ በቀር ሰው ሁኖ በተፈጠረ ሁሉ ላይ ግዳጅ በመሆኑ፡ ማንም ከሞት እንደማያመልጥም አይተናል። እመቤታችንም የዚሁ እጣ ተካፋይ እንደሆነችም ተገንዝበናል። ሰለሆነም፥ ይህንን እውነታ መሰረት በማድረግ፥ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ በጻፏቸው ጽሑፎች የያዙትን የተሳሳተ አቋምና ያቀረቡዋቸውን ማሰረጃዎች በሚከተሉት ፫ ነጥቦች እይታ በመገምገም፥ የደብረ ሣሕል መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ/ክ ምዕመናንና አባታችን ቀሲስ አሰተርአየ ፅጌ እንዲሁም መላው ኦርቶዶክሶች የሚቀበሉትን " እመቤታችን እንደማንኛውም የሰው ፍጡር ከአዳም የሚተላለፈው የውርስ ኃጢአት፥ አርዑተ ኃጢአት፥ መልዓኩ ቅዱስ ገብርኤል እሰኪያበስራት ድረስ ነበረባት" የሚለውን እምነት ትክክለኝነት አቀርባለው።

፩ኛ. እመቤታችን ከአዳም ዘር የተገኘች የሰው ዘር በመሆኗ፥ በአዳም በደል ምክንያት ሰው ሁሉ የመሞት ግዴታ ስላለበት እንደማንኛውም የሰው ዘር በተወለደች በ ፷፬ አመቷ ሞትን በግድ ሞታለች።

፪ኛ. እመቤታችን የሞት ግዳጅ ሳይደርስባት ከዚህ አለም ሳትሞት ተሰውራለች።

፫ኛ. እመቤታችን እንደ ልጇና ፈጣሪዋ እንደ ጌታችንና መድኃኔታችን እየሱስ ክርስቶስ በራሷ ሰልጣን ነፍሷንና ስጋዋን ለየች።

እንግዲህ ከላይ የሰፈሩትን ፫ ነጥቦች መሰረት በማድረግ፥ እመቤታችን ስትፈጠር የአዳም የውርስ ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) ውጤት የሆነው አርዑተ ኀጥያት፥ የሞት ቁራኝነት፥ አልደረሳባትም ካልን፥ ተራ ቁጥር ፪ ወይንም ፫ እውነት ሊሆኑ ነው ማለት ሲሆን። በተቃራኒው ደግሞ፡ እመቤታችን እንደማንኛውም ሰው ስትፈጠር የአዳም የውርስ ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) ውጤት የሆነው አርዑተ ኃጢአት፥ የሞት ቁራኝነት፥ ደርሶባታል ካልን፥ ተራ ቁጥር ፩ እውነት ሊሆን ነው። እዚህ ላይ ቅድስት ቤተክርስቲያናችንም ሆነች መላው ኦርቶዶክሱ የሚሰማማውና የሚያምነው፡ በተራ ቁጥር ፩ ላይ የሰፈረውን ሲሆን፥ እንደውም አባቶቻችን "ሞት በጥር በነሐሴ ቀብር" በማለት የእመቤታችንን ሙሉ ሰው መሆን እስከ ሞቷ ድረሰ በመግለጽ አልፈዋል። ይህንን እውነታ እኔም፥ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴም፥ ቀሲስ አሰተርአየም ሆነ መላው የኦርቶዶክስ አማኝ የማንክደው ሆኖ ሳለ፥ መጽሐፍትን በራስ ግንዛቤ በመተርጎምና በማጣመም ሊቃውንቱ አባቶቻችንና እራሷ እመቤታችን በአንዳበቷ *"ነፍሴ በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች..."* ያለችውን በመካድ መሰረት የሌለው አለማዊ ፍልስፍና ማቅረብ እመቤታችንንም ሆነ ኦርቶዶክሳዊያን አባቶቻችንን ቃላባይ ማድረግና ድፍረትም ነው።

## በመሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ በተጻፈ ጽሑፍ፥
## <u>በጽሑፉ መግቢያ ላይ ስላሰፈሩት ስሕተት የተሰጠ ምላሽ</u>

በመጀመርያ ደረጃ ይህንን ከበድ ያለ የሃይማኖት ጉዳይ አሰመልክቶ: የደብረ ሣሕል መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርሰቲያን ምእመናንና አባታችን ቀሲሰ አሰተርአየ ፅጌ በያዝነው አቋምና: በሕዝብ መወያያ ድሕረ ገፆች ላይ በሚወጡት ጽሑፎች ላይ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ ተሳታፊ በመሆን የሚሰማዎትንና ያለዎትን እምነትና አቋም በማካፈለዎ፥ ለውይይቱ መሰፋፋትና ብሎም ለመማርና ለመማማር ሰለሚጠቅም ከልብ አመሰግናለሁ። *"የተጻፈ ሁሉ ለተግጻጽና ለትምህርት ነው"* የሚለውን የቅዱስ ጳውሎሰን ቃል መመርያ በማድረግ፥ ጽሑፎዎን አሰመልክቼ ደግፌም ሆነ ነቅፌ የምሰጠው አሰተያየት፥ ትኩረቱ በአርሰዎ ማንነት ላይ ፈጽሞ ሳይሆን፥ በምንነጋገርበት ጉዳይ ሰላለዎት አቋም ላይ መሆኑን በቅድሚያ ከወዲሁ ላሳሰበዎት እወዳለው።

መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ፥ ወደ ዋናው የነገረ ሃይማኖት ጉዳይ ከመግባቴ በፊት በ መሰከረም ፲ ፱ሺ፱ ዓ.ም. በጻፉት ጽሑፍዎ፥ ከጽሕፍዎ አርእሰት ጀመሮ ሙሉ በሙሉ በመጀመርያው ገጽ ላይ ያሰፈሩት አሰተያየት እጅግ የሚያሳዝን ነው። ይህንንም ሊያሰኘኝ የቻለበት ምክንያት፥ *<u>በሃይማኖት ጋልቃ ገቢዎች ኢትዮጵያዊያን አይከፋፈሉም።</u>* በማለት የጀመረው ጽሕፈዎ በመቀጠል፥

*የዚች ጽሑፍ ምክንያት፥ ባሁኑ ወቅተ እናት ኢትዮጵያ በሁለት በትረ ስልጣኖች (ቤተ ክህነት ቤተ መንግሥት) የገጠማትን ታላቅ የፈተና ወቅት በመጠቀም ከውጭ በኩል በወዳጅነት ግልባብ ( MASK) በመሸፈን፤ ሕዝቡን ለመከፋፈልና እርስ በርሱ እንዳይሰማማ ለማድረግ የሚጠቀሙበትን የፖለቲካም ሆነ የሃይማኖት ጋልቃ-ገብነት የኢትቶጵያ ሕዝብ በጥንቃቄ እንዲመለከተው፤ በተጠንቀቅ እንዲጠብቀው ለመጠቆም ያህል ነው።* ብለዋለ፥

መሪ-ጌታ፥ እንደው ለመሆኑ እመቤታችን የአዳም የውርስ ኃጢአት ነበረባት ወይንስ አልነበረባትም የሚለውን የኢ.ኦ.ተ. ቤተ/ክ እምነትንና አማኞችን የሚመለከተውን የሃይማኖት ጉዳይ፥ የሐገረ አቀፍ ፖለቲካና ኢትዮጵያውያንን ለመከፋፈል በውጭ ጋልቃ ገቦቸ አነሳሽነት የተቀነባበረ ሴራ አሰመሰሎ ለማቅረብ መሞከረዎ፥ ከመንፈሳዊነቱ ይልቅ ወደ ዋነኛ ፖለቲከኛነቱ እንዳዘመሙ ያሳያል። ይህ ብቻ ሳይሆን፥ ነገረ መለኮቱን በተመለከተ ለሚያቀርቡት የማሳመኛ እሰጥ አገባ እንዲረዳዎ፥ ከመጀመሪያው የአንባቢን የውስጥ ሰሜት በመኮርኮር ሊያቀርቡት ከሞከሩት የማሳማኛ ነጥብ ይልቅ፥ ጭፍን ባለ የሐገር ፍቅር ተነስቶና ታዎሮ፥ እውነተኛው የኦርቶዶክስ እምነት ( Immaculate Conception) በመባል በሚታወቀው በሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ መተካቱን እንዳይረዳው ለማድረግ መሞከረዎ በጣም ያሳዝናል። ምክንያቱም፥

- ኢትዮጵያዊያን ሲሉ፥ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የኢ.ኦ.ተ. ቤተ/ክ አማኝ አድርገው በመውሰድ፥ የነገረ ሃይማኖቱ ውዝግብ ሁሉን ኢትዮጵያዊ ሊከፈፍል እንደሚችል አድርገው ለማቅረብ መሞከረዎ

- *"ባሁኑ ወቅተ እናት ኢትዮጵያ በሁለት በትረ ስልጣኖች (ቤተ ክህነት ቤተ መንግሥት) የገጠማትን ታላቅ የፈተና ወቅት በመጠቀም..."* በማለት የአዛኝ ቅቤ አንጓች እንዲሉ፥ ምን አልባት በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ (ቤተ ክህነትና ቤተ መንግስት) እርሰዎ እንዳሉት ችግር ላይ መሆናቸው ለእርሰዎ ታይቶዎትና ችግር ፈጥሮቦዎት ተሰምቶዎት እንደሆነ እንጂ፥ በቤተክርሰቲያናችን ላይ ችግሩ የጀመረው የቤተክርሰቲያኗ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከተገደሉበት ጊዜ ወዲህ ነው።

- በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ዛሬ እርሰዎ *"(ቤተ ክህነት ቤተ መንግሥት) የገጠማትን ታላቅ የፈተና ወቅት በመጠቀም..."* እያሉ ልክ እኛ ዛሬ ይህንን እርስዎ አለ የሚሉትን አጋጣሚ ተጠቅመን የነገረ ሃይማኖቱን ጉዳይ እንዳሰናሳነው ለማሰመሰል መሞከረዎ ከእውነት የራቀ ሀሰት ነው። ምክንያቱም፥ ይህ የነገረ ሃይማኖቱ ውዝግብ የተነሳው ከዛሪ አምስት አመት በፊት ሲሆን፥ ጉዳዩንም ለቅዱስ ሲኖዶስ፥ ለቅዱስ ፓትርያርኩና ለሊቃውንት ጉባኤ

ያሳወቅነው ያኔውኑ ነው። ማስረጃውን www.medhanialemeotcks.org ይመልከቱ።

ከዚህ በመቀጠልም፥

*ለዚህም መነሻ የሆነኝ አሁን በቅርቡ በአሜሪካ ካንሳስ ሰቴት የሚገኙ የደብረሣህል መድኃኔ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ? ቤተ ክርስቲያን ምእመናን (August 15, 2009; Quatero website) ያወጡት መግለጫ ነው። ምእመናኖቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ? ተከታዮች ነን ሲሉ ነገር ግን እናት ቤተ ክርስቲያን ስለ እመቤታችን ቅድስት ማርያም ለዘመናት የምታስተምረውን ወደጎን በመተው፤ ለማንም ግልጽ ባልሆነ ምክንያት የባዕድ ልብ ወለድ አሰተሳሰብ በመያዝ ሕዝብን ለማሳሳትና ለመከፋፈል የሚያደርጉት እሩጫ ነው።* ብለዋል

መሪ-ጌታ፡ ከላይ የደብረሣህል መድኃኔ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ያወጣነውን ማስታወቂያ ጠቅሰው የያዝነውን እምነት *"የባዕድ ልብ ወለድ"* በማለት የነቀፉት እምነት፡ "ምን የሰማለት ያብዳል' እንዲሉ አይሁንብኝና: እምነታችን የባዕድ እምነት ሳይሆን፡ የእውነተኛዎቹ የኢ.ኦ.ተ. አባቶቻችን፡ የአኀት አብያተ ክርስቲያናትና የመላው ኦርቶዶክሶች እምነት ነው። በአንጻሩ ደግሞ እርስዎ የያዙት (Immaculate Conception) የሮማ ካቶሊክ እምነት ነው። ሌላው ከላይ በጽሑፍዎ ላይ " *ተዋሕዶ ?"* ብለው የጥያቄ ምልክት ማስቀመጠዎ ተዋሕዶዎች መሆናችን ያጠያይቃል ለማለት ከሆነ፡ አይድከሙ። ምክንያቱም በሦስት ፓትርያርክ ጸድቆልናል። ማን ቢሉ? ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በጻፉት መጽሐፍ መሰከረውታል፡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሽኑዳም ያው እንደሚያውቁትና በቪድዮም ላይ እንዳዩት (August 15, 2009 ) በቅዱስ ማርቆስ የግ.ኦ. ቤተ ክርስቲያን በተደረገው ጉባኤ ላይ ወክለው በላኳቸው በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በኩል መሰከረውልናል፡ የሲርያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ሞራን ኢግናቲየስ ፪ኛ: ቁልጭ አድርገው (www.syrianorthodoxchurch.org) ላይ ጽፈውታል። በአጋጣሚውም: ኒው ጀርሲ በሚገኘው የሲርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አኀት አብያተ ክርስቲያናት ያደረጉትንና ወደፊት የሚያደርጉትን የሃይማኖት አንድነት ሰብሰባ እቅድና ፎቶ እዛው ድሕረ ገጽ ላይ ይመልከቱ። ብፁዕ አቡነ ዘካርያስም አሉበት። እንግዲህ እዚህ ላይ የሚመጣው ችግር፡ ከሳቸው በቀር ሌሎቹ በሙሉ ይህን የሮማ ካቶሊክ እምነት አይቀበሉም። የግብጹ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዴቪድ ይህን አሰመልክቶ ለኛ የጻፈልንን ደብዳቤ ጊዜ ካለዎት www.medhanialemeotcks.org ላይ ይመልከቱት። ተዲያ እንግዲህ እንዴት ቢሆን ነው የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ከሌሎቹ አኀት አብያተ ክርስትያናት ተለይታ ይኸንን የሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ የተቀበለችው?? ታዲያ *"የባዕድ ልብ ወለድ አሰተሳሰብ"* የያዘው እኛ ወይስ እርስዎ?? እንባቢ ይፍረድ።

ከዚህ በመቀጠልም፥

*ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳዛኝ የሆነው መነሻቸው "እመቤታችን ቅድስት ማርያም ጥንተ አብሶ አለባት፣ የአዳምን በደል ወርሳ ነው የተወለደቸው ፤..." የሚል ሲሆን፡* ብለዋል፥

መሪ-ጌታ፥"*ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳዛኝ የሆነው መነሻቸው"* ማለተዎ፡ አዎ በኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ካህንነተዎ፡ ቤተ ክርስቲያኗንና እምነተዎንም የመመስከርና ሀሳብዎንም የመሰጠት መብት ብቻ ሰይሆን ግዴታዎም ነው። ሆኖም ግን፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአድነት ተሰማምቶ እርሰዎን ወክሎ እንደላከዎት: አድርገው ለማቅረብ መሞከረዎ አሁንም በድጋሜ ስህተት ነው። ምክንያቱም፡ እኛም የደብረሣህል መድኃኔ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያን ምእመናን፡ አባታችን ቀሲሰ አሰተርአየና ኦርቶዶክሳዊያን አባቶቻችን ጭምር ኢትዮጵያዊያኖች ነን እኮ።

በመቀጠልም፥

*ይሄንንም ሰሕተት ከነርሱ አልፎ ሌላውን ለማሳመን ደጋፊ ያገኙ መሰሏቸው" የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያንን ጠይቀን መልስ ብናጣ ወደ ግብፅ ቤተክርስቲያን ጥያቄያችንን አቅርበን*

*አባ ሺኖዳ (የግብፅ ቤ/ክር መሪ) አጽድቀውልናል..." ያሉት እጅግም የሚያሳዝንና ከእውነት የራቀው ምክንያታቸው ነው።* ብለዋል፡

መሪ-ጌታ፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የሚያሳዝነውና ከእውነት የራቀው አባባል፡ ይህ እርሰዎ ከላይ እንደ እውነት አስመሰለው የተናገሩት ሀሰት ነው። ምክንያቱም፡ አዎ ነገረ ሃይማኖቱን በተመለከተ ጥያቄያችንን ለኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ቅዱስ ሲኖዶስ፡ ለቅዱስ ፓትርያርኩና ለሊቃውንት ጉባኤ ከአምስት አመት በፊት መላካችንን እውነቱን ላለማየት ህሊናውን ሆን ብሎ ካሳወረ ሰው በቀር፡ በገሀድ ማንም www.medhanialemeotcks.org ላይ ሊመለከተው የሚችል ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን: እስከአሁኗ ሰአት ድረስ፡ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያን ምንም አይነት መልስ አልተሰጠንም አልደረሰንንም። ነገረ ግን: በእርሰዎ በኩል ከቅዱስ ሲኖዶሱም ሆነ ከሊቃውንት ጉባኤው መልስ ተሰጥቷል ካሉ፡ ማሰረጃዎን ቢሰጡን ለእኛም ሆነ ለአንባቢዎችም መፍትሔ ይሰጥ ነበር። እውነቱ ግን እንዲህ ያለ ማሰረጃ ከራሰዎ ፈጥረው ካልሆነ በሰተቀር ከየትም ሊያመጡ አይችሉም። ይህም ብቻ አይደለም፡ ከኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር መልስ ባለማግኘታችን "ለግብፅ ኦርቶዶክስ ቤ/ክር" ነገረ ሃይማኖቱን በተመለከተ ጥያቄ ማቅረባችንንና ለጥያቄያችንም መልስ መሰጠቱን በአደባባይ ማሰታወቃችንን ፈጽሞ እንዳልተደረገና *"እጅግም የሚያሳዝንና ከእውነት የራቀ ነው"* ብለው ከአንድ ካህን የማይጠበቅ አይን ያወጣ ሀሰት መናገረዎ መንፈሳዊ አባትነተዎን እግምት ላይ ጥሎታል። ከግብፅ ኦርቶዶክስ ቤ/ክር የተሰጠውን መልስ አልስማማበትም ማለት አንድ ነገር ሲሆን፡ በተቃራኒው ግን የሆነን እንዳልሆነ አድርጎ ሸምጥጦ በመካድ፡ አንባቢውን ሕዝብ፡ እውነቱንና ሐሰቱን አይቶና አመዛዝኖ መፍረድ እንደማይችል በድን አድርጎ በመቁጠር ሆን ብለው እንዲህ ያለ ስህተት ማድረገዎ በጣም ያሳዝናል። ለማንኛውም፡ እውነቱን ለመረዳትና ለማወቅ ለሚሻ፡( www.medhanialemeotcks.org) እና በ youtube under the Title “Ethiopian Orthodox and Original Sin” በሚል ርእስ ሰር ከግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መልስ የተሰጠበትን የጉባኤውን ቪድዮ መመልከትና መፍረድ ይቻላል።

በመቀጠልም፡

*"ከዚህ ቀደም በመሪያቸው በቀሲስ አሰተርአየ አዘጋጅነት ለቤተ ክህነት ባቀረቡትና በግንቦት ወር ፲፱፻፺፯ "በዜና ልደታ" (በአሜሪካ የሚዘጋጅ ጋዜጣ/መጽሔት) ላይ የወጣውን ጽሑፍ አሰመልክቶ ጸሎታቸው አይለየን በረከታቸው ይደርብንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ "ዜና ሕይወት ዘቅድስት ቅዱሳን እመ አምላክ በሚባል መጽሐፋቸው አምልተውና አራቅቀው መልስ ሰጥተዋቸዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያን የሊቃውንት ጉባኤም ጽሑፉን አውግዞ ውድቅ አድርጎታል"* ብለዋል።

መሪ-ጌታ፡ በመጀመሪያ ደረጃ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት: አሁንም በድጋሚ፡ አመለካከተዎ ከመንፈሳዊነቱ ወደ አለማዊውና ፖለቲከኛነቱ ያደላ ለመሆኑ *"በመሪያቸው በቀሲስ አሰተራአየ..."* በማለት የቤተክርሰቲያን እራሷና መሪዋ ጌታችንና መድኃኔታችን እየሱሰ ክርሰቶስ ብቻ እንደሆነ እየታወቀ፡ እኛ የደብረሣህል መድኃኔ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያን ምእመናንን፡ እውነት የሆነውን የቅዱሳት መጽሐፍትን አውቀንና ተረድተን ከመቀበል ይልቅ፡ የራሳችን አሰተሳሰብና ግንዛቤ እንደሌለን በመቁጠር፡ በመንፈሳዊ አባታችንን በቀሲስ አሰተርአየ ሀሳብና ፍላጎት ብቻ አይናችንን ጨፍነን እንደምንመራ አድርገው ማቅረበዎ፡ ከኛ ይልቅ እርሰዎ ህዝብን እንዲያገለግሉበት የተሰጠዎትን ክህነት ለምን እንደሚያውሉት በግልጥ ያሳየናል።

መሪ-ጌታ: አሁንም በድጋሚ ሐሰት እየተናገሩ ነው። በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ፡ ጌታችንና መድኃኔታችን እየሱሰ ክርሰቶስ፡ *"እውነቱን እውነት: ሀሰቱን ሀሰት ማቴ. ፭፡፴፯"* በሉ አለ እንጂ "ሀሰቱን እውነት" በሉ ፈጽሞ አላለም። ሆኖም ግን ከላይ በማሰረጃ እንደገለጽኩት ጥያቄያችንን ለኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ቅዱስ ሲኖዶስ፡ ለቅዱስ ፓትርያርኩና ለሊቃውንት ጉባኤው ከአምስት አመት በፊት መላካችን እየታወቀና፡ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያን ቅዱስ ሲኖዶስም ሆነ

ከሊቃውንት ጉባኤው አንድም መልስ እንዳልተሰጠበት እየታወቀ እርሰዎ ግን ሰውን ለማደናገርና ለማወናበድ በ፲፱፻፹ ዎቹ አመታት የየዛንግዜው የሊቃውንት ጉባኤ ሊቀመንበር የነበሩት ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ፥ እኛ የላክነውን ጥያቄ ሊቃውንቱን ሰብሰበው ጉባኤ ዘርግተው መልስ እንደሰጡበትና የሊቃውንት ጉባኤውም ጥያቄያችንን እንዳወገዘው አድርገው እንዲህ ያለ ሐሰት ማቅረበዎ ተገቢ አይደለም።

እውነቱ ግን፥ ነፍሳቸውን ይማረውና፥ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ከሞቱ በኋላ፥ በግንቦት ፲፱፻፺፱ "ዜና ሕይወት ዘቅድስት ቅዱሳን እመ አምላክ" በሚል ርእስ በታተመ መጽሐፍ ላይ፥ በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ይታተም የነበረውን ዜና ልደታ የሚባል መጽሔትን፥ የሌሎች ሰዎችን ሰምና በይበልጥም የቀሲስ አሰተርአየን ሰም ያካተተ ጽሑፍ ይገኝበታል። የመጽሐፉ ዋና ፍሬ ሀሳብ፥ ስህተትን በስህተት ለመደገፍ የተሞከረበትና ከዚህ በፊት እራሳቸው ዳጋግመው ባሳተሟቸው መጽሐፍቶቻቸው ላይ "እመቤታችን ጌታችንን በጸነሰች ወቅት ነፍስዋም ሰጋዋም በመንፈስ ቅዱስ እንደነጻና እንደተቀደሰ" የመሰከሩበትንና የነበራቸውን አቋም የሚቃረን ሲሆን፡ በምትኩ ደግሞ "እመቤታችን የአዳም የውርስ ኃጢአት ያልደረሰባት ናት" የሚለውን የሮማ ካቶሊክ እምነትና ትምህርት የሆነውን በሚገባ የሚገልጽ ነው። በተጨማሪም፥ ቀሲስ አስተርአየን በተመለከተ፥ከአንድ ትልቅ አባት የማይጠበቅ ንቀት የተሞላበትና ተራ ዘለፋን የያዘም ነው። ሆኖም ግን ይህንን መጽሐፍና ሌሎቹንም መጽሐፍቶቻቸውን በተመለከተ በሰፊው በገጽ፡ ፳፫ ላይ በሰፊው እመለሰበታለው።

በተረፈ ግን፥ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ፥ ይህንን መጽሐፍ፥ እኛ የደብረሣህል መድኃኔ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያን ምእመናን ለኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ሊቃውንት ጉባኤና ለቅዱስ ሲኖዶሱ ላቀረብነው ጥያቄ፥ ከቤተ ክህነት መልሰ ሆኖ እንደተሰጠ አሰመሰለው ሕዝብን ለማወናበድ መሞከራቸው ፈጽሞ ተገቢ አይደለም። እኛ ለጥያቄያችን መልሰ የመሰጠት ሀላፊነትና ግዴታ ላለበት ለተገቢው ክፍል ማለትም፥ ለቅዱስ ሲኖዶሱና ለሊቃውንት ጉባኤው አቅርበናል። ሆኖም ግን ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ፡ እንደቤተክርሰቲያኗ ታላቅ አባትነታቸው፥ ጉዳዩን በተመለከተ ደግፈውም ሆነ ነቅፈውም፥ መጽሐፍ መጻፍ ይችላሉ። ይኸም ሊያሰመሰግናቸውና ሊያሰከብራቸው ይገባል። ሆኖም ግን፥ በወቅቱ ሐላፊነቱ ያለበት ክፍል ማለትም፥ የዘመኑ ቅዱስ ሲኖዶስና የሊቃውንት ጉባኤው፥ እኛ ሁላችንም በተለያዩ ወቅቶች ክቡርነታቸው ያጻፋቸውን መጽሐፍቶች እንደማስረጃ እየጠቀስን እንደምናቀርበው ሁሉ፥ ቅዱስ ሲኖዶሱም ሆነ ሊቃውንት ጉባኤው፥ ደግፎም ሆነ ነቅፎ ለሚሰጠው መልስ፥ ሊረዱን ይችላሉ ብለው የሚሏቸውን የክቡርነታቸውን መጽሐፍቶች እንደ ማሰረጃ ሊያቀርቧቸው ይችላሉ። ከዚህ ውጭ ግን፥ እርሰዎ ከላይ ሊያደርጉት እንደሞከሩት፥ ከላይ የጠቀሱትን የክቡርነታቸውን መጽሐፍ፥ በኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ሊቃውንት ጉባኤው ታይቶና በቅዱስ ሲኖዶሱ ጸድቆ የተሰጠ መልስ እንደሆነ አድርጎ በመቁጠር ሕዝብን ማምታታትና ማወናበድ ተገቢ አይደለም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ፥ እርሰዎም የቤተ ክርሰቲያኗ አንድ ካህን ሰለሆኑ፥ ይህ በተከታታይ የጻፉአቸው ሁለተ ጽሑፎች፡ ልክ በኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ሊቃውንት ጉባኤ ታይቶ በቅዱስ ሲኖዶሱ ጸድቆ በእርሰዎ አፈ ቀላጤነት መልሰ መሰጠቱ ነው ማለት ነውን???? አይመሰለኝም!!!!!

በመቀጠልም፥

*"ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክረስቲያን ጠይቀን መልሰ ብናጣ ወደ ግብጽ ቤተክርስቲያን ጥያቄያችንን አቅርበን አባ ሺኖዳ (የግብጽ ቤተክርሰቲያን መሪ) አጽድቀውልናል የሚለው አባባላቸው ጓደኛ ፍለጋ ቅልውጥ ሄዱ እንጂ ነገሩ እውነተ ሰላልሆነ በሕዝብ ዘንድ ትዝብት ላይ ከመውደቃቸው በሰተቀር ማንንም ማታለለ እንደማይችሉ ለሁሉም ግልጽ ነው።"*
ብለዋል።

መሪ-ጌታ፥ አሁንም በድጋሚ ይህን ከእውነት የራቀ ፈጠራዎን ከላይ ሰለመለስኩት አልፈዋለው ። ሆኖም ግን *"ጋደኛ ፍለጋ ወደ ግብፅ ቤተ ክርስቲያንና አባ ሸኑዳ ቅልውጥ ሄዱ"*

ብለው ያሉት አሳፋሪ ነገር፣ በእውነት ላዝንለዎት እንደሚገባ ነው ያደረገኝ። ምክንያቱም "...ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን...." የሚለውን ዋነኛና መሰረታዊ የሆነውን የሃይማኖታችንን መመርያ እንደው በዘልማድ ሲደግሙት ኖሩ እንጂ፣ እውነተኛ ትርጉሙ ቢገባዎት ኖሮ፣ እንዲህ ያለ ስሕተት ውስጥ አይወድቁም ነበር። የሚገርመውና የሚደንቀው ነገር፣ በጽሑፎዎ ላይ፡ በኩራትና በመመካት ለማሰረጃነት የጠቀሷቸው በሃይማኖተ አበው ላይ ያሉት ሁሉ ሊቃውንቶች ኢትዮጵያዊያኖች መሰሎዎት ነበርን?? ቅዱሴ ማርያሙንና ውዳሴ ማርያሙን የደረሱት ግብፃዊው አባ ሕርያቆስና ሶርያዊው አባ ኤፍሬም ኢትዮጵያዊያኖች መሰሎዎት ነበርን?? የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዋና ጠባቂ በመባል የሚታወቁት እነ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱሰ ቄርሎስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እና ቅዱስ ጎርጎርዮስ ኢትዮጵያዊያኖች መሰሎዎት ነበርን?? ከላይ እንዳልኩት አመለካከተዎ፣ ከመንፈሳዊነቱ ይልቅ ወደ ፖለቲካው ያጋደለና በሐሰት ላይ የተመሠረተ ሰለሆነ፡ ያው እንደ ዘመኑ ፖለቲካ ዘርና ድንበር ላይ አተኩሩ። የሚገርመው ነገር ደግሞ፣ የርሰዎን ሀሳብ የሚደግፍ መሰሎ ሲታየዎ፣ አሌክሳድርያዊው አባታችን ቅዱሰ ቄርሎስ ፣ቅዱስ አትናቴዎስ፣ታላቁ አባታችን ግብፃዊው አባ ሕርያቆስ ሲሉ ይቆዩና የርሰዎን ኑፋቄ የሚመታ ጭብጥ ማሰረጃ ሲቀርብበዎት ደግሞ፣ ያው እንደ ፖለቲካኛ መለሰ ብለው *"ጋደኛ ፍለጋ ወደ ግብፅ ቤተ ክርስቲያንና አባ ሽኑዳ ቅልውጥ ሄዱ"* በማለት"...ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድሰት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን...." ብለን እንደ አይን ብሌናችን የምንጠብቃትን አንዲቷን "ኦርቶዶክስ ተዋህዶ" ሃይማኖት በአለም ላይ ለማሰፋፋት ሌት ተቀን የሚጥሩትን የግብፅ ኦርቶዶክስ ቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ሽኑዳ ፫ኛን አጣጥለው ለመጻፍ መሞከረዎ የተሸከሙትን ክህነት ያልተረዱት መሆንዎን በግልጽ ያሳያል።

በመቀጠልም፣

*ይሁንና በሌላ መልኩ ደግሞ ለዚሁ ምእመናንም ሊታዘንላቸው የሚገባ ው። ሰለምን ? ቢባል በሣር ጎጆ ሆና እውትን ከምታስተምር ቤተ ክርስቲያን መጥተው አሜሪካ ፎቅ ላይ ሲቀመጡ የታቦር ተራራ ሆኖላቸው አዲስ ምስጢር የተገለጸላቸው ቢመስላቸውም ቅሉ እንኳንስ ይኼንን ረቂቅ ምስጢር ይቅርና ሰለራሳቸው ፊደል አገባብ እንኳ አሰተካክሉ የሚያሰረዳቸው በዕውቀት የበሰለ ሰው በመካከላቸው ከለመኖሩና ከገል ስህተት ገና ያልተላቀቁ ለመሆናቸው የተሳ የደብራቸው ማንተም በርሱ ላይ ታማኝ ምሥክር ሆኖባቸዋል።* ብለዋል።

መሪ-ጌታ፣ ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ ማለት እንዲህ ነው። እርሰዎ ዋናውን ቁም ነገር፣ ነገረ ሃይማኖቱን አፈር ድሜ አብልተውት፣ የኛን የሆሐያት ግድፈት ቁም ነገር አድርገው መክሰሰዎ ያሳዝናል። ሐዋርያት ወንጌልን ለመሰበክ ከአገር አገር ተንከራተቱ እንጂ፣ እንደርሰዎ ወደ ለንደን ተሰደው ሰለፊደል አጋባብ አልተጨነቁም። አዎ እርግጥ ነው፣ ፊደልን በሚገባ ማወቅና መማር ተገቢ ነው። እኔም ብሆን የምደግፈውና ማናችንም ብንሆን ትኩረት ልንሰጠው ይገባል። ሆኖም ግን፣ ወደ ሊቃውንቱ መጽሐፍትና ወደ አንድምታው ለመግባት እንዲረዳ የተቆጠረን ፊደል ብቻ ይዞ፣ ወርቁን አፈር ላይ ጥሎ ሰሙ ላይ ማተኮር፣ የፊደል እንጂ የነገረ ሃይማኖት መምህር አያደርገም። ሲሆን ሲሆን፡ ያዩትን የፊደላት ገድፈት አቃንተው ለወደፊቱ እንዲታረም በማሳሰብ፡ ባስተላለፍነው ሐሳብ ላይ ማተኮር ሲገባዎ፣ ፊደልን (ቋንቋን) ሃይማኖት አድርገው በመውሰድዎ፣" *ፊደል ይገላል መንፈስ ግን ሕይወት ይሰጣል" ፪ኛ ቆሮ. ፫፣፮* የሚለውን መሪ ቃል ከቶ እንዳልተገነዘቡት በግልጥ ያሳያል። ይህም ሳይበቃ፣ *"ፊደል አገባብ እንኳ አስተካክሉ የሚያሰረዳቸው በዕውቀት የበሰለ ሰው በመካከላቸው ካለመኖሩ..."* ብለው በአሽሙር አነጋገር ገደም አድርገው አባታችን ቀሲስ አሰተርአየን ለመዝለፍ መሞከረዎን፣ "ስደት ለወሬ ያመቻል" ከማለት በቀር፡ የሰው ልክና እውቀት የሚፈተንበት ጊዜ እስኪመጣ በትዕግስት እናልፈዋለን።

በመቀጠልም፣

*"እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ሲፈጥረው ክፉውንና በጎውን መምረጥ የሚችል አእምሮ ሰጥቶ በጻት ሰለፈጠረው ግብጻዊያንም የወደዱትን ማምለክና ማመን ይችላሉ ገር ግን ትናንት እንደ*

*ነበሩት ዛሬም በሃይማኖት ጣልቃ ገቢዎች ኢትዮጵያዊያንን አይከፋፍሉም። በዚያውም ላይ ምንም እንኳ ወልድ ዋህድ በሚለው መሠረተ እምነት አንድ ብንሆንም (ከጥንታውያን አባቶቻቸው ከነ አትናቴዎስ፥ ቄርሎስ...) ተለይተው የአሁኖቹ የሃይማኖት ተዋካዮች ከሚፈላሰፉት በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ላንስማማ እንችላለን። ለምሳሌ ያህል በምሥጢረ ሥላሴ ላይ አንስማማም፥ ይሄንንም ወደፊት እንደአሰፈላጊነቱ ሊቀርብ ይፅላል።....* "ብለዋል።

መሪ-ጌታ፥

- *ግብጻውያንም የወደዱትን ማምለክና ማመን ይቻላሉ ነገር ግን ትናንት እንደ ነበሩት ዛሬም ነገም በሃይማኖት ጣልቃ ገቢዎች ኢትዮጵያውያንነ አይከፋፍሉም...* "

ብለው ያሉት: እንኳን በ መሪ-ጌታ ማዕረግ ያለ ካህን ይቅርና፥ ከሰንበት ተማሪ የማይጠበቅ ትልቅ ሰህተት ነው። ለመሆኑ፥ ማን በማን ሃይማኖት ነው ጣልቃ የገባው። እስከ ዛሬ ፺ አመት ድረሰ ለ ፲፮፻ አመት ያህል ማርቆሰ አባታችን እስክንድርያ እናታችን ብለው በፍጹም ትህትና ነገረ ሃይማኖቱን ሰይበክሉ ሳይበርዙ ባቆዩት አባቶቻችን እግር፥ ዛሬ እንደርሰዎ ባሉት፥ ሃይማኖት፥ ዘርና ድንበር የሌለውና የማይወሰነው መሆኑን ባልተረዱና ባልተገነዘቡ ሰዎች መተካታቸው በጣም ያሳዝናል። ጠብቀው ሊያሰጠብቁት ምለው የተቀበሉት ክህነት፥ ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የ"ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን" ሃይማኖት ነው እንጂ፥ ኢትዮጵያ ለራሷ በራሷ የፈጠረችው የግሏ ሃይማኖት ኗራት አልነበረም። በዚህ ላይ ደግሞ፥ መንፋሳዊ አባትነተዎት፥ በዘርና በቆዳ ለሚመሰለዎት ኢትዮጵያዊያን በቻ ሳይሆን፥ ለመላው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞችም ነበር። ይህም ማለት፥ ለግብፃዊያኑም፥ ለሶርያዊያኑም፥ ለአርመኑም፥ ለህንዱና ለኤርትርያዊያኑ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች በሙሉ ሲሆን፥ እርሰዎ ግን፥የተሸከሙትን ክህነት ባለመረዳት "*ግብጻውያንም የወደዱትን ማምለክና ማመን ይቻላሉ*" በማለት፥ ግብጻዊያኑ ታሳስተው ቢሆን አስተምረው ሊያቃኗቸው፥ ተበድለው ቢሆን ሊቆረቆሩላቸውና ሊደርሱላቸው ሲገባ: እንደ እንጀራ ልጅ በመቁጠር: የፈለጉትን ይሁኑ ማለተዎ አሳፋሪና አሳዛኝ ከመሆን ብቻ አለፎ ቤተ ክርሰቲያናችንንም ያሰነቅፉታል። መንፈሳዊና ቀና ልቦና ቢኖረዎ፥ በደብራችን የተከሰተውን ችግር አሰመልክተን ለጠየቅነው ጥያቄ: የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ቅዱስ ሲኖዶስ መልሰ ባለመሰጠቱ፥ ባለባቸው ሐዋርያዊ ግዴታ፥ ነገረ ሃይማኖቱን በተመለከተ የግ.ኦ. ቤተ ክርሰቲያንን በጠየቅነው መሰረት፥

- ቤተክርስቲያኗ መልስ ከመሰጠቷ በፊት፥ በቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ ሽኑዳ ፫ኛ በተሰጠ ትእዛዝ፥ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ማንነታችንን ለማረጋገጥና ያለንበትንም ሁኔታ ለማጥናት በቅድሚያ ደብራችን ድረሰ ተልከው ጎበኝተውን ካህናችንን ቀሲሰ አሰተርአየን አነጋገረው ከኛም ለተጠየቁት ጥያቄዎቸ ተገቢውን መልሰ ሰጥተው እውነተኛ የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር አማኞች መሆናችንን ካረጋገጡ በኋላ ባርከውን አጽናንተውን ወደ ግብፅ ተመለሱ።

- ከዚያም ቀጥሎ፥ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ሰለኛ ማንነትና ሰላለንበት ሁኔታ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ካሳወቁ በኋላ ከቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ ሽኑዳ ፫ኛ በተሰጠ ትእዛዝ፥ ለደብራችን መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያሰፈልጉንን ከእጣን አንሰቶ እሰከ መንበር ድረሰ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ወደ ካንሳስ ሲመጡ ይዘው መጥተው እንዲሰጡን ተደረገ። ይህ ብቻ ሳይሆን ባለንበት በካንሳሰ ከተማ እንደዛሬው ሕዝቡ በዚሁ በነገረ ሐይማኖቱ ምክንያት ተከፋፍሎ ሁለት የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ከመኖሩ በፊት ሁላችንም በአነድነት ስርአተ አምልካችንን ሰናካሂድበት ለነበረው ቅዱስ ማርቆስ የግ.ኦ. ቤተ ክርሰቲያን ለሚያሰፈልገን ነገር በተቻላቸው እንዲረዱን፥ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ትዛዝ ሰጥተዋል።

- በመጨረሻም ያው ለህዝብ በአደባባይ እንዳሳወቅነው በ August 15, 2009 ካንሳስ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ የግ.ኦ. ቤተ ክርሰቲያን ለጥያቄያችን መልሰ ተሰጠን።

አንባቢ ሆይ፥ እንግዲህ ከላይ አጠር ባለ መንገድ ጥያቄያችንን ለግ.ኦ. ቤተ ክርሰቲያን ካቀረብንበት ጊዜ አንስቶ መልስ እሳካገኝንበት ወቅት፥ የግ.ኦ. ቤተ ክርሰቲያን ሰለኛ ማንነት፥ ሰለደብራችንና ሰለነገረ ሃይማኖቱ ምን ያህል ተጠንቅቀው ያለባቸውን ሐዋርያዊ ግዴታ: ዘር፥ ጎሳና

ድንበረ ሳይወሰናቸው በሚገባ መወጣታቸውን ማንም ሰለ ቤተ ክርሰቲያኔና ሃይማኖቴ ይገደኛል ለሚል ሰው ግልጽ ነው። የሚያሳዝነውና የሚገርማው ግን፥ እንዲህ ያለውን የተባረከ ሰራ አመሰግኖ ከድርጊቱ እንደመማር ይልቅ፥ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ፥ ይህን የተቀደሰ መንፈሳዊ አገልግሎት፥ ጠምዝዘው፥ ወደ ምድራዊ ፖለቲካ በመቀየር፡ የሕዝብን ሰሜት ለመኮርኮር ያደረጉት ደካማ ሙከራ ከሌላው ነገር ሁሉ ይልቅ ሰለሳቸው ማንነት በሰፊው ይናገራል።

ከዚህ ሁሉ ግን በጣም የሚያሳዝነውና፥ ማንኛውም የኦርቶዶክሰ ተዋህዶ አማኝ የሆነ ሁሉ፥ ሊያሰብበትና ሊያጤነው የሚገባ ነገረ ቢኖር፥ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ፥ በአሁን ሰአት ያለችው የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን "ምስጢረ ሥላሴን" በተመለከተ ያላት አቋምና እምነት ከኢ.ኦ.ተ ቤ/ክር እና ከአባቶቻችን ከነ ቅዱስ አትናቴዎሰና ቅዱስ ቄርሎስ የተለየ ነው በማለት ""...ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድሰት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን...." የሚለውን የአንድነታችንንና የእምነት መሰረታችን የሆነውን የኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ሰንሰለት፥ አለአግባብ ሊቆራርጡትና ሊያፈርሱት መሞከራቸው ነው። ከዚህ እንደምንረዳው እኒህ መሪ-ጌታ፥ የያዙትን የተሳሳተ (Immaculate Conception) የሮማ ካቶሊክ እምነት ከቤተ ክርስቲያናችን ታርሞ እንዳይወጣ ምንም ከማድረገና ከመናገረ እነደማይመለሱ ነው የሚያሳየን። በተጨማሪም "የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሥላሴን ካደች" በማለት፥ ይህን ከእውነት የራቀ ፈጠራቸውን ለማሳመን አሰፈላጊ ከሆነ ማሰረጃ እንደሚያቀርቡ ቃል ሰለገቡ፥ በእናንተ በአንባቢዎች ሰም፡ በአዳባባይ በድሕረ ገፆች ላይ እንዲያወጡት በትህትና እጠይቃቸዋለው። በተረፈ "ምስጢረ ሥላሴን" በተመለከተ የግ.ኦ. ቤተ ክርሰቲያንን እምነትና ትምህርት ለመረዳት ለሚፈልግ፥ከስር ያለውን ድሕረ-ገጽ ይመልከቱና ይፍረዱ http://www.copticchurch.net/topics/theology/The_Meaning_of_the_Holy_Trinity_fr_abraam_sleman.pdf

## በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ይመራ የነበረው የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር የሊቃውንት ጉባኤ የወሰነው ውሳኔ ያስከተለው የሃይማኖት ቀውስ

ከዚህ በመቀጠል፥ ይህ ባለፉት ፳ አመታት ውሰጥ ቤተ ክርሰቲያናችንን እንደ አሸን የወረራት ይህ የተሳሳተ የሮማ ካቶሊክ እምነት፥ በምን ምክንያት እንዲህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊሰፋፋና፥ ከወጣት የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪ አንስቶ እስከ ቤተ ክህነቱ ድረስ ባሉ ካህናት ያለምንም እርማትና ግንዛቤ እየተጻፈ ታትሞ ሊበተን ቻለ የሚለው ዋና ጥያቄ ሊታይና ሊገመገም ይገባዋል። ይህን ያልኩበት ዋነኛ ምክንያት፥ እስከ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ድረሰ፥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሰ ተዋሕዶ ቤተ ክርሰቲያን ቅዱስ ሲኖዶስም ሆነ በሊቃውንት ጉባኤው፥ እመቤታችንን በተመለከተ ቤተ ክርሰቲያኗ ታምነውና ታሰተምረው የነበረው እምነት፥ በቅርቡ በብፁዐን አባቶች ጸድቆ በቅዱስ ፓትርያርኩ በአቡነ ጳውሎስ መልካም ፈቃድ በ ፲፱፻፹፰ ዓ.ም "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት" በሚል መጽሐፍ በአማርኛ በተጻፈው ክፍል ላይ በገጽ ፵፱ እዲሁም ደግሞ በእንግሊዘኛ በተጻፈው ክፍል ደግሞ በገጽ ፶፩ ላይ እንደሚከተለው ተብሎ ተጽፎ ከተቀመጠው ጋር ፈጽሞ አይመሳሰልም። ይህም ጽሑፍ የሚለው እንደሚከተለው ነው፥

"አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች እመቤታችን ድንግል ማርያም ከአዳም ዘር የተላለፈ <u>ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) ያላገኛት</u>: መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ገና ከመወለዷ አሰቀድሞ በአምላክ ኅሊና ታስባ ትኖር የነበረች: በሰው ልማድና ጠባይ ከሚደርሰው ሥጋዊ አሳብና ፈቃድ ሁሉ የተጠበቀች: ከተለዩ የተለየች ንጽሕት ቅድስተ ቅዱሳን ናት መሓል ፬፥፯"

"Our Lady, the Virgin Mary, who conceived and gave birth to Jesus Christ in virginity <u>is free from the original sin derived from the descendants of Adam,</u> clean from any sin of the flesh or soul; embedded in the conscience of God before the time of her birth, free and protected from human desires and frailities, and the choicese from among teh chosen. Such is the Virgin Mary - Pure and Holy and Holies. (Song 4:7) "

**ማሳሰቢያ!!!!**

ይህ ከላይ በአማርኛ፥ "እመቤታችን ድንግል ማርያም <u>ከአዳም ዘር የተላለፈ ኃጢአት (ጥንተ</u> አብሶ) ያላገኛ<u>ት</u>:" የሚለው ሐረግ: በትክክሉ ወደ እንግሊዘኛ ሲተረጎም መሆን የነበረበት፥ እመቤታችን "...was preserved (exempt) from original sin." ሲሆን፥ ተርጓሚው ግን: ሆን ብሎ ለእንግሊዘኛ ተናጋሪ አንባቢዎች እንዲያሻማ አድርጎ፥ እመቤታችን፥ " <u>is free from the original sin derived from the descendants of Adam,"</u> ብሎታል። ይኸም አባባል እመቤታችን "ጥንተ አብሶ" አልደረሰባትም ወይንም አልተላለፈባትም ማለት ሳይሆን: እመቤታችን "ከጥንተ አብሶ" ንጽህናዋ፥ ገና ስትፀነስ ጀምሮ ይሁን፥ ከብስራት በኋላ ይሁን ወይንም መቼ እንደሆነ ግልጽ አድርጎ አይገልጽም። ይህም በመሆኑ፥ ኦርቶዶክሳዊያናት በይበልጥም አኀት አብያተ ክርሰቲያናት: የእንግሊዘኛውን ጽሑፍ ብቻ አይተው: የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክ የሮማ ካቶሊኩን ኑፋቄ (Immaculate Conception) ተቀብላለች ብለው አይጠረጥሩም አይገምቱምም።

ለዚህም በዋናነት ለማስረጃ የማቀርበው፥ ይህ የነገረ ሃይማኖት ጉዳይ እንደተነሳ: ቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ ጳውሎስ ለዶክትሬት ዲግሪያቸው ፍጻሜ ሲሉ በጻፉትን ጥናታዊ ጽሑፍ (Dissertation) ላይ፥ እመቤታችን ከሰው ዘረ በመኾኗ: የአዳም ውርስ ኃጢአት (Original Sin) ነበረባት፥ በተቃራኒው ግን: የሮማ ካቶሊክ ቤ/ክር ብቻ ናት የለባትም የመትለው ብለው የጻፉትን ጠቅሼ፥ ይኼው ዛሬ የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ፓትርያርክ ሲሆኑ የሮማ ካቶሊኩን (Immaculate Conception) አጽድቀው ተቀበሉ በማለት ከላይ የጠቀሰኩትን ጽሑፍ ኮፒ አያይዤ ለአሰተማርያቸው

ለ Dr. Karlfried Froehlich ወደ Princeton Theological Seminary በመላክ ላቀረብኩት ስሞታ: መምህራቸው ከሰጡት መልስ መካከል አንደኛው የሰጡኝ መልስ ከላይ ላስረዳ የሞከርኩትን ነው። የተነጋገርነውን ለማየት፥ ወደ ኢትዮጵያ ለቅዱስ ሲኖዶሱ የተላከው ሰነድ ላይ ( www.medhanialemeotcks.org) መመልከት ይቻላል።

ሆኖም ግን: ከላይ የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር በአማርኛ ጽፋ በይፋ ያወጀችው: ከሮማ ካቶሊክ ቤ/ክር (Immaculate Conception) ትርጉምና እምነት ጋር አንድ ለመሆኑ ከሰር ተመልከት።

**<u>Immaculate Conception</u>** - In the Constitution Ineffabilis Deus of 8 December, 1854, Pius IX pronounced and defined that the Blessed Virgin Mary 'in the first instance of her conception, by a singular privilege and grace granted by God, in view of the merits of Jesus Christ, the Saviour of the human race, was preserved exempt from all stain of original sin. (From Catholic Encyclopedia)

እንግዲህ ከላይ በማሰረጃ ላሳይ እንደሞከርኩት: ይህ አዲስ ሃይማኖት በቤተ ክርስቲያናችን በይፋ መነገር የጀመረው በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም የሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምሕርት ቤት የብሉያትና የሐዲሳት ትርጓሜ ተማሪዎች ስማቸው ከስር በተሰረዘሩት የቤተክርስቲያኗ መምህርና አባት ላይ፥ ሃይማኖታችንን አፋልሳዋል ሲሉ ለቅዱስ ሲኖዶሱ በሳሙት አቤቱታ (ክስ): የተናሳ፥ በወቅቱ በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ሰብሳቢነት ተሰይሞ ጉዳዩን የተመለከተው የሊቃውንት ጉባኤ: የደረሰበትን ውጤት ለቅዱሰ ሲኖዶሱ ባሰተላለፈው መግለጫ መሰረት ለመጀመርያ ጊዜ ቤተክርሰቲያናችን: አኀት አብያተክርሰቲያናትና መላው ኦርቶዶክስ ነቅፎ የጣለውን፥ ይህን በ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ December, 1854 በ Pius IX ጸድቆ (Immaculate Conception) በመባል የሚታወቀውን የሮማ ካቶሊክ እምነት በይፋ አወጀች። ከላይ እንደገለጽኩት: በተማሪዎቹ ከቀረቡት ፫ ክሶች መካከል አንደኛው፥

"ቅድስት ድንግል እመቤታችን በንጽሐ ሥጋ በንጽሐ ነፍስ በንጽሐ ሕሊና በአምላክ ጥበብ ስትጠበቅ የነበረች የአዳም በደል ያልነካት ንጽሕት መሆንዋን ቢቃወሙ በእመቤታችን ተሰምቶ የማይታወቀውን የኑፋቄ ትምህርት በማስተማር ጥንተ አብሶ አለባት በማለት መጽሐፍ ጽፈዋል" የሚል ነው።

ተከሳሾቹም፥
፩ኛ. ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ (በአሁን ሰአት በሰሜን አሜሪካ በሰደት ይገኛሉ)
፪ኛ. ክቡር መጋቤ ብሉይ ስይፈ ሥላሴ (በአሁን ሰአት የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክር የሊቃውንት ጉባኤ አባል ናቸው)
፫ኛ. አቶ አሰራት ገብረ ማርያም (ሰለ ክቡርነታቸው በአሁን ሰአት ምንነት የማውቀው የለም)

ከዚህ በመነሳት፥ ይህ የተሳሳተ ሃይማኖት ከላይ እንደገለጽኩት እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረሰ ዋና መሰረቱና ምክንያቱ፥ ይህ በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ሰብሳቢነት ይመራ የነበረው የሊቃውንት ጉባኤ፥ የሚከተለውን አስተያየት ለቅዱሰ ሲኖዶሰ በማሰተላለፉ ነው፥

" እመቤታችን ጥንተ አብሶ ነበረባት ወይም አለባት የነፃች ከብሥራት በኋላ ነው እሷ ሰው ናት ከሰማይ አልወረደችም እያሉ መናገር ከዚያም አልፎ መጻፍ መሳሳት ብቻ ሳይሆን በደል፥ ድፍረት፥ ክህደትና የማይሰረይ ኀጥያት ነው"።

ለዚህ ውሳኔያቸውን መሰረት አድርገው የሰጡት ዋና ዋና ማሰረጃዎች፥

- "ወዳጄ ሆይ፥ ሁለንተናሽ ውብ ነው፥ ነውርም የለብሽም።" (መሓልይ ፬፥፯)
- ፍጽምት ዘአልባ ርሰሐት ዘበ እንቲአሃ ተሥእረ ዘቀዳሚ መርገም ንጽሕት ድንግል ወላዲተ

አምላክ ማእምንት ብለው አመስግነዋታል።

- ይኢቲ ተአቢ እምኪሩቤል ወትፈደፍድ እምሱራፌል ብሎ አንጺሖ ሥጋሃ ያላበትን ምክንያት ሲየስረዳ መናፍቃንን አሳፍሯቸዋል (ቅዱስ ያሬድ)

በአንጻሩ ደግሞ፥ ቅዱሰ ያሬድ አንጽሖ ሥጋሃ ቀዲሰ ኪያሃ ያለው፥ የእመቤታችንን ሥጋ አነጻ ለማለት አይደለም ሲሉ የሰጡት ንጽጽራዊ ማብራሪያ እንደሚከተለው ነው፥

አንጺሖ የሚለው ቃል ጥንት በደል እንደነበረባት የሚያሳይ አይደለም ብለው ምክንያቱን ሲሰጡ፥

- አምኖ ለሚቀበለው የሚያሳየው ነገር ቢኖር፥ እሷን ለእናትነት አካልዋን ለተዋሕዶ መርጦ ማክበሩን ነው።
- ንጹህ የሚለው ቃል ሁሉ፥ ርስሐት ይቀድመዋል ማለት አይደለም። ቃለ እግዚአብሔር ቃለ ንጹሕ ይላል። የሚያሳየው ንጹሕ ባሕርይነቱን ነው።
- መላእክት ንጹሐን ይባላሉ በደል ኑሮባቸው የተሰረየላቸው ማለት አይደለም በተፈጥሮ ንጹሐን ናቸው ማለት ነው።
- ንጹሕ ቁርባን ይላል ነውር የሌለበት ማለት ነው።

ይህ ምሥጢረ ሰጋዌን የሚያናጋ የነገረ ሃይማኖትን ጉዳይ፥ ከላይ እንደገለጽኩት ሥጋዋን አንጽቶ (አንጽሖ ሥጋሃ) የሚለውን የቅዱስ ያሬድን ቀጥተኛ ቃል፥ ንጹሕ ማለት ነው ብሎ በማን አለብኝነትና ሰውን እንደ ጅልና መአይም አድርጎ በመቁጠር፥ የማይገናኙ ምሳሌዎችን በመደርደር፥ እንዲህ በሚያሳዝንና በሚያሳፍር መልኩ የሮማ ካቶሊክ ፈጠራ የሆነው ኑፋቄ ጸደቀ። ይህ ብቻ ሳይሆን፥ አሁንም በድጋሚ" "ወዳጄ ሆይ፥ ሁለንተናሽ ውብ ነው፥ <u>ነውርም</u> የለብሽም።" (መሓል ፬፥፯) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በመጥቀስ፥ ነውር ማለት (የአዳም መርገም፥ ቁረኛነት ወይንም ጥንተ አበሶ) ነው ብሎ አሁንም በድጋሚ በማን አለብኝነትና በጉልበት ተርጉሞ ሃይማኖትን ያክል ነገር ማፋለስ በጣም ያሳዝናል። ምክንያቱም፥ ነውር የሚለው ቃል በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ተጠቅሷል። ሆኖም ግን፥ ይህንኑ ቃል፥ የሊቃውንት ጉባኤው አላግባብ አጣሞ በተረጎመበት መንገድ ብናየው፥ ብዙ ነገሮችን ያፋልሳሉ። ምክንያቱም እንደሚከተለው ነው፥

- ቅዱሰ ጳውሎሰ "ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን። በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን።" ብሏል (ኤፌ. ፩፥፬-፭)
- እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች፥ በሁለት ቃል የማይናገሩ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጁ፥ነውረኛ ረብ የማይወዱ፥ በንጹሕ ሕሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል።(፩ኛ. ጢሞ. ፫፥ ፰-፱) ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎሰ ተናግሯል
- ንጉሡም ነውር የሌለባቸውንና መልከ መልካሞቹን፥ በጥበብ ሁሉ የሚያስተውሉትን እውቀትም የሞላባቸውን ብልሃተኞችና አስተዋዮች የሆኑትን፥ በንጉሡም ቤት መቆም የሚችሉትን ብላቴኖች ከእስራኤል ልጆች ከነገሥታቱና ከመሳፍንቱ ዘር ያመጣ ዘንድ የከለዳውያንንም ትምህርትና ቋንቋ ያስተምሩአቸው ዘንድ ለጃንደረቦች አለቃ ለአስፋኔዝ ነገረ። (ዳን. ፩፥፬)

እንግዲህ ከላይ እንደምናየው በሊቃውንት ጉባኤው አተረጓጎም ከሄድን፥
፩ኛ. ቅዱስ ጳውሎስ ነውር የሌለን ሲል የአዳም የውርስ ኀጥያት ጥንተ አብሶ አልነበረባቸውም ማለት ነውን?? ፈጽሞ አይደለም።

፪ኛ. አላቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ባሳተሙት "መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት" (ገጽ ፯፻፴፫) ላይ "ነውር" የሚለው ቃል ትረጉሙ፥ እጸጽ፣ ገመና፣ነውረኛነት፣ የመልክ፥ የሕዋስ፥ የግብር ሲሆን በተመሳሳይ ደግሞ "ምግቴ" ማለት ሲሆን ይህም ማለት(ገጽ ፭፻፺፰) : ሕጸጽ፥ ሕጹጽነት፥ ነውረ ሰጋ ማለትም : የሕዋሳት መጉደል ወይም፥ አለመሰተካከለ፥ ዐንካሳ፥ ጠንባሳ፥ ወንካራ፥ ሸውራራ፥ ደፍጣጣ፥ ገጣጣ፥ ድንክ፥ ጎባጣ የመሰለው ኹሉ ብለው ተንትነውታል። ታዲያ እንዲህ የሚለውን ትርጉም

አጣሞና ጠምዝዞ ነውር ማለት" ጥንተ አብሶ" ነው ማለት ተገቢ አይደለም።

፫ኛ. ሌላው የሚገርመውና የሚደንቀው ነገረ፥ ይህ ብቻ ሳይሆን፥ ይህንን ኑፋቄ የፈጠረችው እራሷ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንኳ: ፈጠራዋን የሚደግፍላት ማሰረጃ በመጽሐፍ ቅዱሰ ላይ እንደማይገኝና: ይህ በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ የሚመራው የሊቃውንት ጉባኤ: እንደ ዋነኛ ማሰረጃ አድርጎ ያቀረበውን *"ወዳጄ ሆይ፥ ሁለንተናሽ ውብ ነው፥ ነውርም የለብሽም።" (መሓል ፬፥፯)* የሚለውን ጥቅስ እንኳን: ለሃይማኖቱ ተጨባጭ ማሰረጃ ሆኖ መቅረብ እንደማይችል በማመን ለማሰረጃነት እንዳልተጠቀሙበት በግልጽ አሰቀምጠውታል። ከዚህ በመቀጠል የሮማ ካቶሊክ ቤ/ክር በግልጽ ያስቀመጠችውን ዝርዝሩን ከሰር ይመልከቱ። ዝርዝሩም የተገኘው፥
( http://www.newadvent.org/cathen/ )

## Proof from Scripture
## Genesis 3:15

No direct or categorical and stringent proof of the dogma can be brought forward from Scripture. But the first scriptural passage which contains the promise of the redemption, mentions also the Mother of the Redeemer.

## Other texts

From the texts Proverbs 8 and Ecclesiasticus 24 (which exalt the Wisdom of God and which in the liturgy are applied to Mary, the most beautiful work of God's Wisdom), or from the ***Canticle of Canticles (4:7, "Thou art all fair, O my love, and there is not a spot in thee")***, no theological conclusion can be drawn. These passages, applied to the Mother of God, may be readily understood by those who know the privilege of Mary, but do not avail to prove the doctrine dogmatically, and are therefore omitted from the Constitution "Ineffabilis Deus". For the theologian it is a matter of conscience not to take an extreme position by applying to a creature texts which might imply the prerogatives of God.

እንግዲህ እኒህ እና ሌሎችም በቂ ታጨባጭ ማሰረጃዎች እያሉ: ለምን በወቅቱ የተከሰሱት ሰዎችም ሆነ የቅዱስ ሲኖዶሱ አባላት ጉዳዩን አልተቃወሙም የሚል ተገቢ ጥያቄን በሕዝበ ክርስቲያኑ አይምሮ ላይ ማሰነሳቱ አይቀርም። ይህንንም በተመለከተ፥ በወቅቱ ቅዱስ ሲኖዶሱ፥ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅን በአካል ቀርበው ለተከሰሱበት መልሰ እንዲሰጡ ደጋግሞ መጠየቁንና: ብፁዕነታቸውም በወቅቱ ከአገር ወጭ በሰሜን አሜሪካ ሰለነበሩና በወቅቱ በአካል ቀርበው መልሰ ባለማሰጠታቸው ቅዱሰ ሲኖዶሱ ከክህነታቸው እንዳገዳቸው ጳጉሜን ፪, ፲፱፻፹፬ ባወጣው ጽሑፉ አሰታውቃል።(ሙሉ ሰነዱን በ 2005 ለቅዱስ ሲኖዶስ በተላከው PDF ላይ ገጽ 121-133 (www.medhanialemeotcks.org ) ተመልከት።

ከጽሑፉም እንደምንረዳው፥ ቅዱስ ሲኖዶሱ፥ የሊቃውንት ጉባኤው አጥንቶ ያቀረበውን መግላጫ ሙሉ በሙሉ እንደተቀበለው ያሰረዳል፥ በሌላ በኩል ግን ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በሰደት ባሉበት በሰሜን አሜሪካ ይህንን የእመቤታችንን ጉዳይ አስመልክቶ በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ባለ የራድዮ ዝግጅት ለተጠየቁት ጥያቄ በሰጡት መልስ: እሳቸው፥ እመቤታችን ጥንተ አብሶ አላባት የሚል መጽሐፍ ፈጽሞ እንዳልጻፉ አሰተባብለዋል። ሆኖም ግን ይህ የነገረ ሃይማኖቱ ጉዳይ እሳቸውን ብቻ ሳይሆን መላው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አባቶችን፥ የሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ: በአሁኑ ወቅት ብፁዕነታቸው በአባትነታቸው ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ምን ይላሉ??? እሳቸው በአሁን ሰአት በሕይወት ሰላሉ፥ ለጠያቂም ለሳቸውም በግልጽ የመናገር እድሉ ክፍት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፥ በወቅቱ ተከሰው የነበሩት ክቡር መጋቤ ብሉይ ስይፈ ሥላሴና አቶ አሥራት ገብረ ማርያምን በተመለከተ፥ ጉዳያቸው በምን እንደተዘጋ ከላይ የጠቀሰቁት የቅዱሰ ሲኖዶሱ መግላጫ ላይ ስላልተገለጸና፥ ሌላም በነሱ ላይ የተወሰነውን በሚመለከት ተጨባጭ ማሰረጃ

ስለሌለኝ ይሄ ነው ለማለት አልችልም። ሆኖም ግን: አንድ ሁላችንም የምናውቀው ነገር ቢኖር፥ እኒህ መጽሐፍትን አደላድለው ያወቁና የተማሩ ክቡር መጋቤ ብሉይ ስይፈ ሥላሴ፥ በአሁኑ ወቅት የኢ.ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ አባል መሆናቸውን ነው። እንግዲህ በወቅቱ በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ሰብሳቢነት ተሰይሞ፥ ጉዳዩን የተመለከተው የሊቃውንት ጉባኤ: የደረሰበትን ውጤት ለቅዱስ ሲኖዶሱ ባስተላለፈው መግለጫ መሰረት፥ በክቡር መጋቤ ብሉይ ስይፈ ሥላሴ  የተጻፈውን መጽሐፍ በመንቀፍ፥ እመቤታችንን በተመለከተ ጥንተ አብሶ ነበረባት የሚለውን መጽሐፋቸውን ከኢ.ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ውጭ ነው ብሎ ለቅዱስ ሲኖዶሱ አሰቸካይ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስቧል። ከነዚህ ተጨባጭ ሁኔታዎች በመነሳት ሊደረሰበት የሚቻለው አሰተያየት፥

- ክቡር መጋቤ ብሉይ ስይፈ ሥላሴ በወቅቱ በጻፉት መጽሐፋቸው ላይ: በትክክል ያሰፈሩትን እውነተኛ የኦርቶዶክስ እምነትና ትምህርት ለቀውና ቀይረው፥ አዎ ታሳስቻለው ብለው ሊደርስባቸው ከሚችለውን ሁኔታ አምልጠዋል ማለት ብቻ ነው።

ይህ ደግሞ በካህንነታቸው፥ ጠብቀው ሊያስጠብቁት፥ አሰፈላጊም ከሆነ: እስከ ሕይወት መስዋትነተ ሊከፍሉበት የሚገባ: ቃል ኪዳን ገብተው የተቀበሉት የሃይማኖት ጉዳይ፥ አንተ አብያተ ክርሰትያናትና መላው ኦርቶዶክሶች በሚነቅፉት በሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ በዚህ አይነት ሁኔታ መተካቱ በጣም ያሳዝናል። አዎ፥ "ያልተያዘ ግልግል ያውቃል እንዲሉ"  በሳቸውም ላይ መፍረዱ ለኔም ሆነ ለብዙዎቻጭን ቀላል ነው። ነገር ግን በወቅቱ በቤተ ክርስቲያኗ ዙርያ የነበረውንም ሁኔታ አብሮ መመልከቱ ሰፋ ያለ ግንዛቤና ለወደፊቱም ትምህርት ለሁላቸንም ይሰጣል ብየ አስባለው። ይሄውም፥

፩ኛ. በወቅቱ የቤተ ክርስቲያኗ ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ከቦታቸው ተነስተው መንበረ ፓትርያርኩ ያለ ፓትርያርክ ባዶውን ነበር። ይህ ወቅት ብፁዐን አባቶች እኔ እሾም እኔ እሾም እያሉ እርስ በርሳቸው በአይነ ቁራኛ የሚተያዩበትና፥ በወቅቱ በቤተ ክርስቲያኗና አገሪቱን ለመምራት ስልጣን ላይ በወጣው የኢሕአዴግ መንግስት መካከል ያለው ግንኙነት ግልጽ ባለመሆኑ በቤተ ክህነቱ አካባቢ መረጋጋት አልነበረም። ሰለሆነም "ጥንተ አብሶን" በሚመለከት የነገረ ሃይማኖቱ ጉዳይ ተገቢውን ጥናትና ጥንቃቄ አለማገኘቱን በግልጽ ይታያል።

፪ኛ. በሌላ በኩል ደግሞ፥ እራሱንና ቤተሰቡን ከቤተ ክህነተ በሚያገኛት አነሰተኛ ደሞዝ በንጹህ ልብ አምላኩንና ምዕመናኑን የሚያገለግል ሰው (ካህን): እውነተኛይቱን ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት ጽፎ በማሰተማሩ: በግፍ ተወግዞ ቢባረር: በሌላ የሰራ ሞያ ተሰማርቶ ቤተሰቦቹን ለማሰተዳደር አመቺ ሁኔታ በሌለበት አገር: ሃይማኖቱ የሚጠብቅበትን መሰዋትነት ለመክፈል ብቁ ሁኖ በመገኘት ከራሱ አልፎ ለሁሉም ነገር የሱን እጅ የሚጠብቁትን ቤተሰቦቹን ጭምር አሳልፎ ለችግር ለመዳረግ እጅግ በጣም ጠንካራ መንፈሳዊ ሕይወት ያለው ሰውን ይጠይቃል። ይህን ለማለት የቻልኩበት ምክንያት: እዚህ በሰሜን አሜሪካ የሰው መብትና ሕግ በሚጠበቅበት አገር: ማንም ሰው ካህንንም ጭምር: ያሻውን ሰራ በአቅሙና በችሎታው መጠን ሰርቶ እራሱንና ቤተሰቡን ማሰተዳደር በሚቻልበት አገር እንኳን: ወንጌሉን ተከትለው እውነተኛይቱን ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት በሚያሰተምሩት በአባታችን በቀሲስ አስተርአየና በሌሎችም አባቶች ላይ የሚደርሰውን ግፍ ያየ: በአገር ቤትማ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያደግትም።

## በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ: በተለያዩ ወቅቶች የተጻፉት መጽሐፍቶች ስለ አዳም የውርስ ኃጢአት፥(ጥንተ አብሶ) ምን ይላሉ

ከላይ በሰፊው እንደገለጽኩት: የዚህ የሮማ ካቶሊክ እምነት እንዴት: በ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. በሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ በተመራው የሊቃውንት ጉባኤ ታይቶ በወቅቱ በነበረው ቅዱስ ሲኖዶሰ እንደጸደቀ አይተናል። እዚህ ላይ የሚያሰገርመው ነገር ቢኖር: ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ፥
፩ኛ. በ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. "የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት"
፪ኛ. በ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም. "ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ"
በሚሉት መጽሐፍቶቻቸው ላይ በሚገባ መንፈሰ ቅዱስ የእመቤታችንን ነፍስና ሥጋ አንጽቶ የአምላክ እናት ለመሆን እንዳበቃት እውነተኛውን የኦርቶዶክስ እምነትና ትምህርት ጽፈው መሰክረው አሰተምረው እያለ: ለማመን በሚሳን ሁኔታ ሀሳባቸውን ቀይረው እውነተኛውን የኦርቶዶከሰ እምነት አውግዘውና አስወግዘው ማየቴ በጣም ገርሞኛልም አሳዝኖኛልም። ይህ ድርጊታቸው፥ በዚህ ብቻ ሳይቆም፥
፫ኛ. በ ፲፱፻፷፪ ዓ.ም. " ምልጃ፥ እርቅና ሰላም "
፬ኛ. በ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. "ዜና ሕይወት ዘቅድስት ቅዱሳን እመ አምላክ"
ብለው ባሳተሟቸው መጽሐፍቶቻቸው፥ አላግባብ አውግዘው ያሰወገዙትን ትክክለኛውን የኦርቶዶክስ እምነት የሚነቅፍ ብቻ ሳይሆን: ስህተትን በሰህተት ለማረም በመሞከር: ምሥጢረ ጥምቀቱን ዋጋ አሳጥተውታል፥ በጌታችንና በመድኃኒታችን በእየሱስ ክርሰቶሰ ቦታ: እመቤታችንን የድኅነታችን መሰረት ነች በማለት ስህተት ጽፈዋል። ከዚህ የተነሳ፥ ከቅዱሳት መጽሐፍት ይልቅ ሰውን የሚከተሉ እንደነ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ ያሉ ሰዎቸ፥ እመቤታችንን በተመለከተ ጉዳይ የሳቸውን ስሕተተ በመከተል መጽሐፍትን በማጣመም በሰህተት ላይ ሰህተት እየጨመሩ *"ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን" (ሮሜ ፮፥፭)* ሲል ስለጥምቀት ቅዱስ ጳውሎስ በንጽጸር የተናገረውን ቆንጥሮ በመውሰድ "እኛ ክርስቲያኖች በሰጋ የምንሞተው ሞት: የክርሰቶሰን ሞት አብነተ አድርገን ነው..." እያሉ ከሰንበት ተማሪ የማይጠበቅ ሰህተት በመሰራት፥ የገቡበትን ሰህተተ በሌላ ሰህተት ለማረም በመሞከር ሰውን ያሳስታሉ። ይህንንና ሌሎቹን የመሪ-ጌታን ስህተቶች በሰፊው በገጽ: ፵ ላይ እመለሰበታለው።

ከዚህ በመቀጠል ከላይ የጠቀስኳቸውን የክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው መጽሐፍትን በተመለከተ: ሰለ እመቤታችን ያሉትን ትክክለኛነቱንና እንዲሁም ሰህተቱን በተቻለኝ አቅም አንድ በአንድ ለማብራራት እሞክራለው። በቅድሚያ ግን: ለአንባቢዎች ላሳስብ የምወደው ነገር ቢኖር፥ እኔ የኒህን ታላቅ ሊቃውንትና የሐገር ሀብት የሆኑ አባትን ነቅፎ ለመተቸት ወይንም ለማረም: እውቀቱም፥ ብቃቱም የሌለኝ ተራ ሰው ነኝ። የማከብራቸውና የማደንቃቸው ኦርቶዶክሳዊ አባት ናቸው። ሆኖም ግን በተለያዩ ወቅቶች የጻፏቸው መጽሐፍቶች፥ እመቤታችንን አሰመልክቶ፥ ሰለ አዳም የውርስ ኃጢአት (ጥንተ አበሶ) አንዱ ከአንዱ የሚጋጩ ነገሮችን ሰላገኘሁበት: ይህንን የሀሳብ መገጫጨት ሳይረዱ: እሳቸውንና መጽሐፍቶቻቸውን በመጥቀስ ይህን የሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ በማሰፋፋት ላይ ላሉ ሰዎችና ለናንተ ለአንባቢዎች በመጠቆም: የራሳቸውን መጽሐፍ መሰረትና ማሰረጃ በማድረግ፥ እመቤታችን በራሷ የሰራችውና ያሰበችው ምንም ኃጢአት የሌላባት ንጹኀት ብጽዕት ስትሆን: ነገር ግን ከሰው የተገኘች ሰው በመሆኗ: ክርስቶስን እስከጸነሰችበት ጊዜ ድረስ ቁራኝነት፥ አርዑተ ኀጥያት (ጥንተ አብሶ) ነበረባት የሚለውን ትክክለኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ደግፌ: የመሪ-ጌታን አቋም ነቅፌ ለማሰረዳት እሞክራለው። በዚህ አጋጣሚ ሳትሰለቹ: እኔን ሳይሆን: የማቀርባቸውን ነጥቦች ከመጽሐፍቱ ጋር በማመሳከር እውነቱን ለማየትና ለመፍረድ እግዚአብሔር ያመላክታቹህ።

## የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት
ከሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ
አዲስ አባባ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.

<u>የጺጋ ሰጊድ፥ በሚለው ንዑስ እርእስ ሰር ገጽ:፪፻፭</u>

*"የጌታችን እግር ከቆመበት እንሰግዳለን የሚለው ቅዱስ ቃልም የሚያሰተምረን: እግዚአብሔር ማደርያው ላደረጋቸው ለቅዱሳን: ይልቁንም መርጦ ከኃጢአት አንጽቶ በመንፈስ ቅዱስ ቀድሶ ሥጋዋን፥ ነፍሷን ለተዋሐዳት ለእመቤታችን ድንግል ማርያምና ለተሰቀለበት መሰቀሉ እንድንሰግድ ነው።"*

ከዚህ ከክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ አባባል እንደምንረዳው፥

፩ኛ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሰ የእመቤታችንን ሰጋና ነፍስ ከኃጢአት እንዳነጻ በገልጽ ይናገረል። እዚህ ላይ፥ ኃጢአት የሚለው ቃል ምን አይነት ኃጢአት ነው የሚል ጥያቄ ያመጣል? መልሱም፥

- እመቤታችን ምንም እንደኛ ሰው ሆና ብትፈጠርም፥ የአምላክ ማደሪያው ናትና ቤተ ክርስቲያናችን በራሷ የሰራችው ወይንም ያሰበችው አንድም ኃጢአት የለባትም ብላ ታምናለች ታሰተምራለች። ሆኖም ግን፥ ፍጹም ሰው: ፍጹም አምላክ ከኃጢአት በቀር የተባለለት ጌታችንና መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ብቻ በመሆኑና፥ "***ኃጢአት በበደሉትም ባልበደሉትም ላይ ሆነች***" ተብሎ እንደተጻፈው: እመቤታችንም፥ ከላይ ክርስቶስን በጸነሰች ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከኃጢአት አነጻት ሲል ከቁራኝነት፥ ከጥንተ አብሶ አነጻት ማለቱ ነው።

ሆኖም ግን አንዳንዶች ይህንን በግልጽ የተቀመጠ አባባል በራሳቸው ግንዛቤ አጣመው በመተርጎም የተሳሳተና ደካማ ነገር በመናገር ሕዝብን ለማደናገር ይሞክራሉ፥ ለምሳሌ፥ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ፥ ይህንን በተመለከተ በ ኅዳር ፮, ፪ሺ፪ ዓ.ም. በጻፉት ጽሑፍ በ ገጽ ፳፬ ላይ የሚከተለውን ብለዋል:

- ***"..መንፈሰ ቅዱስ ነፍስዋንና ሥጋዋን ከኃጢአት አንጽቶ የአምላክ እናት ለመሆን አበቃት..." ማለት እኮ፥ ከእናቷ ማሕፀን ከአዳም በደል ነጻ አድርጎ ፈጥሮ ሲሉ ነው፤ ምክንያቱም የነፍስና የሥጋ ውሕደት በማሕፀን እንጂ ከተወለዱ በኃላ ሰላልሆነ ነው።***

፪ኛ. ይህ አባባላቸው ፈጽሞ ስህተት ነው። ምክንያቱም እንደ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ አባባል ከሆነ፥ ጸሐፊው፥ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ "ይልቁንም መርጦ ከኃጢአት አንጽቶ በመንፈስ ቅዱሰ ቀድሶ ሥጋዋን፥ ነፍሷን ለተዋሐዳት" ከማለት ይልቅ "ይልቁንም መርጦ ከአዳም የውርስ ኃጢአት፥ከቁራኝነት (ከጥንተ አበሶ) ጠብቆ በመንፈስ ቅዱሰ ቀድሶ ሥጋዋን፥ ነፍሷን ለተዋሐዳት" ባሉ ነበር።

፫ኛ. መሪ-ጌታ እራሳቸው ***"የነፍስና የሥጋ ውሕደት በማሕፀን እንጂ ከተወለዱ በኃላ ሰላልሆነ ነው።"*** እንዳሉት: የነፍስና የሥጋ ከኃጢአት መንጻትም ሆነ መቀደስም: በአካል ከተፈጠሩ ( Physicaly Exist) ካደረጉ ባኃላ እንጂ: ገና ሳይፈጠሩ በሌለ ነገር ላይ አይደለም። ስለሆነም: ".. መንፈሰ ቅዱስ ነፍስዋንና ሥጋዋን ከኃጢአት አንጽቶ" ሲባል፥ እመቤታችን ከተፈጠረች በኃላ ነው እንጂ፥ እርሰዎ "***ከእናቷ ማሕፀን ከአዳም በደል ነጻ አድርጎ ፈጥሮ ሲሉ ነው***" ብለው ነፍስ ለብቻው ሥጋም ለብቻው ኖሮ ከጥንተ አብሶ እንደነጻና ከዛ ተዋሕደው እመቤታችን እንደተፈጠረች ለማለት መሞከረዎ የያዙት ሰህተት አልበቃ ብሎ፡ እመቤታችን ተፀንሳ ከመወለዷ በፊት ነበረች ወደሚለው ግዙፍ ስህተት ለመግባት በመንደርደር ላይ ነዎትና ያስተውሉ።

፬ኛ. ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት "አንጽሖ ሥጋሃ" (ሥጋዋን አንጽቶ) ብሎ ቅዱስ ያሬድ

የተናገረውን ቀጥተኛ አባባል: በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ይመራ የነበረው የሊቃውንት ጉባኤ፥ አንጽቶ የሚለውን ቃል ንጹህ እንደማለት ነው ብለው ትክክለኛ ትርጉሙን ጠምዝዘው የነሱን የተሳሳተ ሀሳብ ለማሳመን እንደሞከሩት ሁሉ: ዛሬም መሪ-ጌታ እኛን ለማታለልና ለማወናበድ *"ከኃጢአት አንጽቶ"* የሚለውን ሐረግ " *ከአዳም በደል ነጻ አድርጎ ፈጥሮ"* ማለት ነው ብለው ማየትና መገንዘብ እንደማንችል ቆጥረው መናገራቸው ምን ያህል ሰውን እንደናቁትና: እሳቸው እንዳመጣላቸው የሚሉትን ሁሉ ፈጠራና ተረት በጸጋ እንደምንቀበል አድርገው በድፍረት መናገራቸው: ከማሳፈር አልፎ: ቤተክርስቲያናችን እንደሳቸው ባሉ አንዳንድ ካህናት ተይዛ ማየቱ በጣም ያሳዝናል።

፬ኛ. በሌላ በኩል ደግሞ፥ እመቤታችን የአዳም የውርስ ኃጢአት ያልደረሰባት፥ ያልተላለፈባት ናት ከተባለ: ቀድሞውኑ ሲጀመር ጀምሮ መንጻት የማያስፈልገው "ነፍስና ሥጋን" *"ነፍስዋንና ሥጋዋን ከኃጢአት አንጽቶ"* ተብሎ ሊባልለት እንዴት ይቻላል?? ይሄ ማለት "እሳት በሌለበት ቦታ እሳት ለማጥፋት ማሞከር ማለት ነው።" ስለሆነም፥ የማያዛልቅ የፈጠራ ትንታኔ ለመስጠት ከመሞከር፥ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ አባቶቻቸው "አብ ላአጽንዖ: መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ ወልድ ለለቢሰ ሥጋ ያሉትን መሪ ቃል ተከትለው፥ ከላይ *“..መንፈሰ ቅዱስ ነፍስዋንና ሥጋዋን ከኃጢአት አንጽቶ የአምላክ እናት ለመሆን አበቃት...”* ብለው መንፈስ ቅዱስ፥ እመቤታችንን ከቁራኝነት፥ (ከጥንተ አብሶ) እንዳነጻት አሙልተውና አሰፍተው፥ ሰመ ጥሩ ሊቃውንቶች በነበሩበት ዘመን የመሰከሩትን ሃይማኖትና ትምህርት ማመንና መቀበል ትክክል ብቻ ሳይሆን አዋቂነትም ነው።

## ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ
### ከሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ
### አዲስ አባባ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

<u>ሥርዓት፥ በሚለው ንዑስ እርእስ ሰር በገጽ: ፳፯-፳፰</u>

"ብዙ ዘመን ካለፈ በኃላ እግዚአብሔር ዓለምን በልጁ ሲዋጅና በክርስቶስ ሁሉ አዲስ እንዲሆን ሲፈቅድ መበሥር መልአክ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም መጥቶ "መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል: የልዑል ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ ነው: የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል አላት" በዚህ ቃል የድንግል ሥጋዋም ነፍስዋም በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ: አዲስ ሕይወት አገኘ:: የልዑል ኀይል ወንድ ከማወቅ ድንግልና ከማጣት ዘር ከመቀበል በጠቅላላ ከዓለም ጠባይና ግብር ጠበቃት: ስለዚህ የመጀመሪያውን ቅድስና ከሰው ልጆች ሁሉ በፊት ለእግዚአብሔር እናት በመሆን ታደለች:: በዚህ መሰረት "ሰውነቴ በአምላኬ በመድኃኒቴ ደስ ይላታል" ብላ ለመናገር በቃች::(ሉቃ.፩፥፵፮ ና ፵፯)።

አንባቢ ሆይ፥ እንግዲህ ይህ ከዚህ በላይ ግልጥና በማያሻማ ሁኔታ: እመቤታችንን በተመለከተ በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ተብራርቶ: እውነተኛውን የኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ እምነትን የመሰከረውን ጽሑፍ አንድ በአንድ በታትነን እንመልከተው።

፩ኛ. *"ብዙ ዘመን ካለፈ በኃላ እግዚአብሔር ዓለምን በልጁ ሲዋጅና በክርስቶስ ሁሉ አዲስ እንዲሆን ሲፈቅድ መበሥር መልአክ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም መጥቶ "መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል: የልዑል ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ ነው: የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል አላት"* ከዚህ አባባል የምንረዳው፥

- ይህ ድርጊት የተፈጸመው እመቤታችን ሰትፀነሰ ሳይሆን ክርሰቶሰ ከእመቤታችን እንደሚፀነስ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ባበሰራት ወቅት መሆኑ ግልጽ ነው።

- ቀጥሎም: የሚያሳየን የክርስቶስን የአፀናነስ ሁኔታ ሲሆን፥ ለዚህም ድንቅ ስራ፥ ሥላሤ በመለኮት፥ በባሕርይና በፈቃድ አንድ ቢሆኑ፥ በአካል ያላቸውን የሰራ ድርሻ እንደሚከተለው በሚገባ ተገልጿል። ይኸውም፥
  - ፩ኛ. መንፈስ ቅዱስ በእመቤታችን ላይ እንደሚያድርባት
  - ፪ኛ. የልዑል ኃይል እመቤታችንን እንደሚጸልላት
  - ፫ኛ. ከሷ(ከእመቤታችን) የሚወለደው: የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ

፪ኛ. በመቀጠልም *"በዚህ ቃል የድንግል ሥጋዋም ነፍስዋም በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ: አዲስ ሕይወት አገኘ::"* ከዚህ አባባል የምንረዳው፥

- ከላይ መንፈሰ ቅዱስ በእመቤታችን ላይ እንደሚያድርባት የተነገረውን፥ ሰለ መንፈስ ቅዱስ የስራ ድርሻ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ አብራርተው አስፍተውና አሙልተው ሲተረጉሙት፥ "መንፈስ ቅዱስ የእመቤታችንን ሥጋዋንና ነፍስዋን እንደቀደሰ፥ ከዚህም የተነሳ እመቤታችን አዲስ ሕይወት እንዳገኘች" መሰከረዋል። እንግዲህ ይህ ከሆነ: መንፈስ ቅዱስ ሥጋዋንና ነፍስዋን ከቀደሰ በኃላ እመቤታችን አዲስ ሕይወት አገኘች ማለት ምን ማለት ነው? የሚል ተገቢ ጥያቄን ያስነሳል። ምክንያቱም፥

እመቤታችን ሰትፈጠር የአዳም የውርስ ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) ያልደረሰባት ናት ከተባለና፤ ሁላችንም እንደምናምነው በራሷ ያሰበችው፥ ያደረገችው ኃጢአት የሌለባት ከልማደ አንስት ነጻ የሆነች ንጽሕት ብፅዕት ሆና እያለ: *"ሥጋዋም ነፍስዋም በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ: አዲስ ሕይወት*

*አገኘ"* መባሉ፥ ክርስቶስን እስከፀነሰችበት ጊዜ ድረስ የነበረው የእመቤታችን *ሥጋዋ፥ ነፍስዋም ሆነ በአጠቃላይ* ሕይወቷ: ምን ጎድሎት ተገኝቶ ነው? የሚለው ተገቢ ጥያቄ ሊመለስ ይገባል። አዎ፥ ለዚህ መልሱ፥ ከመጀመርያውኑም እመቤታችን ሰው ሆና በመፈጠሯ፥ የአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ቁራኝነት (ጥንተ አብሶ) ስለነበረባት፥ መንፈስ ቅዱስ ከዛ ሰላነጻትና ስለቀደሳት *"አዲስ ሕይወት" አገኘች* ተባለ። ለዚህም ማስረጃው: ብዙ ሳንርቅ እራሳቸው ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ "የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት" በሚለው ከላይ በዝርዝር ባብራራሁት መጽሐፋቸው ላይ እንዲህ ሲሉ አረጋግጠዋል፥ *"ይልቁንም መርጦ ከኃጢአት አንጽቶ በመንፈስ ቅዱስ ቀድሶ ሥጋዋን፥ ነፍሷን ለተዋሐዳት ለእመቤታችን ድንግል ማርያምና ለተሰቀለበት መስቀሉ እንድንሰግድ ነው።"*

፫ኛ. በመቀጠልም *"የልዑል ኀይል ወንድ ከማወቅ ድንግልና ከማጣት ዘር ከመቀበል በጠቅላላ ከዓለም ጠባይና ግብር ጠበቃት"* ይላል: ከዚህ አባባል የምንረዳው፥

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ባበሰራት ጊዜ: የልዑል ኃይል ይጸልልሻል ተብሎ የተነገረለትን የልዑል እግዚአብሔርን የሰራ ድርሻ፥ አሁንም በድጋሚ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ አብራርተው አስፍተውና አሙልተው ሲተረጉሙት፥ የሊቁ አባታቸው ቅዱስ ቄርሎስ ሃይማኖትንና ትምህርትን መሰረት በማድረግ፥ ከሩካቤ፥ ዘር ከመቀበል፥ ድንግልና ከማጣት ጠበቃት ሲሉ መሰከረውታል።

- *"ቅዱስ ቄርሎስ ወደ ሱክንሲስ ሰዎች ጽፎ በላከበት በመጀመርያው መልእክቱ: እንደ ተናገረ: ስለዚህ ሕፃን ክርስቶስ ከእሷ ከተወለደ በኋላ ድንግል ንጽሕት ማርያምን ማኅተመ ድንግልናዋን ሳይለውጥ ጠበቃት: እሱ ድንቅ ድንቅ ሥራን የሚሰራ የባሕርይ አምላክ ነውና አሁንም እሱ በሰው ዘንድ ከተሰሩ ከታወቁ ከሦሰቱ ግብራት ንጹሕ ነው። እነዚህም፥ ሩካቤ፥ ዘር፥ የድንግልና መለወጥ ናቸው። ብሩክ የባሕርይ አምላክ እሱ ከሰው፥ ከእንስሳት: ልደቱን የሚመስለው: እንደሌለ በዚህ ሲያስረዳን: በድንግልና መወለድ ከዚህ በፊት አልተደረገም እንግዲህም አይደረግም። ስለዚህ ድንግል እግዚአብሔር ቃልን የወለደች እንደሆነች ተረዳን" (ሃይ. አበው ፸፲፥ ፳፱)*

እንግዲህ ከላይ በግልጽ እንደተቀመጠው፥ የመንፈስ ቅዱስ ሰራና የልዑል እግዚአብሔር ስራ ተለይቶ: መንፈሰ ቅዱስ እመቤታችንን ከአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ከቁራኝነት (ከጥንተ አብሶ) እንደ አነፃ፥ የልዑል ኀይል ከ፫ቱ ግብራት ማለትም ከሩካቤ፥ ዘር ከመቀበል፥ ድንግልና ከማጣት እንደጠበቃትና እግዚአብሔር ቃልም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ካሷ እንደተወለደ በሚገባ አይተናል። ይህንንም የሥሩጉ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱሰ ያዕቆብ እንደሚከተለው አሰቀምጦታል:*"*

- *መንፈሰ ቅዱስ በሥጋ በነፍስ አንጽቶ ያድርብሻል ኀይለ ልዑል ወልድም ከሦስቱ ግብራት ይከለክልሻል ብሎ መልአክ ለቅድስት ድንግል የነገራትን ነገር ይህ የሥሩግ ኤጲስ ቆጶስ ያዕቆብ ዳግመኛ እንዲህ አለ። ትንንሽ ሕፃናትን የሚፈጥር እርሱ ይዋሐደው ዘንድ ሥጋን ካንቺ ፈጠረ ልጆችን የፈጠረ እርሱ በማኅፀንሽ አደረ።" (ሃይ. አበው ፹፰፥ ፫)*

ሆኖም ግን ይህንን ሁሉ ማሰረጃ እያየ አሁንም ለማይቀበል፥ ከዚህ ቀጥሎ በ ፬ኛ ደረጃ የሚቀርበው ከላይ ያሰፈርኩት የክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ የጽሑፍ መዝጊያ አርፍተ ነገር ያማያንቀሳቅስ ነው ይሄውም፥

፬ኛ. *ስለዚህ የመጀመሪያውን ቅድስና ከሰው ልጆች ሁሉ በፊት ለእግዚአብሔር እናት በመሆን ታደለች:: በዚህ መሰረት "ሰውነቴ በአምላኬ በመድኃኒቴ ደስ ይላታል" ብላ ለመናገር በቃች:: (ሉቃ.፩፥፴፰ ና ፵፮)።* ይላል። እንግዲህ ከላይ እንዳየነው: ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ እመቤታችንን፥ በመንፈስ ቅዱስ ነፍስና ሥጋዋ ተቀድሶ አዲስ ሕይወት እንዳገኘች፥ የልዑል ኃይልም ከሩካቤ፥ ዘር ከመቀበልና፥ ድንግልና ከማጣት እንደጠበቃትና እግዚአብሔር ቃልም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ: አለምን ለማዳን ካሷ እንደተወለደ አስፍተው አሙልተው እውነተኛውን ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት ከመሰከሩልን በኋላ *"ስለዚህ የመጀመሪያውን ቅድስና ከሰው ልጆች ሁሉ በፊት ለእግዚአብሔር እናት በመሆን ታደለች::"* በማለት፥

- እመቤታችን የእግዚአብሔር ቃል፥ እናት በመሆን: ማለትም፥ እንደቃልህ ይሁንልኝ ብላ ቃል ሥጋ ሆኖ ክርስቶስ በመሐፀኗ ከተፀነሰበት ቅጽበት ጀምሮ: የመጀመሪያውን ቅድስና: ከሰው ሁሉ በፊት እንዳገኘችና፥

- ሆኖም ግን፥ የሰው ልጅ ሁሉ ይህን: እሷ በመጀመርያ ያገኘችውን ቅድስና: ከሷ በኃላ ጊዜው መቼ እንደሆነ ይሄ ነው ብለው ባይጠቅሱም " *የመጀመሪያውን ቅድስና ከሰው ልጆች ሁሉ በፊት"* በምትለው ሐረግ: እኛ ሁላችን እንዳገኘነው በሚገባ መስክረዋል።

እንግዲህ ይህ እመቤታችን ከሰው ልጆች በፊት ቀድማ ያገኘችው፥ በኃላም ለሰው ልጆች ሁሉ የደረሰን ይህ ቅድስና ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ: ለማንም አይምሮውን ከፍቶ፥ እውነቱን ለማወቅና ለመረዳት ለሚሻ: አጥጋቢና የማያወላዳ መልስ ይሰጣል። ስለዚህ የዚህን ጥያቄ መልስ: ቅዱሳት መጽሐፍትን ማሰረጃ በማድረግ መልሱን ለማግኘት ይህ ቅድስና እመቤታችንና እኛም ያገኘነው፥

፩ኛ. የአምላክ እናት መሆንን? ፈጽሞ አይደለም: ምክንያቱም ከእመቤታችን በቀር ያአምላክ እናት የሆነም፥ የሚሆንም ፈጽሞ የለምና።

፪ኛ. ከ፫ቱ ግብራት መጠበቅን? ፈጽሞ አይደለም፥ ምክንያቱም ያላ ሩካቤ፥ ያለወንድ ዘርና ድንግልናዋ ሳይለወጥ(ሳይገሰስ) በድንግልና ፀንሶ በድንገልና የወለደ በድንግልና ምድራዊ ሕይወቱን የፈፀመ ከእመቤታችን በቀር ማንም አልነበረም፥ አይኖርምምና።

፫ኛ. ከአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ከቁራኝነት መላቀቅ፥ (ከጥንተ አብሶ) መንጻት? ይህ ብቻ ነው ትክክለኛ መልሱ። ምክንያቱም፥

እግዚአብሔር አምላክ በዲያቢሎስ ተይዞ ዘላለማዊ ሞት የተፈረደበትን: በአምሳሉ የፈጠረውን ሰው፥ ለማዳን፥ ሞት አሸትቶ ሊይዘው የማይቻለውን፥ ከማንኛውም ኃጢአት ያልተነካካ የኛን ሥጋ መዋሐድ ስለነበረበት፥ በራሷ ያሰበችው ወይንም የሰራችው ኃጢአት ከሌለባት ንጽሕት ብጽዕት ከሆነች፥ ሆኖም ግን: እንደኛው ከአዳም የተገኘች በመሆኗ: በሞት ጥላ ስር ከሆነች ከቅድስት ድንግል ማርያም ይህን የሞት እዳ "አርዑተ ኀጥያት: ቁራኝነት: ጥንተ አብሶ አንጽቶ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ እኛን ለማዳን እንደ ሰው ተወለደ። በተወለደ በ፴፫ ዘመኑ በዕለተ አርብ በቀራንዮ መሰቀል ላይ ሞት ሊይዘው ያልቻለውን ሥጋ: በራሱ ፈቃድና ሥልጣን ነፍሰና ሥጋውን ለይቶ፥

- *"ኃጢአታችንን ስለማስተሰረይ ለእኛ የሚገባ ሞትን ሞተ: ቤዛችን በሚሆን ሞት ሞትን ያጠፋው ዘንድ ሞት በመሸፍ ባሕር ተሰጠመ: ሞት ጽናትህ የታ አለ? መቃብርስ ማሸፍህ የት አለ? ብሎ ሐዋርያ እንደተናገረ"(ሃይ. አበው ፳፫:፲)*

እንዳለው ቅዱስ አትናቴዎስ፥ የኛን ሞት በመሞት በሦስተኛውም ቀን በራሱ ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ በመነሳት፥ ሞትን ድል ነሳ።

ከዚህ የተነሳ: ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ *"እመቤታችን የመጀመሪያውን ቅድስና ከሰው ልጆች ሁሉ በፊት ለእግዚአብሔር እናት በመሆን ታደለች::"* ብለው ያሉትን ቅድስና: እራሷ እመቤታችን ሥላሴ በሷ ላይ የሰሩትን እጹብ ድንቅ ሰራ ከቁራኝነት፥ ከጥንተ አብሶ እንዳነፃትና ልጇም፥ አምላኳም እንዲሁም መድኃኒቷም እንደሆነ በግዛ አንደባቷ ስትመሰክር *"ሰውነቴ በአምላኬ በመድኃኒቴ ደስ ይላታል" ብላ ለመናገር በቃች::(ሉቃ.፩፥፴፭ ና ፵፯)::* ብለው መስክረዋል። ይህ ቅድስና ክርስቶስ ከተወለደ ከ፴፫ ዘመን በኋላ ጌታችንና መድኃኒታችን እየሱሰ ክርስቶስ፥ በከፈለው ዋጋ ሥጋውን ቆርሶ ባፈሰሰው ደሙ "ከአርዑተ ኃጢአት: ከቁራኝነት: ከጥንተ አብሶ አጥቦን እንደ እመቤታችን ለመንጻት አበቃን። ሰለዚህም: እግዚአብሔር አምላክ ይመሰገን። ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ሁለት ጥቅሶች: ከሊቃውንቱ መጽሐፍ ከሆነው ከሃይማኖተ አበውና ከቅዳሴ መጽሐፍ ላይ የተወሰዱ

ሲሆን: ከላይ ላየናቸውን ለክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ጽሑፎች ተጨማሪና በቂ ማስረጃዎቸ ናቸው። አንባቢ ሆይ፥ ከዚህ አልፎ መጽሐፍትን የለአግባብ አጣሞ በመተርጎምና በማን አለብኝነት ስሕተትን በስሕተት ለመደገፍ ማሞከር ለጊዜው ካልሆነ በቀር እራስን ማታለል ነው የሚሆነው።

- *፮ኛ. ቅዱስ ጎርጎርዮስ፥ "ቃል በግብረ ቅዱስ ከሰው የተ ገረው ትርጓሜም ከሐድያን መናፍቃን ሰዎች እንደሚያስቡት ለመንፈስ ቅዱስ ሥጋ ኖሮት ወይም የተፈጠረ ሆኖ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ የማርያምን ሥጋ አ ጻ ቀደሰ የአብ አካላዊ ቃልንም ለመፅ ስ የበቃች አደረጋት እንጂ። (ሃይ .አበው: ፴፮:፲፱)"*

- *፯ኛ. ያዕቆብ ዘሥሩግ፥ "ከአብ ያልተለየ ረጅም ፈትል ሰማይንና ምድርን የፈጠርህ በፈቃድህ ከሰማያት ወረድህ የድንግል ማኅፀን ወሰ ህ የድሆች ልጅ ትንሽ ብላቴና ገሊላዊት አቀፈችህ አጸናሃት ባንተ አልደ ገጠችም። ፍስዋን አከበርህ ሥጋዋንም አ ጻሕ።" (ቅዳሴ ገጽ ፫፻፵፫: ፳፩)*

ከዚህ በመቀጠል: ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ: ከላይ ባየናቸው ሁለት መጽሐፍቶቻቸው ላይ: በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ያሰፈሩትን አቋማቸውንና እምነታቸውን ለማመን በሚያዳግት ሁኔታ: ሙሉ በሙሉ ለውጠውና ቀይረው : በ ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. በሳቸው ስብሳቢነት ይመራ የነበረው የሊቃውንት ጉባኤ በከፈተው ቀዳዳ ገብቶ: ለመጀመርያ ጊዜ በኢ.ኦ.ተ ቤ/ክር ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲጸድቅ የተደረገውን "እመቤታችን የአዳም የውርስ ኃጢአት፥ አርዐተ ኀጥያት (ጥንተ አበሶ) አልደረሳባትም" የሚለውን የሮማ ካቶሊክ ትምህርት በሰፊው የሚያብራሩ፥ ሁለት መጽሐፍቶችን በ ፲፱፻፺፪ እና በ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም አሳትመዋል። እነዚህ መጽሐፍቶች በይበልጥም በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የታተመው "ምልጃ፥ እርቅና ሰላም" የሚለው መጽሐፍ ብዙ የዘመኑ ሰባኪያንን፥ የሃይማኖት መጽሐፍ ጸሐፊዎችንና አንዳንድ ብፁዐን አባቶችን፥ እመቤታችንን በተመለከተ: ይህን የተሳሳተ የሮማ ካቶሊክ እምነትና ትምህርት በሰፊው እንዲሰብኩትም ሆነ እንዲጽፉት በር የከፈተና፥ ያበረታታ ነው። ለዚህም ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው: ከብዙ በጥቂቱ: በማሕበር ደረጃ: ማሕበረ ቅዱሳን፥ ከቄስ፥ እንደ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ ሲሆኑ፥ ከጳጳሳቱ ደግሞ፥ ብፁዕ አቡነ ማቲያስ ናቸው። ይህን ያልኩበት ምክንያት: በየጊዜው እየታተሙ ከሚወጡት መጽሔቶች ባሻገር፥ ይህ የነገረ ሃይማኖቱ ውዝግብ የዛሬ አምስት አመት በደብራችን ሲጀመር: ብፁዕ አቡነ ማቲያስ በደብራችን ተገኝተው: አባታችን ቀሲስ አሰተርአየን አግደው የሮማ ካቶሊኩን ኑፋቄ አጽድቀው ሲሄዱ፥ ለውሳኔያቸው መሰረት አድርገው ካቀረቧቸው አምስት ማሰረጃዎች መካከል: ፬ቱ ከክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተያያዙ ናቸው። እነሱም፥

፩ኛ. ሉቃ. ፩፥ ፳፮-፴፰

፪ኛ. በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ሰብሳቢነተ ይመራ የነበረው የሊቃውንት ጉባኤ እነ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴክን ፥ ክቡር መጋቤ ብሉይ ስይፈ ሥላሴንና አቶ አሰራት ገብረ ማርያምን አሰመልክቶ ለቅዱስ ሲኖዶሱ ያሰተላለፈውን አሰተያየት። (እ.ኢ.ት.ዘ.አ. ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. ት/ሊ/ጉ/፹፬ ገጽ ፭፥፮ እና ፯)

፫ኛ. ይህ ከላይ በተራ ቁጥር ፩ ላይ የጠቀስኩትን: በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ሰብሳቢነተ ይመራ የነበረው የሊቃውንት ጉባኤ ያስተላለፈውን አሰተያየት መሰረት አድርጎ በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. በኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ሰም " የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት" በሚል የታተመ መጽሐፍ።

፬ኛ. ምልጃ፥ እርቅና ሰላም። (በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ የተጻፈ መጽሐፍ ገጽ ፺፱)

፭ኛ. "በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለው: ከማሕፀን ሳትወጣ ቀድሼሐለው: ለአሕዛብም ነብይ

አድርጌሃለው" (ኤር. ፩፥፭)

አንባቢ ሆይ፥ ከላይ በተራ ቁጥር ፪፥፫ እና ፬ ላይ በብፁዕ አቡነ ማቲያስ የቀረቡት ዋነኛ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት: ማስረጃዎቹ በሙሉ የክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ውሳኔዎች ያሉባቸው ናቸው። ይህን ነጥብ ሳቀርብ ለማለት የፈለኩት ነገር፥ ብፁዕ አቡነ ማቲያስም ሆኑ ሌሎች የዘመኑ አስተማሪዎች፥ ይህን የተሳሳተ የሮማ ካቶሊክ እምነት በድፍረት ሲሰበኩም ሆነ ሲጽፉ የሚጠቅሱት "ምልጃ እርቅና ሰላም ገጽ: ፵፱ " የሚለውን የክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩን መጽሐፍ ሲሆን: የሚገርመው ግን እዚሁ መጽሐፍ ላይ በገጽ: ፺፪-፺፬ ላይ ያለውን ምስቅልቅሎሽ ልብ አላሉትም። ይህ የሚያሳየው፥ የመጽሐፉ ባለቤት ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ: ለቤተ ክርስቲያናችን ያበረከቱትን: ይሄ ነው የማይባል ከፍተኛ አስተዋፆ፥ ያላቸውን ከፍተኛ እውቀትና ማዕረግ ብቻ በመመልከት: ምንም ሊሳሳቱ አይችሉም ብሎ በማመን ያለምንም ግንዛቤ መጽሐፉን በደፈናው ስለተቀበሉ ነው። ስለሆነም ይሄንን በገጽ: ፺፪-፺፬ ላይ ያለውን ምስቅልቅሎሽ በቦታው ሰንደረስ አሳያለው።

በመቀጠልም: ከላይ በዝርዝር እንዳሳየሁት: እራሳቸው ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ይህን ከላይ በተራ ቁጥር ፩ ላይ የሰፈረውን የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል፥ (ም.፩፥፳፮-፴፯) መሰረት በማድረግ "ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ" ብለው በጻፉት መጽሐፍ ላይ *"ብዙ ዘመን ካለፈ በኃላ እግዚአብሔር ዓለምን በልጁ ሲዋጅና በክርስቶስ ሁሉ አዲስ እንዲሆን ሲፈቅድ መበሥር መልአክ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም መጥቶ "መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል: የልዑል ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ ነው: የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል አላት" በዚህ ቃል የድንግል ሥጋዋም ነፍስዋም በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ: አዲስ ሕይወት አገኘ።* ብለው እንደመሰከሩና እኔም በተጨማሪ በሊቃውንት መጽሐፍ በታጀበ ማስረጃ መንፈስ ቅዱስ እመቤታችንን ከ ቁራኝነት፥ ከአዳም የውርስ ኀጥያት (ከጥንተ አብሶ) እንዳነጻት አሳይቻለው። ስለሆነም፥ ብፁዕ አቡነ ማቲያስ ይረዳኛል ብለው ለማስረጃነት ያቀረቡት ጥቅስ: ዞሮ በሳቸው ላይ እንደመሰከረባቸው አስተውሉ።

አሁንም በድጋሚ፥ በተራ ቁጥር ፭ ላይ የቀረበው ማስረጃ የሚያሳየው ምን ያህል ቤተክርስቲያናችን ችግር ላይ እንዳለች ነው። ምክንያቱም፥ *"በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለው: ከማሕፀን ሳትወጣ ቀደሼሐለው: ለአሕዛብም ነብይ አድርጌሃለው" (ኤር. ፩፥፭)* የሚለውን ጥቅስ አንስቶ፥ እንካን እመቤታችን ነብዩ ኤርሚያስም ጥንተ አበሶ የለበትም ብሎ አንድ የቤተ ክርስቲያኗ ሊቀ ጳጳስ እንደ ማስረጃ አድርጎ ማቅረብ በጣም ያሳዝናል ያሳፍራልም።

ከዚህ በመቀጠል፥ በ ፲፱፻፺፪ እና በ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ የተጻፉትን ሁለት መጽሐፍቶች እንመለከታለን። እነዚህን መጽሐፍቶች አሰተውሎ ላያቸው: በውስጣቸው እርስ በርሳቸው የሚገጫጩ ሀሳቦች ያሉባቸውና ስህተትን በስህተት ለመደገፍ የተሞከረባቸው ናቸው። ስለሆነም፥ ከዚህ በመቀጠል ካላይ እንዳደረኩት፥ በሁለቱንም መጽሐፍቶች ላይ: እመቤታችንን አሰመልክቶ ሰለ (ጥንተ አብሶ) ያየሁትን ሰህተትና የሀሳብ መገጫጨት: እንደሚከተለው በትህትና አቀርባለው።

**ምልጃ፥ እርቅና ሰላም**
**ከአለቃ አያሌው ታምሩ**
**አዲስ አባባ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.**

*"ልዑል እግዚአብሔር ከፍጥረት ሁሉ፣ ከሰው ዘር ሁሉ፣ ከሴቶች ሁሉ እሷን ለእናትነት መርጧል፤ በዚህም ምርጫ ከሁሉም አልቋታል፣ አክብሯታል። ስለዚህም ለናትነት የመረጣትን ማደሪያውን ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ ከኃጢአት፣ ከርኩሰተ፣ ከህድፈት ሁሉ ጠብቋታል። የሰው ልጆች የተያዙበት፣ በአዳም በደል ወይንም በራሣቸው በደል ምክንያት የረከሱበት የኃጢአት ቅሪት መርገመ ሥጋ፥ መርገመ ነፍስ የለባትም፤ አላገኛትም። ምክንያቱም እሱ ለራሱ ማደርያ አድርጎ ስለመረጣት ነው።" (ገጽ: ፵፱)*

ከዚህ ከላይ ከሰፈረው ጽሑፍ እንደምንረዳው: እመቤታችን የአዳም የውርስ ኀጢአት፥ ቁራኝነት ወይንም ጥንተ አብሶ እንዳልደረሳባትና እንዳላገኛት በግልጽ ያሰረዳል። ሆኖም ግን በመቀጠልም በገጽ: ፶፪ ላይ እና በገጽ: ፶፫ ላይ ደገሞ እንዲህ ይላል፥

*እንግዲህ ከዚህ በላይ እንዳየነው እግዚአብሔር ቃል የቤዛነቱን ሥራ የፈጸመው ከእመቤታችን ሥጋን ነፍስን ነሰቶ ነው። የቤዛነት ሥራም የተጀመረው ጌታ ቁራኝነትን ባጠፋበት በዕለተ ጽንስ ሲሆን፣ የተፈጸመው በዕለተ ስቅለት በዕለተ ትንሣኤ ነው። ቅዱስ ያሬድም፣ ቅዱስ ጳውሎስም በምሥጢር የሄዱበት መንገድ መሰረቱ የነቢዩ የዳዊት ቃል ነው። (ገጽ: ፶፪)*

*በእመቤታችን ከምንመካበት ከተሻረው የመርገም ክፍልም አንዱ ቁራኝነት ነው። ጌታ ሰው ከመሆኑ በፊት ሰው ሁሉ በዘር በደም ከእናት ከአባት ሲከፈል በውርስ ኃጢአት ይተላለፍበት እንደነበረ፣ በዚህም ምክንያት በቁራኝነት ይያዝ እንደነበረ ይነገራል። ነገር ግን ጌታ ይህንን ማለት ቁራኝነትን የኃጢአትንም በውርሰ መተላለፈ በጽንስ በጀመረው የቤዛነት ሥራው ሰላሻረውና ሰለአጠፋው ከጌታ ሰው መሆን ወዲህ በማንኛውም የሰው ዘር ላይ ቁራኝነት የለም። የውርስ ኃጢአት የለም። (ገጽ: ፶፫)*

አንባቢ ሆይ፥ እዚህ ከላይ ካየናቸው ሁለት አርፍተ ነገሮች ላይ የሚከተሉትን ሐረጎች አብረን እንድናያቸው በትህትና እጠይቃለው፥ በገጽ: ፶፪ ላይ፥

- *"የቤዛነት ሥራም የተጀመረው ጌታ ቁራኝነትን ባጠፋበት በዕለተ ጽንስ ሲሆን፣ የተፈጸመው በዕለተ ስቅለት በዕለተ ትንሣኤ ነው።"* ይላል፥

ከዚህ ጽሑፍ እንደምንረዳው: ቁራኝነት፥የአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ጥንተ አብሶ የጠፋው: ጌታችንና መድኃኒታችን እየሱስ ክርሰቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተጸነሰ እለት ሲሆን አለምን ለማዳን ቤዛነቱን የፈጸመው ደግሞ በእለተ ስቅለት በዕለተ ትንሣኤ እንደሆነ ያሳየናል።ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በገጽ ፶፫ ላይ፥

- *"በእመቤታችን ከምንመካበት ከተሻረው የመርገም ክፍልም አንዱ ቁራኝነት ነው። ጌታ ሰው ከመሆኑ በፊት ሰው ሁሉ በዘር በደም ከእናት ከአባት ሲከፈል በውርስ ኃጢአት ይተላለፍበት እንደነበረ፣ በዚህም ምክንያት በቁራኝነት ይያዝ እንደነበረ ይነገራል።"*

እዚህ ላይ በድጋሚ በግልጽ እንደተቀመጠው፥ ቁራኝነት ወይንም የውርስ ኃጢአት ከዘር ወደዘር እንደሚተላለፍና ሰው ሁሉ በዚሁ ቁራኝነት እንደሚያዝ በገልጽ ያሳይና: በመቀጠልም፥

- *"ነገር ግን ጌታ ይህንን ማለት ቁራኝነትን የኃጢአትንም በውርሰ መተላለፈ በጽንስ በጀመረው የቤዛነት ሥራው ሰላሻረውና ሰለአጠፋው ከጌታ ሰው መሆን ወዲህ በማንኛውም የሰው ዘር ላይ ቁራኝነት የለም። የውርስ ኃጢአት የለም።"* ይላል፥

አንባቢ ሆይ፥ እንደሚታወቀው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ሲያበስራት፥ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ ባለችበት ቅጽበት: እግዚአብሔር ቃል ሥጋ ሆነ። እንግዲህ: ከዚች ጊዜ ጀምሮ: ጌታችንና መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት በቀር ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ሆነ። ታዲያ እንግዲህ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ እንደሚሉት፥ እመቤታችን የውርስ ኃጢአት፥ ቁራኝነት ወይንም ጥንተ አበሶ አልደረሳባትም ከተባለ፥

- *"ጌታ ይህንን ማለት ቁራኝነትን የኃጢአትንም በውርሰ መተላለፈ በጽንስ በጀመረው የቤዛነት ሥራው ሰላሻረውና ሰለአጠፋው ከጌታ ሰው መሆን ወዲህ በማንኛውም የሰው ዘር ላይ ቁራኝነት የለም። የውርስ ኃጢአት የለም።"*

ብለው ያሉት: ጌታችን ሲጸነስ በእመቤታችን መሐፀን የጠፋውና፥ የተሻረው የማን የውርስ ኃጢአት፥ ቁራኝነተ ነው ሊሉ ነው??? የጌታችን ነው እንዳይባል: ከሰማይ ይዞት የመጣ ሥጋ የለ። የለበሰው ያው የሷን ሥጋ ነው። አለምም የዳነ: በዕለተ አርብ ጌታችን በመሰቀል ላይ በከፈለው ካሳ ነው። እስከዛች ሰአት ድረሰ አለም አልዳነም። አለምም ዳነ ሲባል: እሳቸው ከላይ *"በማንኛውም የሰው ዘር ላይ ቁራኝነት የለም"* እንዳሉት ሳይሆ፥ ክርስቶስ በመሰቀል ላይ ሥጋውን ቆርሶ: ደሙን አፍስሶ እዳዬን ከፍሎልኛል ብለን ላመንና ለተጠመቅን በክርሰቶስ ክርሰቲያን ለሆን እንጂ፥ ሰው ብቻ በመሆኑ ላላመነ፥ ላልተጠመቀ ለእሰላሙም፥ ለአይሁዱም፥ ለጣኦት አማኙና ለመሳሰሉት ኢአማኒያን ማለት አይደለም። እንዲህ ከሆነማ፥ *"ኃጢአትን ለማስተሰረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ብለን የምንለው ከንቱና ዋጋ ቢስ መሆኑ ነው።"* ለዚህ ነው አባቶች እንዲህ ያለ የተመሰቃቀለ ነገረ ሲገጥማቸው "እንዲያ ሲል ያውካል የሚሉት።" ያም ሆነ ይህ: መልሱ ግን፥ ጌታችን በእመቤታችን መሐፀን ሲፀነሰ ሰው ሆና በመፈጠሯ በሷ ለይ የነበረውን የውርስ ኃጢአት፥ ቁራኝነት (ጥንተ አብሶ) አንጽቶ ከነፍሷ ነፍስ ከሥጋዋ ሥጋ ነሰቶ ተዋሐደ። ከሠላሣ ሦስት ዘመን በኃላ በዕለተ አርብ: ጌታችን በመሰቀል ላይ ሞታችንን ሞቶ በሦስተኛውም ቀን ሞትን ድል አድርጎ መነሳቱን ላመንና ለተጠመቅን: ቁራኝነተ፥ የውርስ ኃጢያት (ጥንተ አብሶ) ተሻረልን። ስለዚህ፥ ሐቄና እውነተኛይቱ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት እቺ ነች ብለው አባቶች፥

- *"ወአናሚሁኒ መንፈስ ቅዱስ። ያነጻ የከፈለ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነው። እመንፈስ ቅዱስም ቢል: በመንፈስ ቅዱስ ተከፍሎ ኑሮበት አይደለም አነፃ ሲል ነው እንጂ። ወአኮ ዘቦቱ ሥጋ ለመንፈስ ቅዱስ አላ መንፈስ ቅዱስ አንጽሖ ሥጋሃ ለማርያም ወረስያ ድሎተ ለተዋክፎ ቃል አብ እንዲል" (ቅዳሴ ማርያም የአንድምታ ትርጓሜ)*

ብለው ተንትነው ተርጉመው ያሰተማሩንንና ያቆዬልንን ሃይማኖት በሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ ማንም ሊበርዘውም ሆነ ሊታካውም ፈጸሞ አይችልም።

አዎ፥ ከቡርነታቸው የነበራቸውን አቋምና እምነት ባይቀይሩት ኖሮ፥ *"የቤዛነት ሥራም የተጀመረው ጌታ ቁራኝነትን ባጠፋበት በዕለተ ጽንስ ሲሆን፣ የተፈጸመው በዕለተ ስቅለት በዕለተ ትንሣኤ ነው።"* ብለው ከላይ የመሰከሩትን ትክክለኛውንና ኦርቶዶክሳዊውን እምነት፥ ከላይ በሰፊው ባብራራሁት እራሳቸው "ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ" ብለው በጻፉት መጽሐፍ ላይ፥ ይህንኑ ድንቅ የአምላክ ሰራ ማለትም፥ የእመቤታችን ከቁራኝነት መንፃትን ከሰው ልጆች ሁሉ በፊት ጌታን ስተፀንስ እንደተፈፀመላትና አለም ደግሞ በተራው ለሷ ቀድሞ የታደለውን ይህንን ቅድስና: በዕለተ አርብ ጌታችን በመሰቀል ላይ በከፈለው ካሳ ለመቀዳጀት እንደበቃና እሷም ይሄንን መሰረት አድርጋ *"ሰውነቴ በአምላኬ በመድኃኒቴ ደስ ይላታል" ብላ ለመናገር በቃች::(ሉቃ.፩፥፴፭ ና ፵፮)።* ብለው እኔ ደካማው: ልገልፀውና ለብራራው ከምችለው በላይ አሰፍተውና አሙልተው አሰተምረውት ነበር።

ከዚህ በመቀጠል: ይህን የተሳሳተ የሮማ ካቶሊክ እምነትን ለመደገፍ ሲባል: ሰህተትን በሰህተት ለመጠገን በተሞከረው ሙከራ: ከላይ በመጠኑ ጠቆም አድርጌ ያለፍኩትን፥ ለድጎነታችን አንዱና ዋነኛው የሆነውን፥ ለክርስቲያን ከአዳም የውር ኃጢአት (ከጥንተ አበሶ) መንጽያችን

የሆነውን ምሥጢረ ጥምቀትን በዚሁ መጽሐፍ ላይ ቦታ አሳጥተውታል። ይሄውም እንደሚከተለው ነው፥

*ጌታ ይህንን ማለት ቁራኝነትን የኃጢአትንም በውርሰ መተላለፈ በጽንስ በጀመረው የቤዛነት ሥራው ሰላሻረውና ሰለአጠፋው ከጌታ ሰው መሆን ወዲህ በማንኛውም የሰው ዘር ላይ ቁራኝነት የለም። የውርስ ኃጢአት የለም። ማንኛውም ሰው በራሱ ኃጢአት ከሚጠየቅ፣ ከሚከሰስ፣ ከሚወቀስ፣ በቀር በአዳም በደል አይከሰስም፣ አይወቀሰም። ሰለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ በአንድ ሰው በደል ምክንያት ዓለም ሁሉ እንደተፈረደበት በአንድ ሰው ጽድቅም ምክንያትም ሰው ሁሉ ይጸድቃል። ኃጢአት ከበዛች ዘንድ የእግዚአብሔር ጸጋ በዛች። ብሎ ጽፋአል። (ሮሜ ፭፥ ፲፪-፲፱)* ካሉ ባኋላ በመቀጠል፥ *እንግዲህ የውርስ ኃጢአት ሕፃናትም እንኳ ቢሆኑም የሌለባቸው መሆኑን ማንም ሊገነዘበው ይገባል።* በማለት ይሄንን ሀሳብ እነዲደግፍላቸው የሚከተለውን በማለት ያጠቃልሉታል፥ *"እውነት እነግራችኋለሁ መንግሰተ ሰማያትን እንደ ሕፃናት ያልተቀበላት አይገባባትም። ማለቱን ቅዱስ ወንጌል ያሰተምረናል። (ማቴ. ፲፱፥ ፲፫-፲፭, ማር. ፲፥ ፲፫-፲፮, ሉቃ. ፲፰፥ ፲፭-፲፯) እንግዲህ ጌታ ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ አትከልክሏቸው ካለ በኃላ መንግስተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና ማለቱ የውርስ ኃጢአት ላለባቸው ናት ማለቱ ነውን? አይደለም። የሕፃናትን ንጽሕና ማረጋገጡ ነው። (ገጽ: ፶፬)።*

ይህ ከላይ *"እውነት እነግራችኃለሁ መንግሰተ ሰማያተን እንደ ሕፃናት ያልተቀበላት አይገባባትም።"* የሚለውን የክርስቶሰን ቃል ወስዶ *"እንግዲህ የውርስ ኃጢአት ሕፃናትም እንኳ ቢሆኑም የሌለባቸው መሆኑን ማንም ሊገነዘበው ይገባል።"* ማለት ፈጽሞ ስህተት ነው። ክርስቶስ ይህንን የተናገረው፥ ሕፃናት እንደ አዋቂ አሰበውና አቅደው ኃጢአት ሰላማይሰሩ፥ ሰላማይዋሹ፥ ቂም ሰላማይዙና ሰላማይበቀሉ፥ የተነገራቸውን ማንኛውንም ነገር በየዋህነትና ሙሉ በሙሉ ያለጥርጥር ሰለሚቀበሉና ሰለሚታዘዙ፥ የነሱን የተቀደሰና ገና ያልጎደፈ ባሕሪና ፀባይ ምሳሌ አድርጎ መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ የሰው ልጅ እንደ ሕጻናት መሆን እንዳለበት ለደቀመዛሙርቱ ለማሰተማር እንጂ፥ የውርስ ኃጢአት የለባቸውም ለማለት አይደለም። እንዲህ ከተባለ ደገሞ፥ እንግዲህ ሕፃናቱ ማደጋቸው አይቀርምና፥ ሲያድጉ የአዳም የውርስ ኃጢአት እንደ ጉፋን ሊይዛቸው ነው ማለት ነዋ?? ይህ ብቻ ሳይሆን: ከላይ እንደገለጽኩት ሕፃናት በራሳቸው ያሰቡትና የሰሩት ኃጢአት ፈጽሞ ባይኖርባቸውም፥ ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ከአዳም የውርስ ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) የተነሳ እንኳን ተወልደው በናታቸው መሐፀንም እያሉ ይሞታሉ።

ይህም ሰለሆነ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን፥

- *"ኢየሱስም መልሶ። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው። ኒቆዲሞስም። ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው። ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። (ዮሐ.፫፥፫-፭)*

የሚለውን የጌታን ቃል መሰረት በማድረግ: ከአዳም የውርስ ኃጢአት የሚያነጻንን ሚሥጥረ ጥምቀትን ታከናውናለች። ይህ በመሆኑም ቤተክርስቲያናችን ወንድ ልጅ በተወለደ በ አርባ ቀኑ፥ ሴት ልጅ በተወለደች በ ሰማንያ ቀኗ ታጠምቃለች። እንደውም በጠና ታሞ ይሞታል ተበሎ የሚጠበቅ ሕፃን፥ አርባ ቀን ወይንም ሰማንያ ቀን ሳይጠበቅ ወድያውኑ ይጠመቃል። ይህ ሁሉ የሚደረገው: ሕፃናቱ ኃጢአተኛ ሁነው ሳይሆን፥ ያው ሰው በመሆናቸው ከአዳም የውርስ ኃጢአት እንዲነጹ ለማድረግ ነው። ለዚህም፥ ቤተ ክርስቲያናችን የሚከተለውን ብላ ታሰተምራላች፥

- *"ጥምቀት በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ለሚያምን ሰው ሁሉ የሚሰጥ የኃጢአት መደምሰሻ፥ ከእግዚአብሔር የልጅነትን ጸጋ መቀበያ፥ የመንግስተ ሰማያትን መውረሻ ነው....። አምኖ የሚጠመቅ ሁሉ የኃጢአት ሥርየትን ያገኛል፥ ኃጢአትን ለማሰተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን (ጸሎተ ሃይማኖት) ማንም ሰው በጥምቀት ከእግዚአብሔር ይወለዳል፥ ከፍዳ ይድናል።* (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት። ገጽ: ፳፯-፳፰)

እንግዲህ ከላይ በሚገባ እንዳየነው፡ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ሕጻናትም የአዳም የውርስ ኃጢአት እንዳለባቸው በማመን ጌታ እንዳዘዘው ከመንፈስ ቅዱስ ተወልደው ከጥንተ አብሶ እንዲነጹ በአርባና በሰማንያ ቀን አንዴ ታጠምቃለች። ከዚያ በኋላ ግን ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ እንዳሉት፥ ማንም ሰው የሚጠየቀው እራሱ በሰራው ኃጢአትና በደል ነው። ከዚህም የሚነፃው በጥምቀት ሳይሆን ለሰራው ኃጢአትና ለበደለው በደል ከልብ ተጸጽቶ በሚገባው ንሰሐ ብቻ ነው።

# ዜና ሕይወት ዘቅድስት ቅዱሳን እመ አምላክ

ከአለቃ አያሌው ታምሩ

አዲስ አበባ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

*"አዎን፥ ሙታንን በሚያነሣ በእግዚአብሔር እንጂ በራሳችን እንዳንታመን፥ እኛ ራሳችን የሞትን ፍርድ በውስጣችን ሰምተን ነበር። እርሱም ይህን ከሚያህል ሞት አዳነን፥ ያድነንማል፤ እናንተም ደግሞ ስለ እኛ እየጸለያችሁ አብራችሁ ስትረዱን፥ በብዙ ሰዎች በኩል ስለ ተሰጠን ስለ ጸጋ ስጦታ ብዙዎች ስለ እኛ ያመሰግኑ ዘንድ፥ ወደ ፊት ደግሞ እንዲያድነን በእርሱ ተስፋ አድርገናል።ትምክህታችን ይህ ነውና፤ በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ በሥጋዊ ጥበብ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ቅድስናና ቅንነት በዚህ ዓለም ይልቁንም በእናንተ ዘንድ እንደኖርን የሕሊናችን ምስክርነት ነው። (፪ኛ.ቆሮ. ፩፥፱-፲፪)።"*

ከላይ: ትምክህታችን፥ መመኪያችንና ተሰፋችን እግዚአብሔር ነው ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን እውነተኛ ቃል ጠምዝዞና ገልብጦ፥ ስለ እመቤታችን እንደተነገረ አሰመሰሎ በማሰቀመጥ: የአንባቢን ልብና ሰሜት ለመኮርኮረ ታቅዶ: በመጽሐፉ ሽፋን ላይ እመቤታችን ልጇን ታቅፋ ካለው ምሰል በላይ፥

- "እስመ ዛቲ ይእቲ ትምክሕትነ ወስምዐ ገዕዛንነ በምሕረቱ ወበተመይጦቱ ለእግዚአብሔር።" "በእግዚአብሔር ቸርነቱና ይቅርታው መመኪያችን፥ የነጻነታችን ምስክር ይኸቺ ናትና።"(፪ ቆሮ፤ ፩:፲፪።)

በማለት የሚጀምረው ይህ በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ የተጻፈው መጽሐፍ፥ ከሞላ ጎደል ያተኮረው።

- በደብረ ሣሕል መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክር ምዕመናን ለኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ቅዱስ ሲኖዶሰና ሊቃውንት ጉባኤ በተላከው ሰነድ ላይ፥ ቀሲሰ አስተርአየ በ ክፍል (Section D & E) ነገረ ሃይማኖቱን በተመለከተ የጻፉትን

- በዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው በወቅቱ የነበረው የማሕበረ ካህናት ነገረ ሃይማኖቱን በሚመለከት አድርጎ በነበረው ጉባኤ ላይ የደረሰበትን ውሳኔ፥ ማለትም የቀሲስ አሰተርአየ እምነትና ትምህርት ትክክለኛው የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር መሆኑን በማረጋገጥ ለኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ቅዱስ ሲኖዶሰና የሊቃውንት ጉባኤ የላኩትን ሰነድና

- "ድንግል ሆይ! በሕጋዊ ጋብቻ ከኢያቄምና ከሐና ተወለድሽ" በሚል ርእስ በአሁኑ ሰአት የቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ሐላፊ ሆነው በሚያገለግሉት በብፁዕ አቡነ ገብርኤል በግንቦት ወር በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. "ዜና ልደታ" በተባለ በዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው ልደታ ለማርያም የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር በሚያዘጋጀው መጽሔት ለይ ያወጡትን ጽሑፍ በሚመለከት ነው።

የመጽሐፉ ዋና ፍሬ ነገር፥ በ፲፱፻፹፩ ዓ. ም. በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ሰብሳቢነት ይመራ የነበረው የሊቃውንት ጉባኤ፥ "እመቤታችን የአዳም የውርስ ኃጢአት ያልተላለፈባት፥ ያልደረሰባት ናት..." ሲል፥ (Immaculate Conception) በመባል የሚታወቀውን የሮማ ካቶሊክ ትምህርትና እምነት ያጸደቀበትን መግለጫና ይህንኑ መግለጫ ዋነኛ ማሰረጃ በማድረግ ብፁዕ አቡነ ማቲያሰ በደብራችን ተገኝተው ያጸደቁትን ይህንኑ የተሳሳተ የሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ በመቃወም ቅዱሳት መጽሐፍትን በማሰረጃነት ጠቅሰው ማህበረ ካህናቱና ቀሲሰ አሰተርአየ የጻፉትን ጽሑፍ፥ ለመቃወም የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ሆኖም ግን፥ ጸሐፊው በማሕበረ ካህናቱና በቀሲስ አሰተርአየ የቀረቡትን ማሰረጃዎች፥

- *" ዛሬ በአሜሪካ የተነሳው ቄስ ወይም መልአከ ብርሃን አሰተርአየ የተባለ ሰው ይኸንኑ መነሻ አድርጎ ጉባኤ ሰብስቦ ከማጽደቁም በላይ በብዙ ጥቅስ ገብስባሶ እንዲታጀብ አድርጎ ወሳኘን*

*የሊቃውንት ጉባኤ በመክሰስ ወደ ዘመ- ቤተ ክህነት ያቀረበው ጽሑፍ ኮፒ ስለ ደረሰኝና በውስጡም ያለውንም ዝር....ገጽ:፬"*

በማለት: ሀሳብን: በሀሳብ፥ ማስረጃን: በማስረጃ ወድቅ በማድረግ ከማስተማር ይልቅ፥ ዘለፋ የተሞላበትና "ምልጃ፥ እርቅና ሰላም" በሚለው ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፋቸው ላይ እንዳደረጉት: በድጋሚ ስሕተትን በስሕተት ለመደገፍ የተሞከረበት መጽሐፍ ነው። ለዚህም ማስረጃው እንደሚከተለው ነው፥

፩ኛ. ከላይ እንደገለጽኩት: በመጽሐፉ መግቢያ ላይ: በ ፪ኛ ቆሮ. ምዕ. ፩፥ ቁ.፲፪ ላይና በ ፩ኛ. ጴጥ. ምዕ. ፩፥ ከቁ. ፲-፲፪ ላይ ስለ ጌታችንና መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የተነገረውን በማን አለብኝነት አንስተው ስለ እመቤታችን እንደተነገረ አድርጎ በማቅረብ የሰውን ስሜት በተሳሳተ መንገድ ለመኮርኮርና ጥንት የነበራቸውን አቋምና እምነት ቀይረው በስህተት ያጸደቁትን እምነት ለመደገፍ ሲሉ ይህን ማድረጋቸው ተገቢ ያልሆነ ስህተት ነው።

፪ኛ. ከዚህ በመቀጠል በሉቃስ ወንጌል ምዕ. ፩፥ በቁጥ. ፵፮ እና ፵፯ ላይ *"ማርያምም እንዲህ አለች። ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች..."* ብላ እመቤታችን ልጇና አምላኳ መድኃኒቷ እንደሆነ በማያወላውልና በማያሻማ አገላለጽ የመሰከረችውን: ክቡርነታቸው በዚህ መጽሐፍ ላይ እንዲህ ብለው ገልጸውታል፥

- *"አምላኬ ማለትን የወደደ ብቻ ሳይኾን የጠላም ቢኾን በግድ የሚቀበለው ነው። አዳኜ፥ መድኃኒቴ ማለትን ግን የሚናገረው የተደረገለትን ያወቀ፥ ያመነ ነው። ለዚኽ ነው፤ በአምላኬ በመድኃኒቴ ልቦናየ ደስ ይላታል ያለች። አምላኬ ስትል ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ መፍጠሩን ብቻ ሳይኾን፤ ጎረያ እግዚአብሔር ለጽዮን ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ።" "እግዚአብሔር ጽዮንን መረጣት፤ ማደሪያው ልትኾን መረጣት፤" እንዲል (መዝ፤ ፻፴፩: ፲፫።) እናቱ ልትኾን ከፍጥረት ኹሉ በላይ ለኾነ ክብር እንደ ፈጠራት፤ ስለዚኽም በተፈጥሮ ከሚመጣው ግዴታ ኹሉ እንዳዳናት፥ እንደ ጠበቃት፤ ይኸም የማይለወጥ መኾኑን ዐውቃለች። ስለዚኽም፤ "ልቡናዬ በአምላኬ በመድኀኒቴ ደስ ይላታል፥" አለች።" ገጽ፥፭*

ይህ ከላይ ክቡርነታቸው የሰጡትን ማብራርያ አንድ በአንድ እንመልከተው፥

- *"አምላኬ ማለትን የወደደ ብቻ ሳይኾን የጠላም ቢኾን በግድ የሚቀበለው ነው። አዳኜ፥ መድኃኒቴ ማለትን ግን የሚናገረው የተደረገለትን ያወቀ፥ ያመነ ነው። ለዚኽ ነው፤ በአምላኬ በመድኃኒቴ ልቦናየ ደስ ይላታል ያለች።*

እመቤታችን ጌታችንን እስከፀነሰችበት ሰአት ድረስ ብላ የማታውቀውን *"በአምላኬ በመድኃኒቴ ልቦናየ ደስ ይላታል"* ብላ በሙሉ ልብ ጌታችንን ከፀነሰች በኃላ የተናገረችበት ምክንያት: የአምላክ እናት ለመሆን በመብቃቷና፥ ከአዳም ዘር የተገኘች ሙሉ የሰው ዘር ሁና በመፈጠሯ: እንደማንኛውም የሰው ዘር ሁሉ: ቁራኝነት፥ የአዳም የውርስ ኃጢአት ሰለነበረባት: ለዚህም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሲያበሰራትና: እሷም እንደቃልኽ ይሁንልኝ ብላ ፈቃዷን ለአምላኳና ለፈጣሪዋ ሰታሰገዛ፥ መንፈስ ቅዱስ ከቁራኝነት እንዳነፃት ተረድታ መዳኗን በመመሰከሯ ብቻ ነው። ምክንያቱም፥

- እመቤታችን ገና በእናቷ በሐና መሐፀን ከአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ከቁራኝነት ተጠብቃ ተፀነሰች ከተባለ፥ በራሷ የሰራችውም ሆነ ያሰበችው ኃጢአት ሰለሌለባት: ከምን መዳን ኖሮባት ነው *በአምላኬ በመድኃኒቴ* ልትል ያስፈለጋት?።

- ከላይ ክቡርነታቸው *"አዳኜ፥ መድኃኒቴ ማለትን ግን የሚናገረው የተደረገለትን ያወቀ፥ ያመነ ነው።"* ብለዋል። አዎ ይኽ አባባል ትክክል ነው። ሆኖም ግን፥ ከዚህ አባባል የምንረዳው: እመቤታችን *በአምላኬ በመድኃኒቴ ልቦናየ ደስ ይላታል* ብላ የተደረገላትን ለመመሰከር የበቃችው: ሥላሴ፥ በመሐፀኗ ያከናወኑትን ታላቅ እጹብ ድንቅ ሥራ: ማለትም: አብ አጽንቷት፥ መንፈስ ቅዱስ አንጽቷት ወልድ ከሥጋዋ ሥጋ: ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በመሐፀኗ ከተፀነሰ በኋላ ነው። ለዚህም ማስረጃው በዙ ሳንርቅ ከላይ በሰፊው ማብራሪያ የሰጠሁባቸው፥

እራሳቸው ክቡርነታቸው የጻፏቸው የሚከተሉ መጽሐፋቶቻቸው ናቸው።

- የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት በሚለው ላይ በገጽ: ፪፻፫
- ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ በሚለው ላይ በገጽ: ፳፺-፳፰
- ምልጃ፣ እርቅና ሰላም በሚለው ላይ በገጽ: ፶፫

ከዚህ በመቀጠል፥

- *" እግዚአብሔር ጽዮንን መረጣት፤ ማደሪያው ልትኾን መረጣት፤" እንዲል (መዝ፤ ፻፴፩: ፲፫።) እናቱ ልትኾን ከፍጥረት ኹሉ በላይ ለኾነ ክብር እንደ ፈጠራት፤ ሰለዚኽም በተፈጥሮ ከሚመጣው ግዴታ ኹሉ እንዳዳናት፥ እንደ ጠበቃት፤ ይኽም የማይለወጥ መኾኑን ዐውቃለች። ሰለዚኽም፤ "ልቡናዬ በአምላኬ በመድኀኒቴ ደስ ይላታል፤" አለች።"* ብለዋል።

ይህ አባባላቸው *"በተፈጥሮ ከሚመጣው ግዴታ ኹሉ እንዳዳናት"* ከመትለዋ ሐረግ በሰተቀር ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው። አዎ! እመቤታችን በሴቶቸ ላይ ከሚመጣው ከማንኛውም የተፈጠሮ ግዴታ ተጠብቃለች፥ ሰው ከመሆን የተነሳ ከሚሠራና ከሚታሰብ ከማንኛውም ኃጢአት ተጠብቃለች። ሆኖም ግን የአዳም ዘር ሰው በመኾኗ፥ አዳም ከበደለ በኃላ በሥጋ መሞት ከክርሰቶስ በቀር ለሰው ሁሉ ግዴታ በመሆኑ፥ እመቤታችንም ብትኾን ከዚህ ግዳጅ ሳታመልጥ፥ ይህንን አለም በተወለደች በ፷፬ አመቷ ለጊዜውም ቢሆን በሞት ተለይታለች።

፪ኛ. በዚሁ መጽሐፍ በገጽ: ፺ ላይ፥ በሙሴና በሰለሞን ዘመን በድንኳኑ ውሰጥ ለታቦት ማደርያ ተለይታ ቅድስተ ቅዱሳን ተብላ የምትጠራው ክፍል የእመቤታችን ምሳሌ እንደሆነች በሚገባ ገልጸዋል። ሆኖም ግን ቀጠል አድርገው: እመቤታችን የአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ቁራኝነት አልደረሰባትም የሚለውን የተሳሳተ አቋማቸውንና እምነታቸውን እንዲደግፍላቸው፥

- *"ሙሴ ድንኳኑን ሲተክል፤ ደብተራ ኦሪትን አንጻት፥ ቀባት፥ ቀደሳት ይላል። ዘፀ: ፵። ርኩሰት ነበረባት ማለት አይደለም። ለያት፥ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት አከበራት ማለት ነው: በዚያው አንጻር በሰለሞን ቤተ መቅደሰ: አንጻት ቀደሳት እየተባለ የተነገረው ፩ ነገ: ፰፥፮-፲፩። በእግዚአብሔር ስም ለእግዚአብሔር ክብር አከበራት ማለት ነው።"* ብለዋል።

ይህ ከላይ *"ደብተራ ኦሪትን አንጻት"* የሚለው ሐረግ በ*ዘፀ: ፵* ላይም ሆነ በ*፩ ነገ: ፰፥፮-፲፩* ላይ *ደብተራ ኦሪትን ቀባት፥ ቀደሳት* ከሚል በቀር *አንጻት* የሚል ቃል እንደሌለ እየታወቀ: በማን አለብኝነት እንዳለ አድርገው ለመግለጽ ሞክረዋል። በመጀመርያውኑ *ደብተራ ኦሪትን አንጻት* የሚል አባባል ሊኖርም አይችልም። ምክንያቱም፥ድንኳኑ ለታቦቱ ማደርያ ብቻ እንዲሆን ተቀድሶና ተቀብቶ ተለየ እንጂ፥ ግዑዝ የኾነ ድንኳን፥ ኃጢአትም ሆነ ርኩሰት ያለበት ይመሰል መንጻት አያሰፈልገውምና። ሆኖም ግን አባቶች ጎዶሎ ምሳሌ ቢሆንም ለንጽጽር ሲሉ፥ በድንኳኑ ውሰጥ ለታቦት ማደርያ ተለይታ ቅድስተ ቅዱሳን ተብላ የምትጠራውን ክፍል የእመቤታችን ምሳሌ ሆና ያቀረቡትን አጋጣሚ በመጠቀም ክቡርነታቸው: ከዚህ በፊት ቅዱስ ያሬድ "አንጽሖ ሥጋሃ..." የእመቤታችንን ሥጋዋን አንጽቶ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሰቶ እንደተዋሐደ የተናገረውን እውነተኛና ቀጥተኛ አባባል ጠምዝዘው: አንጽቶ ማለቱ ንጹሕ ማለቱ ነው ብለው ለማሳመን እንደሞከሩት ኹሉ፥ አኹንም፥ *"ሙሴ ድንኳኑን ሲተክል፤ ደብተራ ኦሪትን አንጻት፥ ቀባት፥ ቀደሳት ይላል። ዘፀ: ፵። ርኩሰት ነበረባት ማለት አይደለም። ለያት፥ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት አከበራት ማለት ነው:"* በማለት ለማሳመን መሞከራቸው ትክክል አይደለም።

፫ኛ. ከዚህ በመቀጠል እመቤታችን የአዳም ዘር ሰው በመኾኗ: በሞት ጥላ ሰር ሰለነበረች ይህንን አለም በሞት መለየቷ ከአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ከቁራኝነት፥ ከጥንተ አብሶ እንዳላመለጠች አንዱና ዋነኛው ማረጋገጫ ነው የሚለውን ትክክለኛ እውነታ ሲነቅፉና ሲቃወሙ፥

- *"ሰው ተፈጥሮው ከመሬት በመኾኑ ሞት የሚሰማማው ኾኖ ነው የተፈጠረ። ግን ባይበድል ግዳጅ አይኾንም ነበር። ከበደለ በኋላ ግን ግዳጅ ኾኖአል። ይኽም ሞተ ሥጋ ነው። ይኽ ሞተ ሥጋ ጌታ ከሷ ሥጋን ነስቶ በተቀበለው መከራ ድል ተነሥቶአል። ትንሣኤና የዘላለም ሕይወት ለሰው ኹሉ ተሰጥቶአል። ለዚኽ የቤዛነት ሥራ መሠረቱ እሷ ነች። ገጽ: ፲"*

ሲሉ፤ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከጥንቱ ሲፈጥረው የነበረውን እቅዱን በመሻር፥ የተሳሳተ እምነታቸውን ለመደገፍ ሲሉ የራሳቸውን ግንዛቤ ተክተውበታል። ይህ በጣም አሳዛኝና ትልቅ ሰህተት ነው። ምክንያቱም፥

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከመጀመርያውኑ በአምሳሉ ሲፈጥረው: ዘላለማዊ ሁኖ እንዲኖር እንጂ እንዲሞት አልፈጠረውም። ሆኖም ግን እግዚአብሔር የፈቃድ አምላክ ነውና: አዳምን ፈጥሮ በዔድን ገነት ሲያኖረው ከትእዛዝ ጋር ነበር። ይኸውም ትእዛዝ፥

- *"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው። ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።ዘፍ. ፪፥ ፲፮-፲፯"*

ብሎ እግዚአብሔር አዳም የፈጣሪውን ትእዛዝ በሚያፈርስባት ቅጽበት፥ ሞት፥ ማለትም (የሥጋ፥ ሞት፥ የነፍስ ሞት) እንደሚታወጅበት የወደፊት ቅጣቱን ነገረው እንጂ፥ ክቡርነታቸው እንዳሉት፥ እግዚአብሔር የአዳም *" ተፈጥሮው ከመሬት በመኾኑ ሞት የሚሰማማው ኾኖ ነው የተፈጠረ"* ብሎ ያለበት ቦታ ፈጽሞ የለም ሊኖርምም አይቻልም። ምክንያቱም፥ ይኸ ቢሆን ኖሮማ፥ አዳም ከመበደሉ በፊት የፈጣሪው ፀጋ ከእርሱ እደተለየ፥ እርቃኑን መቅረቱንና፥ ለዲያቢሎሰ መጋለጡን ባወቀ ነበር። ይህ ባለመሆኑ ነው፥ አዳም እንደበደለ ያኔውኑ ዘላለማዊ ኾኖ የተፈጠረው ባሕሪው በሞት፥ እንደተተካ ያወቀው እንጂ እግዚአብሔር መጥቶ እሰኪነግረውም አልጠበቀም። ምክንያቱም፥ አዳም የፈጣሪውን ትእዛዝ አፍርሶ አትብላ የተባለውን እፀ በለስ እንደበላ ሲፈጠር የነበረው የእግዚአብሔር ክብር ከላዩ ላይ ተገፈፈ። በነፃነት በዔድን ገነት ይመላለሰ የነበረ አዳም እራቁቱን እንደሆነ አወቀ በአፍረት ተጨማደደ። የእግዚአብሔር ክብርና ፍቅር ከእርሱ እንደተለየ እግዚአብሔር ሳይነግረው ህሊናው አወቀ፥ ሰለዚህም ከፈጣሪው ፊት እራሱን በተሳሳተባት ቅጠል ሊደብቅ ሞከረ። ፈጣሪው ግን፥ የለም፥ በቅጠል ሳይኾን የምትደበቀው፥ በለበሰከው አፈር ለዘላለም ትሸፈናለህ ወደመጣኽባት ትመለሳለህ ሲል፥

- *"አዳምንም አለው። የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና። ዘፍ. ፫፥ ፲፯-፲፱"*

በመቀጠልም፥ አዳም ከመበደሉ በፊት: ከፈጣሪው ሰልጣንና ፈቃድ ውጭ፥ እራሱ በሰልጣኑ ባልፈጠረው ሥጋውና ነፍሱ ላይ: እራሱ በመረጠበት ጊዜ: ሞትን በራሱ ላይ ማወጅ እንደሚችል አድርገው፥ *"ሰው ተፈጥሮው ከመሬት በመኾኑ ሞት የሚሰማማው ኾኖ ነው የተፈጠረ። ግን ባይበድል ግዳጅ አይኾንም ነበር።* ብለዋል። ይኸ አባባላቸው፥ ከላይ: አዳም ከመበደሉ በፊት የነበረው ሰብአዊ ተፈጥሮው: በሥጋው የመሞት ባሕሪ እንደነበረበት አድርገው ለማቅረብ የሞከሩት ሰሕተት አልፎ፥ እንዲህ ማለት ደግሞ: የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሰልጣን ለአዳም መሰጠት ይኾናል። ይህ ደግሞ ትልቅ ሰሕተት ብቻ ሳይኾን፥ ኃጢአትም ነው።

ከዚህ በመቀጠል *"ይኸ ሞተ ሥጋ ጌታ ከሷ ሥጋን ነስቶ በተቀበለው መከራ ድል ተነሥቶአል። ትንሣኤና የዘላለም ሕይወት ለሰው ኹሉ ተሰጥቶአል።* ብለዋል። አዎ! የጌታችንና የመድኃኒታችን የእየሱሰ ክርስቶሰን አዳኝነትና አምላክነትን ላመን፥ ለተጠመቅን ክርስቲያኖች፥ በአዳም በደል ምክንያት ያጣነውን ዘላለማዊነት እንደገና ለመቀዳጀት እድሉ ተሰጥቶናል። ሆኖም ግን፥ ለክርስቲያን፥ ለዚህ ዘላለማዊና ሰማያዊ ሕይወት ለመብቃት: መጀመርያ በጊዚያዊ ሞት ማለፍ አለብን። እዚህ ላይ ሁላችንም ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር፥ የነፍስና የሥጋ በሞት መለያየት ለዘላለምም ይሁን ለጊዜው፥ የተጀመረው በአዳም በደል ምክንያት ነው። ሰለሆነም፥ የአዳም ዘር የኾነ ኹሉ: ከአዳም የውርስ ኃጢአት የተነሳ በሞት ይኸችን ዓለም ይለቃል። ይኸም በመኾኑ፥ እመቤታችንም ሞትን ለአጭር ጊዜም ቢኾን ቀምሳለች።

ከዚህ በመቀጠል: ክቡርነታቸው የያዙትን አቋምና እምነት አጠንቅረው ለመገለጽ ሲሉ፣ በራሱ ፈቃድ ከሰማይ ወርዶ፣ እራሱ ከፈጠራት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሰቶ በተዋሐደው ሰውነቱ፣ በቀራንዮ መሰቀል ላይ እራሱ ብቻ በከፈለው ካሳ ያዳነንን ብቸኛ አምላክ ትተው: *ለዚኽ የቤዛነት ሥራ መሠረቱ እሷ ነች።"* ማለታቸው ክርስትናን የሚያፋልስ ትልቅ ስህተትና ድፍረት ነው። ምክንያቱም፣ እመቤታችን መሰረት ከሆነች፣ ጌታችን ጣራና ግድግዳ ሊኾን ነው ማለት ነዋ?

የኦርቶዶክስ ክርስትና መምሕር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ: ስለ እመቤታችን ሲናገር: ከወንጌሉ ላለመውጣት: የነበራትንም ፍጹም እምነትና ምሳሌነቷን ለመግለጽ ሲል፣

- *"እንደ እኔስ በዘር በሩካቤ ተወልዶ ቢሆን ብዙ ሰዎች ዕሩቅ ብእሲ ባሉት ነበር: አምላክነቱንም በካዱት ነበር። እንዲህስ እንዳይሉት ከድንግል ተወለደ: በወለደችውም ጊዜ ድንግልናዋንም ያለመለወጥ አጸና ድንቅ በሚሆን ፅንሷ ለደገኛው ሃይማኖት መሪ ትሆን ዘንድ። (ሃይ. አበው: ፷፯:፴፪)"*

በማለት: ለሃይማኖቱ መሪነቷንና ስለእምነቷ ፍጹም ጥንካሬ፣ ቅድስት ኤልሳቤጥ *"ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና የምታምን ብፅእት ናት"(ሉቃስ ፩፥፵፭)* እያለች የተናገረችውን መሠረት በማድረግ ተናገረ እንጂ የድኅነታችን መሠረት እመቤታችን ናት ፈጽሞ አላለም:: ይህንንም የቅድስት ኤልሳቤጥን አባባል: እራሷ እመቤታችን፣ *"መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤ የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፣ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው...።ሉቃ. ፩፥፵፮-፵፰"* እያለች በሰጠችው ምስክርነት አረጋግጣለች::

ይኸ ብቻ ሳይሆን እዛው ሃይማኖተ አበው ቁጥር ፴፫ ላይ: "...ለቃል ምስክር ከምትሆን ከድንግል በኀቱም ድንግልና መወለዱን ምስክር አድርጌ እናገራላሁ።" ሲል በድጋሚ: የድኅነተ መሰረትነቷን ሳይሆን: ለሃይማኖቱ ምስክረነቷን አስረድቷል። ሆኖም ግን: የሕይወትንና የድኅነትን ነገር በተመለከተ: ሊቁ፣
*"ነገር ግን ሔዋን ዲያቢሎስ አሳታት: የሞት ምክንያት የሚሆን ቃየልን ወለደች: ማርያም ግን መልአክ በአበሠራት ጊዜ ሁሉን ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚመራ አካላዊ ቃልን በሥጋ ወለደች። (ሃይ. አበው ፷፯:፲)"*

በማለት፣ የቤዛነቱን ሥራ መሠረትነቱን ለፈጠራትና ለወለደችው ለጌታችን ሰጠ እንጂ፣ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው እንዳሉት ለእመቤታችን አልሰጠም። ጌታችንም ቢሆን፣ *"እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ... ዮሐ ፲፬:፮"* ሲል ደምድሞታል።

አዎ! እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም: ንጽሕት፣ ብጽዕት እግዚአብሔር አምላክ እናቱ እንድትሆን ከሴቶች ሁሉ የመረጣት፣ ያከበራት፣ ከፍጡራን ሁሉ በላይ፣ ነገር ግን ከፈጣሪ በታች የሆነች፣ አማላጃችን ስትኾን፤ ከዚህ አልፎ ግን: ለጥጦና ፈጥሮ፣ እንደ ሮማ ካቶሊክ ቤ/ክር: እሷ ከሰማይ የወረደች ናት ወደ ማለትና ወደ አምላክነት ደረጃ ለማሰጠጋት መሞከር፣ እርሷን ማክበር ሳይሆን: ልጇን፣ ፈጣሪዋንና አምላኳን መድፈርና መጋፋት ነው። ለእመቤታችን የአምላክ እናት ከመሆን በላይ ምንም ክብር የለም። ማንም: ከዚህ የበለጠ ክብር ሊሰጣት የሚችል የለምና።

## መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ ነገረ ሃይማኖትን
## <u>በተመለከተ የፈፀሙት ስሕተት</u>

ከዚህ በመቀጠል: ከላይ በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ የተጻፉትን አራት መጽሐፍትና፥ በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. በክቡርነታቸው ሰብሳቢነት ይመራ የነበረው የወቅቱ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክር የሊቃውንት ጉባኤ ወስኖ: ለቅዱስ ሲኖዶሱ ባስተላለፈው መግለጫ መሰረት፥ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክር ታሪክ: በሮማ ካቶሊክ ቤ/ክር ብቻ (Immaculate Conception) በመባል የሚታወቀው ሃይማኖት ጸድቆ ይፋ የሆነበትን ሰነድ በገልጽ ለማሳየት ሞክሬአለው። ከላይ በሚገባ እንዳሳየኹት፥ ክቡርነታቸው እስከ በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. የጻፏቸው ሁለቱ መጽሐፍቶች: በግልጽ ይህንን ኑፋቄ የሚቃረኑ ሲኾኑ፤ በተቃራኒ ደግሞ ከዛ በኋላ የጻፏቸው ሁለቱ መጽሐፍቶች፥ ኑፋቄውን ለመደገፍ ተብሎ በሰህተት ላይ ሰህተት የታከለባቸውና ቀደም ብሎ የጻፏቸውን መጽሐፍቶች መኖራቸውን የሚክድ ነው። ሆኖም ግን: በቀና ልቦናና እውነቱን ለማግኘት በንጹህ አይምሮ ለተመለከተው፥ ሐቁ ይኽ ሆኖ ሳለ: እንዴት ባለፉት ሀያ አመታት ውስጥ፥ ይህ የሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ በሚግርም ፍጥነት ቤተ ክርስቲያኗን ሊያጥለቀልቃት ቻለ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ፥ ተወደደም ተጠላ ከክቡርነታቸው እራስ አይወርድም። ይህንንም ለማለት የቻልኩበት ምክንያት፥

፩ኛ. በጹሕፌ መግቢያ ላይ እንደገለጽኩት፥ ይኽ የነገረ ሃይማኖት ጉዳይ በእኔና በዲያቆን ሳሙኤል ዘርይሑን መካከል ሲነሳ፥ ዲያቆን ሳሙኤል ለያዘው እምነት በመጀመርያ ለምስክርነት የጠራው ብሎም በሰልክ ደውሎ ለማነጋገር የሞከረው ክቡርነታቸውን በመሆኑ።

፪ኛ. ብፁዕ አቡነ ማቲያሰም በደብራችን ተገኝተው ለወሰኑት ውሳኔ ማሰረጃ ብለው ካቀረቧቸው ፭ ማስረጃዎች ፬ቱ ከኦርቶዶክሱ ትምህርትና እምነት ጋር የተጋጩ ጽሑፎቻቸው በመሆናቸው።

፫ኛ. ይህንን የተሳሳተ የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖት በመደገፍ ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. ወዲህ የተጻፉት በዛ ያሉት ጽሑፎች ዋና ማሰረጃ አድርገው የሚያቀርቡት ክቡርነታቸውን በመኾኑ።

፬ኛ. ከልጅነት አንስቶ የሕይወት ዘመናቸውን በቤተክርሰቲያኗ ውስጥ ያሳለፉ፥ መጽሐፍትን አደላድለው የተማሩና ያመሰጠሩ እውነተኛውን አርቶዶክሳዊ ሃይማኖት የሚያሰተምሩትን ሊቃውንቶች ያላግባብ በማውገዝ፥ በማፈንና ሰም በማጠፋት ቤተክርሰቲያኗን ባዶ ወና አድርጎ ለማሰቀረት ዋነኛ መሳርያ የኾነው፥ ይኽ የክቡርነታቸው የተሳሳተ ሰራ በመሆኑና።

፭ኛ. ይህንን ጽሑፍ ለመጻፍ ዋነኛ ምክንያት የኾነኝ፥ የመሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ ጽሑፍ፥ የክቡርነተቸውን ዝና እንጂ፥ የጻፉትን መጽሐፍቶች ምን እንደሚሉ በቅጡ ሳይረዱ፥ በደፈናው ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው እንዲኽ ብለዋል በማለት እየጠቀሱ፥ እሳቸውን ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ወዲህ የነበራቸውን አቋም ለውጠው በስህተት የተኩትን ደግመው በመጻፍ ሕዝብን ለማሳመንና ለማደናገር የሚሞክሩት በቂ ማሰረጃ ነው። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚኾነው: መሪ-ጌታ በመስከረም ፲ እና በኅዳር፲፮ ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በጻፉት ጽሑፍች ላይ ከሰፈሩት ብዙ ሰህተቶች ጥቂቶቹን እንመልከት፥

- *"ቅዱስ ያሬድ ግን ድንግል ማደሪያውን ከጥንተ አበሶ ንጹሕ አድርጎ እንደፈጠራት ሲነግረን አንጺሖ ሥጋሃ ቀዲሶ ኪያሃ ሥጋዋን አንጽቶ እርስዋን ለይቶ አክብሮ አለና ጥንቱን የተመረጠችበትን ፍጻሜ ኃደረ ቃል ላዕሌሃ አካላዊ ቃል ከርሷ ተዋሐደ ካለ በኋላ ሊቁ... ከእርስዋ ሰው የሆነኩባት ድንግልን እኔ እራሴ በእጄ ፈጠርኳት አለ እግዚአብሔር ሲል መንገድ ይዘጋባቸዋል።"* ብለዋል

መሪ-ጌታ፥ መቼም "*አንጺሖ ሥጋሃ*" የምትለዋ የማታስኬድ ቁልፍ ሐረግ፥ እርሰዎም ሆኑ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ፥ ፍቃቹህ ልታጠፏትና ልትክዷት የማትችሉት ሰለሆነችባቹህ: የራሳቹህን የፈጠራ ትርጓሜ በመሰጠት: ሰውን እንደአላዋቂ በመቁጠር ለማሳመን መሞከራቹህ እናንተኑ አሰገመታቹህ። ለመሆኑ እርሰዎ ከላይ " *"ቅዱስ ያሬድ ግን ድንግል ማደሪያውን ከጥንተ*

*አበሶ ንጹሕ አድርጎ እንደፈጠራት ሲነግረን"* ብለው ሊቁ ያላለውን እንዳለ አድርገው የተናገሩት ትልቅ ስህተትና ድፍረት ነው። ምክንያቱም: ቅዱስ ያሬድን ያክል ሊቅ: እንደርሰዎ አባባል *"ከጥንተ አብሶ ንጹሕ አድርጎ ፈጥሯታል ካለ"* በኋላ፥ ከምን መንጻት ቢኖርባት ኖሮ ነው መልሶ "*<u>አንጺሖ ሥጋሃ</u>*" የሚለው??? አያሰኬድም።

በ ኅዳር ፯ ፪ሺ፪ ዓ.ም. በጻፉት ጽሑፍ ላይ በገጽ፥፲፯-፲፰ ላይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በመጽሐፈ አርጋኖን ላይ የጻፉትን አሰመልክቶ ቀሲስ አሰተርአየ የሰጡትን ትክክለኛ ትንታኔ እርሰዎ ሳይገባዎትና ሳይረዱት ቀሲስን ተችተው የርሰዎን የተሳሳተ የፈጠራ ትንታኔ እንደሚከተለው እንዲህ ብለዋል፥

- *"ጸራቅሊጦስ ውእቱ ዘዐቀባ እምከርሠ እማ ከመ እትጌጊ፤ የውርስ ኃጢአት እንዳይተላለፍባት ጸራቅሊጦስ (መንፈስቅዱስ) በእናቷ ማኅፀን ጠበቃት... ከመ እትጌጊ እንዳትበድል ማለቱ፤ ሰው ወዳጅ አምላክ ተሰቅሎ በደልን እስኪያጠፋት ድረስ ሰው ሁሉ በውርስ ኃጢአት ምክንያት በደለኛ ነበር ሮሜ ፭፡ ፲፪-፲፫ ስለዚህ የአዳም በደል ወደእርስዋ ተላልፎ በደለኛ እንዳትሆን መንፈስቅዱስ በእናቷ ማኅፀን ጠበቃት ማለት ነው እንጂ ማንም በእናቱ ማኅፀን እያለ አሰቦ ኃጢአት የሚሠራ እንደሌለ ለሁሉም ግልጽ ነው። እንዳንጠራጠርም አባ ጊዮርጊስ ለይቶ በእናቷ ማኅፀን ጠባቃት በማለት ግልጽ በሆነ ቃለ አስረድቶናል።"* ብለዋል፥

መሪ-ጌታ፥ በመጀመርያ ደረጃ አንድ ጸሐፊ በይበልጥም ካህን የሆነ ሰው: በሌላ ሰው የተጻፈን መጽሐፍ፥ ጽሑፉን ከግእዝ ወደ አማርኛ ሲተረጉም የራሱን ሀሳብና ምኞት ጨምሮ እርሰዎ እንዳደረጉት መተርጎም የለበትም። ይህ ድርጊት የርሰዎን እውነተኛነት ገና ከመጀመርያው ጥያቄ ላይ ይጥለዋል። ይህን ያልኩበት ምክንያት ከላይ አባ ጊዮርጊስ፥ *"ጸራቅሊጦስ ውእቱ ዘዐቀባ እምከርሠ እማ ከመ እትጌጊ፤..."* ማለትም፥ "ጸራቅሊጦስ (መንፈስቅዱስ) በናቷ ማኅፀን እንዳትበድል ጠበቃት፥.." የሚለውን፥ እርሰዎ በማን አለብኝነት ያልተባለውን ነገር ግን በልብዎ እንዲል የሚፈልጉትን ጨምረው ፥*"የውርስ ኃጢአት እንዳይተላለፍባት ጸራቅሊጦስ (መንፈስቅዱስ) በእናቷ ማኅፀን ጠበቃት..."* ብለዋል።

ቀጥለውም፥

- "ከመ እትጌጊ እንዳትበድል ማለቱ፤ ሰው ወዳጅ አምላክ ተሰቅሎ በደልን እስኪያጠፋት ድረስ ሰው ሁሉ በውርስ ኃጢአት ምክንያት በደለኛ ነበር ሮሜ ፭፡ ፲፪-፲፫ ስለዚህ የአዳም በደል ወደእርስዋ ተላልፎ በደለኛ እንዳትሆን መንፈስቅዱስ በእናቷ ማኅፀን ጠበቃት ማለት ነው እንጂ ማንም በእናቱ ማኅፀን እያለ አሰቦ ኃጢአት የሚሠራ እንደሌለ ለሁሉም ግልጽ ነው።"

ብለው እማይወጡበት ግዙፍ ስሕተት ውስጥ ወደቁ። ምክንያቱም፥

- *ሮሜ ፭፡ ፲፪-፲፫ የሚናገረው "ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም"* ሲል ቅዱስ ጳውሎስ በአባታችን አዳም በደል (ኃጢአት) ምክንያት ሞት በሰው ልጆች ላይ ሁሉ የማይቀር እዳ፥ ቀንበር መሆኑን ተናገረ እንጂ፥ እርሰዎ ከላይ እንደልማደዎ አጣመው፥ *"ሰው ሁሉ በውርስ ኃጢአት ምክንያት በደለኛ ነበር ሮሜ ፭፥ ፲፪-፲፫"* ብለው ሰውን ለማደናገር እንደሞከሩት አይደለም። እንደርሰዎ አባባል ከሆነ፥ የሰው ልጅ ሁሉ ሲወለድ፥ ኃጢአተኛ ሆኖ ነው የሚወለደው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ኦርቶዶክሶች የነቀፉት የተሳሳተ የሮማ ካቶሊኩ የAugustine ፍልስፍና ነው።

- በሌላ በኩል ደግሞ *ከመ እትጌጊ እንዳትበድል ማለቱ፤... የአዳም በደል ወደእርስዋ ተላልፎ በደለኛ እንዳትሆን መንፈስቅዱስ በእናቷ ማኅፀን ጠበቃት ማለት ነው..."* ካሉ ደግሞ: እንደርሰዎ አባባል: እመቤታችንን መንፈስ ቅዱስ በእናቷ ማኅፀን እንዳትበድል (ከጥንተ አብሶ) ጠበቃት ከተባለ፥ የሰው ልጅ በእናቱ ማኅፀን እያለና ተወልዶ በኅጻንነት ዘመኑ አስቦም ሆነ ሳያስብ ኃጢአት አይሰራምም፥ አይበድልምም። ሰለዚህ፥ እነዚህም ህጻናት

አድገው አይምሯቸው በደልና ኃጢአትን ማሰተናገድ እስኪጀምር ድረስ፣ ከአዳም የውርስ ኃጢአት፣ ከጥንተ አብሶ ለጊዜው ተጠብቀው ሲያድጉ እንደ ጉንፋን ሊይዛቸው ነው ማለት ነዋ?? ይህ ፈጽሞ ስህተት ነው። ምክንያቱም ህጻናትም የአዳም ዘር በመሆናቸው ከውርስ ኃጢአት፣ ከቁራኝነት የተነሳ፡ እንኳን ተወልደው፣ ሳይወለዱም በእናታቸው ማኅፀን እያሉ በሞት ይቀሰፋሉ። ዳሩ ግን በእርሰዎ አይፈረድም፣ ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩም፣"*እንግዲህ የውርስ ኃጢአት ሕፃናትም እንኳ ቢሆኑም የሌለባቸው መሆኑን ማንም ሊገነዘበው ይገባል።*" ብለው ጽፈው የለ!!!!!

- ሆኖም ግን እውነቱን ለመረዳት ለፈለገ ሰው፣"*ጸራቅሊጦስ ውእቱ ዘዐቀባ እምከርሠ እማ ከመ እትጌጊ*" ማለት፣ እመቤታችን እንደ ማንኛውም ህጻን ተወልዳ አድጋ የህፃንነት ጊዜዋን ጨርሳ አይምሮዋም ሆነ ሥጋዋ፣ እንደሌሎቻችን የሰው ፍጡሮች ሁሉ፡ ኃጢአትን ለማሰተናገድ በሚደርስበት ወቅት፣ ከሰው ሁሉ ተለይታ ከማንኛውም ኃጢአት እንድትጠበቅ መንፈስ ቅዱስ በናቷ ማኅፀን ጠብቃት ለዚህ አዘጋጃት ማለት ነው። ከዚህ አልፎ አባ ጊዮርጊስ ያላሉትን ፈጥሮና ጨማምሮ መጻፍ ስሕተት ነው።

በመቀጠልም በመሰከረም ፲ ፪ሺ፺፪ ዓ.ም. በጻፉት ላይ "ዕረፍተ ሶልያና" በሚለው ንዑስ ርእስ ሰር እንዲህ ብለዋል፣

- *አሜሪካ የካንሳስ ደብረሣህል መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን "እመቤታችን ቅድስት ማርያም የሞተችው የውርስ ኃጢአት ሰላለባት ነው" ብለው አባ ሺኖዳ መስክረውልናል የሚል ባወጡት መግለጫ አሰቀምጠዋል። በመግቢያው እንደተገለገረው አባ ሺኖዳ ያመኑብትንና የመሳላቸውን መናገር መብታቸው ነው። በኢትዮጵያዊያን ዘንድ ግን ተቀባይነተ አይኖረውም። ...."*

መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ፣ ያለዎትን ክህነት፣ ማዕረግና ብሎም ሐላፊነት በውል ቢረዱት ኖሮ፣

- ከ አንድ መቶ በላይ ኦርቶዶክሳዊ የሃይማኖት መጽሐፍትን የጻፉ፣
- ፓትርያርክ ሆነው ቢሾሙም እንኳ፣ እስካሁን ድረስ: በየሳምንቱ ለ ፫ ቀናት በገዳም ውሰጥ ተወሰነው በጸሎትና በንባብ የሚያሳልፉ
- በመላው አለም በመዞር ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን የሚያስተምሩ፣ የሚያሰከበሩና ለሚመጣው ማናቸውም ጥያቄ መልስ የሚሰጡ
- በየሰንበቱ ዘወትር ሳያቋርጡ በብዙ ሺኽ ለሚቆጠሩ ምእመናን ጉባኤ ዘርግተው ወንጌል የሚሰብኩ
- የአኀት አብያተክርሰቲያናት ግንኙነት እንዳይቋረጥ ሌት ተቀን የሚሰሩትን

በአለም ዙርያ ላሉ የተዋሕዶ አማኞች፣ ባያውቁት ነው እንጂ ለእርሰዎም ጭምር፣ አለኝታና መመኪያ የሆኑትን ታላቅ ኦርቶዶክሳዊ አባት፣ በድፍረት መዝለፈዎ፣ በጣም ያሳዝናል።

ቀጥለውም በተራ ቁጥር ፫ ላይ እንዲህ ብለዋል፣

- *የክርስቲያን ሞት፤ ከዚህ በኋላ የምንሞተው ሞትም ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የሞትን ሥልጣን ሽሮ የእኛ ሞት በቁራኝነት ሳይሆን በእደ እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ለእኛ አብነት ለመሆን ክብርት ነፍሱን "አባት ሆይ ነፈሴን አደራ እሰጣለሁ" ሉቃ ፳፫፥፵፮-፵፯ ብሎ የሞትን መንገድ ሰለቀየረው እኛም" ...ወእመሰኬ ተመሰልናሁ በሞቱ ንትመሰሎ በሕይወቱሂ፤ በሞቱ ከመሰልነው በሕይወቱ እንመሰለዋለን ሮሜ ፮፥ ፭ እንዲል ለዘላለም ሕይወት የርሱን ሞት አብነት አድርገን እንሞታለን በትንሳኤውም እንነሳለን እንጂ በጌጋየ አዳም የምንያዝና የምንሞት አይደለንም።*

መሪ-ጌታ፣ የያዙትን ስሕተተ በሌላ ስሕተት እጠግናለሁ ሲሉ: ጭራሹን ነገሩን ሁሉ አበለሻሹት። እግዚአብሔር አምላክ: በአምሳሉ የፈጠረውን ሰው ለማዳን ሲል ብቻ: በለበሰው ሥጋ፣ በገዛ ሥልጣኑ፣ በቀራኒዮ መሰቀል ላይ የኛን ሞት የሞተውን: ለእኛ የሞት አብነተ ለመሆን ሲል ነው ብለው መናገረዎ: ምንኛ ቤተ ክርሰቲያናችን እርቃኗን እንደቀረች ያሳያል። የጌታችን ሞት ለኛ

የሞት አብነት ከሆነ፥ የሕይወት ምሳሌያችን ከቶ ማን ሊኾን ነው??

ቅዱስ ጳውሎስ *"እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ከሙታን ተለይቶ በመነሣት ለሚነሡት ሁሉ በኩር ነው" (ቆላ ፩፥፲፰)* ሲል ያስተማረውን መሠረት በማድረግ፥ ሊቁ ኤጲፋንዮስ ሲያብራራ እንዲህ ብሎ አሰቀምጦታል፥ "

- *ኤልያስ አንድ ምውት አስነሣ፡ ደቀ መዝሙሩ ኤልሳዕም ሁለት ሙታንን አሥነሣ፡ አንዱን ሳይቀበር ሁለተኛውን ከተቀበረ በኋላ ሥጋውን አስነሣ። እነዚህ ሙታን ቢነሡ ኋላ እንደ ሞቱ፡ እነርሱም ኋላ አንድ ሆነው የሚነሡትን ትንሣኤ ዛሬ ተስፋ ያደርጋሉ። ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ግን የሙታን ትንሣኤያቸው በኩር ነው። እንግዲህ ወዲህም ሞት የሌለበትን ትንሣኤ አሰቀድሞ የተነሣ እርሱ ነው፥ ዳግመኛ ሞት አያገኘውም ተብሎ እንደተፃፈ።(ሃይ አበው ፶፯፥ ፬-፭)።*

አባቶቻችን እንዲህ እያሉ ያስተማሩት፥ ክርስቶስ አርዓያነቱ፥ ምሳሌነቱና በኩርነቱ ለሕይወትና ለትንሣኤ ነው እንጂ ለሞት አይደለም:: ቅዱስ ጳውሎስ የጥምቀትን ምሥጢር በጠቀሰበት አንቀጹ፥ በውኀ ጠልቆ መውጣቱን በትንሣኤው ለተገኘው ሕይወት ንጽጽር አቀረበው እንጂ፥ የክርስቶስን ሞት ለኛ ሞት ምሳሌ በማድረግ ማቅረቡ አልነበረም::

- *"እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። ሮሜ ፮፥፩-፬"*

የሚለው ቃል የሚያሳየው በጥምቀታችን ጊዜ በውኀው ውስጥ ገብተን ስንወጣ የምናደርገውን ተግባራዊ ምስክርነትና፥ *"እክህደከ" ብለን ሰይጣንን በመካድ "የሙታንን መነሣት ተስፋ አደርጋለሁ"* ብለን የምንሰጠውን የቃል ምስክርነት ለመግለጽ እንጂ: የክርስቶስን ሞት ምሳሌአችን ለማድረግ አይደለም::

እርሰዎ የተሳሳተ እመነትዎን ለመደገፍ ሲሉ፥ አላግባብ ጥቅሱን ጎርደው በመወሰድ አለቦታው ከተው፥

- *"እኛም" ...ወእመሰኬ ተመሰልናሁ በሞቱ ንትመሰሎ በሕይወቱሂ፤ በሞቱ ከመሰልነው በሕይወቱ እንመሰለዋለን ሮሜ ፮፥ ፭ እንዲል ለዘላለም ሕይወት የርሱን ሞት አብነት አድርገን እንሞታለን በትንሳኤውም እንነሳለን..."*

ማለትዎ ባይገነዘቡት ነው እንጂ: ለሰው ልጅ: የሞት ምክንያቱ አዳም ሲሆን: አብነቱ ደግሞ የልጁ ያአቤል ሞት ነው።

በመቀጠልም በተራ ቁጥር ፬ ላይ ሰለ እመቤታችን ሞት የሚከተለውን ብለዋል፥

- *"የድንግል ሞት ጥንተ አብሶ ከጠፋ፥ ቁራኝነት ከቀረ፤ ሞት ከተሻረ ከ፲፭ ዓመት በኋላ ነው። ከላይ ዘር ዘር ባለ መልኩ እንደተመለከትነው ከሆነ፥ ታዲያ እንዴት ተብሎ ነው ሞትን የሻረውን አምላክ እናተ የአዳም በደል ስላለባት ነው የሞተችው ተብሎ እንኳን ለመናገር ሊታሰብበሰ የሚገባው? ኽረ እናሰተውል ወገኖች። ይሄማ ለኛ ብሎ የሞተውን ሞት ከንቱ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሊወገዝ የሚገባው ታለቅ ስተት ነው።"*

መሪ-ጌታ፥ አሁንም በድጋሚ ስሕተትን በስሕተት ለመደገፍ ሲሉ የባሰ ስሕተት ውስጥ ገቡ። ምክንያቱም፥

- ፩ኛ. እመቤታችኝ የአዳም የውርስ ኃጢአት፥ ቁራኝነት (ጥንተ አብሶ) አልደረሰባትም ሲሉ ቆይተው: አሁን መልሰው ደግሞ፥ *"የድንግል ሞት ጥንተ አብሶ ከጠፋ፥ ቁራኝነት ከቀረ፤ ሞት*

*ከተሻረ ከ፲፭ ዓመት በኋላ ነው።* ብለው ማለትዎ አልተጋጨበዎትምን? ምክንያቱም፥ እመቤታችን የአዳም የውርስ ኃጢአት፥ቁራኘነት ከልደረሰባት: የቁራኘነት በክርስቶሰ ሞት መሻሩ: ከእርሷ ጋር ምን ጉዳይ አለውና?

- ፪ኛ. በሌላ በኩል ደግሞ ይኸ አባባለዎ የሚያመለክተው: እመቤታችን የዳኑቸው እንደሌላው ክርስቲያን ሁሉ ክርስቶስ በመሰቀል ላይ ካሳ ከከፈለ በኋላ ነው ማለተዎ ነው። ይህ ደግሞ ከራስዎ ብቻ ሳይሆን ከሁሉ ጋር የሚያጋጨዎ ነው። በይበልጥም ከራሷ ከእመቤታችን ቃል ጋር ይጋጫል። ምክንያቱም *"ነፍሴ በአምላኬና በመድኃኒቴ..."* ብላ ከቁራኘነት እንዳዳናት ገና እንደፀነሰችው ነው የመሰከረቸው እንጂ እመሰቀል ላይ እስኪወጣ አልጠበቀችምና።

*መሪ-ጌታ፥* ***ታዲያ እንዴት ተብሎ ነው ሞትን የሻረውን አምላክ እናተ የአዳም በደል ስላለባት ነው የሞተችው ተብሎ እንኳን ለመናገር ሊታሰብበሰ የሚገባው?*** ብለው ላሉት፥

እግዚአብሔር ቃል በራሱ፥ በአባቱና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ከሰማየ ሰማይ ወርዶ ሰው የኾነበት ዋነኛ ምክንያት: በአምሳሉ የፈጠረውን ሰው: ለማዳን ሲል እንጂ፥ እመቤታችንን ከአዳም የውርስ ኃጢአት አንጽቶ ለመፍጠር አይደለም። ሆኖም ግን: ዲያቢሎስ በእባብ ሥጋና አንደበት ተሰውሮ: አዳምን ለዘላለማዊ ሞት ሰለዳረገው: ሰው ሆኖ የተፈጠረ ሁሉ: ሞት የተቆራኘው ሥጋ ለባሽ ሆነ። ይህ በመሆኑም: ሞት አሽትቶ የሚይዘው ሆነ። ስለዚህ፥ ክርስቶስም፥ ሞትን ድል ለማድረግ ሞት አሽትቶ የሚጠጋው: ነገር ግን ፈጽሞ ሊይዘው የማይቻለው፥ ከቁራኘነት የተላቀቀ፥ የነጻ የሰው ሰጋ መልበሰ ነበረበት። ስለሆነም፥ ለዚህ ተግባሩ ሲል: ከሴቶች ሁሉ መርጦና ባርኮ ሥጋዋን አንጽቶና ቀድሶ፥ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሰቶ ከእመቤታችን ተወለደ። በ፴፫ ዘመኑ እዳችንን ሊከፍል በቀራንዮ መሰቀል ላይ ተሰቀለ: በ፫ኛውም ቀን ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ።

ጌታችን በመስቀል ላይ ስለሰው ሲል የከፈለው ካሳ ዋና ቁም ነገሩ: አዳም የፈጣሪውን ትእዛዝ አፍርሶ: ፈቃዱን ለዲያቢሎስ በማሰገዛቱ: ያጣውን የእግዚአብሔርን ፀጋና ዘላለማዊነትን: እንደገና በዚች ምድር ላይ ሳይሆን: በሳማያዊው አለም እንዲያገኝ እድሉን ሊሰጠው ሰለወደደ ነው። የክርስቶሰ ሞት የቀየረው፥ በአዳም በደል ምክንያት የሰው ልጅ፥ ይህቺን አሰከፊ አለም በሞት ከተለየ በኋላ፥ በነፍሰና በሥጋው ላይ የታወጀውን አሰከፊ ፍጻሜ፥ ማለትም፥ የሰጋችን ወደ አፈርነት መመለሰንና የነፈሳችን ለዘላለም በዳያቢሎስ መያዝን እንጂ የነፍሰና የሥጋን ጊዚያዊ መለያየት አልቀየረውም። ምክንያቱም፥ አሁንም ቢሆን፥ ሥጋችንና ነፍሳችን ያለ ውድ በግዴታ ለጊዜውም ቢሆን በሞት ይለያያሉና። ይህም ብቻ ሳይሆን፥ በእናታችን በሔዋን ላይ የተጣለው እዳ፥ አሁንም ቢሆን በእናቶቻችን፥ በእህቶቻችንና በሴት ልጆቻችን ላይ እንዳለ ነው አልተለወጠም። በአዳም በደል የተነሳ የተረገመችው መሬት፥ ከበፊቱ በከፋ ሁናቴ እሾህ አሜከላ ማብቀሏን ቀጠለች እንጂ አላቆመችምም። ስለሆነም፥ እመቤታችንም ከአዳም የተገኘች በመኾኗ፥ ለአጭር ጊዜም ቢሆን፥ ይህቺን አለም በሞት አልፋታለች። ይህ ደግሞ ሙሉ ሰው መሆኗንና ክርሰቶስም የሷን ስጋ በመልበሱ ፍጹም ሰው ለመሆኑ ዋነኛ ማሰረጃ ነው።

## በጽሑፍ ለትውልድ እንዲተላለፍ የተቀመጠን እውነታ:
## እንደሌለ አድርጎ ለመካድ የተሞከረ ሙከራ

በጣም የሚያሳዝነውና ማንኛውም የኢ.ኦ.ተ. አማኝ ነኝ፥ ሰለእምነቱ ይገደኛል ያለ ሁሉ: ሊያሰብበትና መፍትሔ ሊፈልግለት የሚገባው ነገር ቢኖር፥ ብፁዕ አቡነ ማቲያሰ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. በ(Ref.No. 492/97) ለኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት በላኩት ደብዳቤ: በገጽ: ፱ ላይ ያሰፈሩት ቃል ነው። ይኼውም እንዲህ ይላል፥

- "በመሠረቱ እነ ቀሲስ አስተርአየ ድንግል ማርያም የውርስ ኃጢአት ነበረባት ለሚሉት አባባላቸው እንደ ማስረጃዎች አድረገው ካቀረቧቸው መጻሕፍት ከፊሎቹ" መድሎተ አሚን፤ ኮኩሐ ሃይማኖት፤ የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት፤ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ" እንደሆኑ ጠቅሰዋል። በእነዚህ በተጠቀሱት ማጻሕፍት ውስጥ የእነሱን አባባል የሚደግፉ አንዳንድ አንቀጾች ቢኖሩም ባይኖሩም ቁም ነገሩ፥ ፩ኛ. የወንጌላዊው የቅዱስ ሉቃስ ምሥክርነት ከሁሉም የሚበልጥ መሆኑን። ፪ኛ. የቤተ ክርስቲያን ርዕስ በሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ የጸደቀው የነገረ ሃይማኖት መጽሐፍ በቋሚነት የሚጠቀስ መሆኑን። ፫ኛ. በሞት የተለዩት ሊቃውንት በሊቃውንት የተተኩ መሆናቸው። ፬ኛ. በሕይወት ያሉትም የቀድሞዎቹን ጽሑፎች የሚተኩ ሌሎችን ማጻሕፍት ጽፈው ያበረከቱ መሆናቸውን መረዳት እጅግ አሰፈላጊ ይመሰለናል።" ሙሉ ደብዳቤውን ለማየት (www.medhanialemeotcks.org ) ለቅዱስ ሲኖዶሱ የተላከው ሰነድ ውስጥ ይመልከቱ።

አንባቢ ሆይ!!! የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክ ልጅ ነኝ፥ አማኝ ነኝ ለሚል ለማንኛውም ሰው: ከዚህ የበለጠ ሞት፥ የሞት ሞት የለም። ምክንያቱም፥ ሃይማኖቱን ጠብቀው ለማስጠበቅ በቦታው ላይ የተሰየሙት ብፁዕነታቸው: ከላይ በጠቀሰኩት ቃላቸው: በይበልጥም በተራ ቁጥር ፫ እና ፬ ላይ እንደነገሩን፥ እንደ መድሎተ አሚን፤ ኮኩሐ ሃይማኖትና ባዛ ያሉ የሃይማኖት ማስተማርያና መጠበቂያ መጽሐፍትን ለተተኪው ትውልደ ያበረከቱት: ታላላቅ የቤተክርስቲያኗ ሊቃውንቶች እንደነ፥ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፥ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስና ሌሎችም: ሞተዋልና: በሕይወት እያሉ ከአባቶቻቸው የተቀበሉትን፥ የማይሻር፥ የማይለወጥና የማይተካ የቤተክርስቲያኗም እምነት የሆነውን ነገረ ሃይማኖት፥ መስክረው ያረጋገጡባቸው መጽሐፍትም: አበረው እነደተቀበሩና እንደማይረቡ "*__በሞት የተለዩት ሊቃውንት በሊቃውንት የተተኩ መሆናቸው በማለት"__* የአባቶቻችን እምነት ተክዶ: በእነ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ መሰል የዘመኑ ሊቃውንቶች እየጸደቀ በሚሰበከው በሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ መተካቱን እውነቱንና ሐቁን ቁርጥ አድረገው ነግረውናል። "

ይህ ብቻ ሳይሆን፥ ቀደም አድርጌ በጽሑፌ ላይ: ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ: እመቤታችንን አሰመልክቶ: ስለ አዳም የውርስ ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) የነበራቸውን ኦርቶዶክሳዊ እምነት በሮማ ካቶሊኩ ኑፋቄ መተካታቸውን: እራሳቸው በጻፏቸው መጽሐፍት ማሰረጃነት: በሚገባ አሳይቻለሁ። የእውነተኞቹ ኦርቶዶክሳዊያን አባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን፥ ይኸው ዛሬ ብፁዕ አቡነ ማቲያስ ከላይ በጠቀስኩት ቃላቸው፥ በተራ ቁጥር ፬ላይ፥ *"በሕይወት ያሉትም __የቀድሞዎቹን ጽሑፎች የሚተኩ ሌሎችን ማጻሕፍት ጽፈው ያበረከቱ መሆናቸውን መረዳት እጅግ__ አሰፈላጊ ይመሰለናል።"* ብለው በድጋሚ: የአባቶቻችን እምነት ተክዶ: በሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ መተካቱንና ክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩም ቢሆን የካቶሊኩን ኑፋቄ አጽድቀው የቀድሞ እምነታቸውን የሚመሰክሩትን "<u>የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት፤ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ"</u> የተባሉትን መጽሐፍቶቻቸውን የሚቃረኑ እንደ "ምልጃ፥ እርቅና ሰላም" የመሳሰሉ መጽሐፍትን እንደጻፉ ብፁዕነታቸው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

አንባቢ ሆይ!!! እንግዲህ፥ ክቡር ሊቀጠበብት አያሌው ታምሩ: በሚያሳዝን ሁኔታ እምነቱን እንዳፋለሱት፥ በግልጽ እየታየ: እምነቱን ሊጠብቁ በቦታው የተሰየሙት ብፁዐን አባቶች፥ ይኸ <u>እንዴት ሊሆን ይችላል ብለው እንዴት ጥያቄ አላቀረቡም??? ቅዱስ ሲኖዶሱስ ቢሆን፥ "በእንቅርት</u>

ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ"፥ ሃይማኖቱ ታፋላስ፥ ኧረ ቶሎ ድረሱለት ተብሎ አቤቱታ ቢላክላቸው፡ ዝም ጭጭ በማለታቸው፥ ይኼው ዛሬ ደግሞ *"በሞት የተለዩት ሊቃውንት፡ በሊቃውንት የተተኩ መሆናቸውን መረዳት እጅግ አሰፈላጊ ይመሰለናል።"* ተብሎ የአባቶቻቸው ሃይማኖትና ድካም፡ ዛሬ ዋጋ እንደሌለው እንዲያውቁት፡ በአድራሻቸው ደብዳቤ ተላከላቸው። ይኸንንም፥ የክቡር ሊቀ ጠበብትን የአቋም ለውጥ፥ የብፁዕ፥ አቡነ ማቲያስን ምስክርነትና የቅዱስ ሲኖዶሱን ደካማነት የተመለከተ፡ ከሰንበት ተማሪ እሰከ መሪ-ጌታ ያለው ሁሉ፡ የነሱን ስህተት አብነት አድርጎ በሞቱትም ሆነ አሁን በሕይወት ባሉት መምህራንና ሊቃውንት ላይ በማን አለብኝነት የስም ማጥፋቱን ዘመቻ እያፋፋመ ነው።

ለዚህም ተጨባጭ ማሰረጃው፡ መሪጌታ ገ/ሥላሴ በጽሑፋቸው፥ የግብጽን ቤተ ክርስቲያን ሥላሴን ክዳለች ከማለት አልፎ፡ ቅዱስ ፓትርያርኩን አቡነ ሽኑዳን ለመዝለፍ መሞከራቸው አንዱና ዋነኛው ነው። የሚገርመውና የሚደንቀው ግን፡ የያዙትን የሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ የሚነቅፍና ትክክለኛውን የተዋሕዶ ሃይማኖት የሚያሳየውን፥ "መድሎተ አሚን" የተባለውን መጽሐፍ፥ ቀሲስ አስተርአየ፥ በጽሑፋቸው ላይ ለማሰረጃነት ቢያቀርቡት፥ መሪጌታ ገ/ሥላሴ በሚያሳዝን ሁኔታ፡ የሚከተለውን ሐሰት፥ ኅዳር ፮ ፪ሺ፪ ዓ.ም. በጻፉት ጽሑፍ፡ በገጽ፡ ፳፫ ላይ የሚከተለውን ብለዋል፥

*" ሊቀ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ የኖሩት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሲሆን መላ ዘመናቸውን ለቅድስት ቤተክርሰቲያን አሰረክበው ላሚጻረራት መናፍቅ (እንደነ ዘመንፈስ ላሉት) ሁሉ ተገቢውን በመስጠት የእናት ቤተክርስቲያንን እምነትዋንም ሆነ ባሕሏን አሰጠብቀው የኖሩ ስለሆነ ሰለእርሳቸው ብሒልና እምነት በሁሉ ዘንድ ያታወቀ ነውና በየትኛውም ጊዜ አልተናገሩም፥ በጻፏቸውም መጻሕፍት ውሰጥ " ድንግል ጥንተ አብሶ ሰለነበረባት ገብርኤል ባበሠራት ጊዜ ነፃች..." የሚል አላሰፈሩም"*

*እንዲያውም ለኢትዮጵያ ወጣት ኵኵሐ ሃይማኖት በሚባለው መጽሐፋቸው በመቅድሙ " ለትምህርት ወደ ውጭ አገረ ስትላኩም ቢሆን የሀገራችሁን ሃይማኖት ጠብቁ፤ ሀገራችሁ በሃይማኖት ከጥንት ጀምራ ራሷን የቻለች ስለሆነች መዋስ አትፈልግም፤ የሃይማኖት ጉዳይ እንደ ቀላል ነገረ የሚታይ አይደለምና አሰቡበት እያሉ በጊዜው የሚያሰጠነቅቋችሁን እንዳትዘነጉት..." በማለት የነበረውና ያለው እምነተ እንዲጠበቀ እንጂ የተፈለሰፈ አዲስ ነገር እንዳይዙ ወደ ውጭ ለሚላኩተ ኢተዮጵያዊያን እርሰዎን ጨምሮ ያሰጠነቀቁት። ታዲያ የሊቁን ምክር መቀበል ሲገባዎት፤ ያልተናገሩትን አሉ ብሎ የስሕተት ተባባሪ ማድረጉ ሰለምን እንደሆነ አንባቢ ይታዘበው።*

አንባቢ ሆይ!! ከላይ መሪ-ጌታ፡ ሊቁ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ከጻፏቸው መጽሐፍቶች ውስጥ፡ "ኵኵሐ ሃይማኖት" የሚባለውን በመጥቀስ፡ በመጽሐፉ መቅድም ላይ፡ ሊቁ ለተተኪው ትውልድ የጻፉትን ትክክለኛ ማሳሳሰቢያ አስፍረዋል። ሆኖም ግን፥ አባታችን ቀሲሰ አሰተርአየንና እኛን ከአገር ውጭ ያምንኖርን የተዋሕዶ ልጆች፡ የሊቁን ማሳሰቢያ እንዳልተቀበልን አድርገው በማቅረብ፡ ለመዝለፍ ሞክረዋል። ሐቁና እውነቱ ግን፥ አባታችን ቀሲሰ አሰተርአየም ሆነ እኛ የደብረሣህል መድኃኔ ዓለም የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር ምዕመናን፡ የአባቶቻችን ሃይማኖት አይበረዝብን በማለታችንና ጸንተንም በኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ እምነታችን በመቆማችን፡ የደረሰብንን መከራና ፈተና ሁሉ በእግዚአብሔር ቸርነት በመቋቋም፡ ሊቁ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬና አባቶቻቸው የጣሉብንን አደራ ጠብቀናል። በተቃራኒው ግን፡ መኖሪያቸው ከ ሮማው ካቶሊክ መንበር ከ ቫቲካን ያርፋጃ መንገድ እርቀት ያኽል ከሆነው በለንደን ከተማ የሚገኙት መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ፥ የሊቁን የመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬንና የአባቶቻቸውን አደራ በልተው፡ ለዚህ ባለፉት ፳ አመታት ውሰጥ ሰርጎ ለገባው የሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ፡ ቋሚ ጠበቃና ተጠሪ ለመሆናቸው ማሰረጃ፡ እራሳቸው ሊቁ፥ ለምን መጽሐፉን እንደጻፉትና፥ የተጻፈውስ ምን እንደሚል በመቅድሙ ላይ፡ የጻፉትን ዋና ዋና ነገሮች፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አማኝ ነኝ ለምንል ሁሉ ለማሳሰቢያነት ሰለሚጠቅም፡ እንዳለ ገልብጬ ቀጥየ አቀርባለሁ።

## መድሎተ አሚን ፡

የሃይማኖት ሚዛን።

ከመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ተዘጋጀ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ. ም.

## መቅድም።

ከመልአከ ብርሃን አድማሱ የተዘጋጀ።

መቅድም ማለት ለሚመጣው ነገር መሪ ፊታውራሪ በር ከፋች ማለተ ነው። ዮሐንስ አፈ ወርቅ ይደልዎ ለዘያነብብ ቅድመ ይዝክር ስሞ ለበዓለ መጽሐፍ ወእምዝ ያንብብ ወይምህር። መጽሐፍ ለሚመለከተው ሰው አሰቀድሞ የደራሲውን ስምና ታሪክ ማወቅ ከዚያ በኋላ መጽሐፉን ማንበብ መተርጎም ይገባዋል ብሎ እንደነገረን እኔም አሰቀድሜ ስሜንና አድራሻዬን ቀጥየም ይህን መጽሐፍ ላመጻፍ ያሰብኩበትን ምክንያት እያከታተልኩ እጽፋለሁ።

እኔ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ የተወለድኩበትና የደግሁበት፡ የተማርኩበት ሀገሬ በጎጃም ጠቅላይ ግዛት ዲማ ጊዮርጊስ፡ መልአከ ብርሃን ተብዬ የተሾምኩበት ብቸና ጊዮርጊስ ነው። ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያሰብኩበት ምክንያት፡ ዶክተር አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት የተባሉ ካቶሊካዊ መነኵሴ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰለክርስቶስ ባሕርያት አካላዊ ተዋሕዶ የምታምነው ትምርት በሚል አርእስት ተነሥተው አንድ መጽሐፍ ጽፈዋል። ይህም መጽሐፍ የዶክተርነት መዓርግ ለመቀበል ሊቅነታቸውን ለማስመስከር የጻፉት እንደኾነ ታውቋል።

ፍሬ ነገሩም ኢትዮጵያ በኬልቄዶን ጉባኤ ስላልነበረች፡ በልዮንና በዲዮስቆሮስ ማካከል የተደረገውን ታሪክ ሳታውቀው እንደ ጠፍ ከብት ለግብፅ መናጆ ኾና ትነጉዳለች እንጂ ባህሏ ከካቶሊክ ባህል ጋራ አንድ ነውና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥር ትተዳደር የሚል ነው።

ይህንኑም እውነት ለማስመሰል ከውጭ ሀገር ታሪክ ጸሐፊዎች መጽሐፍ በብዙ ጠቅሰዋል። ዐፄ ካሌብና ፱ቱ ቅዱሳንም ከቶሊካውያን እንደ ነበሩ ለማስረዳት ሞክረዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነትም ለማለያየት፥ ሊቃውንቶቿንም ርስ በርሳቸው ለማጣለት በብዙ ጥረዋል። ምናልባት ይህን መጽሐፍ ለተመለከተው እውነት ይመሰለው ይኾናል። ይኸን መጽሐፍ አይቶ መልስ ሳይሰጡ ዝም ማለት፡ የቀደሙ አባቶቻችንን እንደ ማሰወቀስ፥ ክብርን እንደ መቀነስ፥ ሀገርን እንደ መበደል፥ ራስን እንደ መግደል ኾኖ ስለታየኝ፥ ተመልካች ነገሩን ያመዛዝንበተ ዘንድ ይህን መጽሐፍ ጻፍኩ፡ ስሙንም መድሎተ አሚን ብዬ ሰየምኩት። ነገሩን ለማመዛዘን የሚረዳ የኬልቄዶኑን ጉባኤ መነሻና ውሳኔ ማወቅ ስለሆነ ስለዚህ ጉዳይ በኢትዮጵያ የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ ያገኘሁትን ታሪክ መቅድም አድርጌ እጽፋለሁ። ይልና፡

- ፩ኛ. <u>ስለ ካቶሊክ ሃይማኖት መነሻ የሚገልጽ ታሪክ</u> በሚል ንኡስ ርእስ ሰር ከ ገልጽ ፲፬-፲፯ በሚገባ ተቀምጧል። ሆኖም እንዳይረዝም በማለት ዘልየው በገልጽ ፲፯ እኩሌታ ላይ፥ ፪ኛ. ይህ የካቶሊክ ባህል ወደ ኢትዮጵያ በምን ጊዜ እንደመጣና፡ <u>የኢትዮጵያ ሊቃውንት በምን ዓይነት እንደተቃወሙት የሚገልጽ ታሪክ። የሚለውን እንመልከት።</u>

ኢትዮጵያ ግራኝ መሐመድ በወረራት ጊዜ ዐፄ ልብነ ድንግል ከፖርቱጊዝ መንግሥት ርዳታ ጠይቀው እርሳቸው ተሞቱ በኋላ በፖርቱጊዞች ርዳታ ግራኝ ድል ኾኖ ኢትዮጵያ ሙሉ ነፃነቷን አግኝታ መንግሥቷን በትክክል ማቋቋምዋ የታወቀ ነው።

በዚህ ጊዜ ከኢትዮጵያ ተልኮ ፖራቱጊዞችን ለርዳታ ያመጣው ቤርሙንዲዝ፡ ከኢትዮጵያ ግዛት ገሚሱ ለፖርቱጊዝ መንግሥት ይሰጥ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ከእንግዲህ ወዲያ አቡን

ከእስክንድርያ መምጣቱ ቀርቶ ከሮም ይምጣ። እኔም ለኢትዮጵያ አንደኛ መጀመሪያ ሮማዊ ጳጳስ ልኹን ብሎ ዐፄ ገላውዴዎስን ጠየቀ። የኢትዮጵያ ሊቃውንትም ፍርድ በቃ ይስጡን እንከራከርና ሮማውያን ቢረቱን እንልቀቅላቸው: ብንረታቸው ይልቀቁልን አሏቸው። ንጉሡም ፈቅደው ጉባኤ ተደረገ: ለኢትዮጵያ ሊቃውንት አፈ ጉባኤ ዝክሪና ጳውሊ ኾኑ። ጳውሊም በጎጃም ጠቅላይ ግዛት በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ አጠገብ የሚገኝ የደብረ ጽሙና ገዳም ሊቃውንት ናቸው። ይልና፥ በጉባኤው ላይ የተነሱትን ፫ ጥያቄዎች ከነ ሙሉ የመከራከሪያ ነጥባቸውና እንዴት አድርገው አባ ጳውሊና ዝክሪ ካቶሊኮቹን እንደረቷቸው አስቀምጠውታል። ሆኖም ግን በድጋሚ: ጽሑፉ እንዳይረዝም: በማለት ሰለተነሳንበት ጉዳይ የሚመለከተውን በተራ ቁጥር ፫ ላይ የሰፈረውን እሰጥ አገባ ሙሉውን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

## ፫ኛ. ጥያቄ

ስሙን ልዮን የሚሉት አንድ ሮማዊ ተነሥቶ: ወልደ አብ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሥጋ ማርያምን በለበሰ ጊዜ: ሰይፍ በሰገባው እንዲከተትና እንዲቀመጥ አደረበት እንጂ: አልተዋሐደውም: በ፴ ዘመኑ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በራሱ ላይ ሲቀመጥ መለኮቱ ከትስብእቱ ተዋሐደ፣ የጸጋ አምላክ ሆነ: መዋቲ ትስብእትም የማይሞት ኾነ ከ፴ ዘመን በፊት የጸጋ አምላክ ስላልሆነ አምላካዊ ሥራ አልሠራም፤ ከተጠመቀ በኋላ ግን የጸጋ አምላክ ስለሆነ ውኃውን ወይን አደረገ ብዙ የአምላክነት ሥራ ሠራ አለ።

እንደዚኽውም በንግድ ምክንያት መጥቶ እስክንድርያዊ መሰሎ በኢትዮጵያ የሚኖር አንድ ሰው ተነሥቶ እንዲህ ሲል ተናገረ። እናንተ ኢትዮጵያዊያን ቃል ሥጋ በለበሰ ጊዜ በማኅፀነ ማርያም መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የባሕርይ አምላክ ሆነ ትላላቹህ በማኅፀን መንፈስ ቅዱስን ሲቀበል ያየው የለም። ሮማዊያን ግን እስከ ፴ ዘመን በሰብአዊ ግብር ኖሮ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ ሰው ኹሉ እያየው በራሱ ላይ ስለተቀመጠበት የጸጋ አምላክ ሆኖ የአምላክነት ሥራ ሠራ ይላሉና ከእስክንድርያ ሃይማኖት የሮማ ሃይማኖት ትሻላለች አለ።

አባ ጳውሊ ሲመልስ፤ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ሲያበሥራት መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል የአብም ኃይሉ ይጋርድሻል: ካንቺ የሚወለደውም ቅዱስ ነው: የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። ፫ቱም አካላት በማኅፀነ ማርያም እንደ አደሩ ተናግሯል። ማደራቸው: አብ ለአጽንዖ፥ መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ፥ ወልድ ለለቢሰ ሥጋ ነው እንጂ ፫ቱ ኹሉ ለለቢሰ ሥጋ ያደሩ አይምስልህ።

በዚህ ጊዜ መለኮት ርቀቱን ለቆ ሳይገዝፍ፥ ሳይለወጥ: ትስብእትም ግዘፉን ለቆ: ሳይረቅ፥ ሳይለወጥ እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ። ወልድ ለለቢሰ ሥጋ ማለት: ይህ ነው: አብ ለአጽንዖ ማለትም፤ ሰማይ ምድር የመይወስኑትን ምሉእ፥ ሰፉሕ፥ ረቂቅ መሎኮትን: እመቤታችን በጠባብ ማኅፀን እንድትችለው: አጸናት ማለት ነው: መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ ማለትም: ትስብእትን ከአዳም መርገም አንጽቶ፥ ቀድሶ ለተዋሕዶተ መለኮት የበቃ አደረገው ማለት ነው። ይህን በማኅፀን በረቂቅ ምሥጢር የሠሩትን አምላካዊ ሥራ: በዮርዳኖስ ወልድ ባጭር ቁመት፥ በጠባብ ደረት ተወስኖ ሲጠመቅ በመታየት አብ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ የሚል ድምጸ በማሰማት: መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጦ: አብ ልጄ ይህ ነው ብሎ የመሰከረለት ወልድ ይህ ነው ብሎ በጣት ጠቅሶ እንደ ማሳየት በመመስከሩ ገልጸውታል እንጂ እስከዚያ ድረስ ፴ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ተለይቶት ኖሮ በዮርዳኖስ አደረበት ማለት አይደለም አለ። ያ ሮማዊ መልስ አጥቶ ዝም አለ።

አንባቢ ሆይ!!! ከዚህ በመቀጠል መቅድሙን ሲዘጉ እንዲህ ብለዋል፥

እነሆ ፩ኛ. ልዮንና ዲዮሰቆሮስ የተለያዩበትን ታሪክ: ፪ኛ. ካቶሊካዊያን ወደ ኢትዮጵያ ሊገቡ የሞከሩበትንና ኢትዮጵያውያንም ተከራክረው የመለሱበትን ታሪክ አባቶቻችን ካቆዩን የታሪክ

መጻሕፍት በተቻለ መጠን ጽፌላችኋለሁ። ይህም ከአባቶቻችን የተገኘው ቅርስ: ጠቃሚ መኾኑን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በትውልድ የሚደርሱ፥ የሚታዩና የሚሰሙ ነገሮች ኹሉ ከዋና ትምህርት የሚቆጠሩ ናቸው። ብለው አስረድተውናል: ሐምሌ ፲፮ ፲፱፻፴፫: ቀ-ኃ-ሥ

"በአእምሮ ጠንክሩ፥ በሥራ ጠንክሩ፥ በሃይማኖት ጠንክሩ፤ የመጨረሻውን ዕድልና፥ የድል አክሊል ትወርሳላችሁ" ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. የሚለውን ንጉሳዊ መሪ ቃል መሠረት በማድረግ ካባቶቻችን በወረሰናት ሃይማኖት ጸንተን ተገኝተን የመጨረሻውን የድል አክሊል ለመቀዳጀት ያብቃን: አሜን።

--------------------

አንባቢ ሆይ!!!! ከላይ ቁልጭ ብሎ፥" መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ ማለትም: ትስብእትን(የማርያምን ሥጋ) ከአዳም መርገም (ከጥንተ አብሶ) አንጽቶ፥ ቀድሶ ለተዋሕዶተ መለኮት የበቃ አደረገው ማለት ነው። ብለው በ፲፩ ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ሊቃውንት አባቶቻችን: የሮማ ካቶሊኮችን አመስጥረው የረቱበትን የአደራ ቃል: ማን ነው ዛሬ ሊክደው የሚችለው????።

እንግዲህ ወገኖቼ፥ ከዚህ የበለጠ: የሃይማኖት ክህደት ከየት ሊመጣ ነው? ከዚህ የበለጠ በሃይማኖት የከፋ ውደቀት ከቶ የለም።

መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ፥ በጽሑፍዎ ላይ: አባታችን ቀሲስ አሰተርአየን አሰመልክቶ፥ "*ታዲያ የሊቁን ምክር መቀበል ሲገባዎት፤ ያልተናገሩትን አሉ ብሎ የስሕተት ተባባሪ ማድረጉ ሰለምን እንደሆነ አንባቢ ይታዘበው።* ብለው ሀስት ስለተናገሩት፥ ያ ሮማዊ መልስ አጥቶ ዝም አለ፥ ብለው ሊቁ ቢነግሩንም፥ እኔ ግን ለእርሰዎ ከልብ የምመኝለዎት: ቀሲስ አስተርአየን ለመዝለፍ ከመሞከር ይልቅ፥ ከሳቸው ለመማር ቢሞክሩ: ሃይማኖትዎን የበለጠ ያውቋት ነበር።

<u>ማሳሰቢያ</u>

ይህ የነገረ ሃይማኖት ውዝግብ ተጀምሮ: ብፁዕ አቡነ ማቲያስ በደብራችን ተገኝተው የወሰኑትን ውሳኔ አስመልክቶ: በብፁዕ አቡነ ይስሐቅ አነሳሽነት በ ዋሽንግተን ዲሲና አካባቢ በወቅቱ የነበረው የማህበረ ካህናት ጉዳዩን ለማየት ጉባኤ ማድረጉ ይታወሳል። ይህ የተሰየመው ጉባኤ: ጉዳዩን አይቶና አጥንቶ: ቀሲስ አሰተርአየ የያዙት እምነትና ያስተማሩት ትምህርት: ትክክለኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ነው ሲል አረጋግጧል። ይህ ብቻ ሳይሆን: ጉባኤው የደረሰበትን የውሳኔ ቃለጉባኤ በሸኚ ደበዳቤ (ቁጥር 06 / ማ / ካ ) ኅዳር ፲፮ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክር ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት አዲስ አባባ ጉዳዩ እንዲታይ መላካቸው ይታወሳል። ይኽ ትክክለኛ ውሳንያቸውና የወሰዱት እርምጃ፥ እኛን ብቻ ሳይሆን ብዙ ሕዝበ ክርስቲያንን ያጽናና፥ ያሰደሰተና ተሰፋም የሰጠ ነበር።

እንደሚታወቀው፥ ይህን የሃይማኖት ጉዳይ በተመለከተ: እስካሁን ድረስ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክር ቅዱስ ሲኖዶስ ምንም የተሰጠ መልስ የለም። ምን አልባት ቀን ቀንን ሲወልድ፥ ነገሩ ተረሰቶ: አባታችን ቀሲስ አሰተርአየም ሆነ እኛም ደብዛችን ጠፍቶ ይቀራሉ ተብሎ ታሰቦም ይመሰላል: ጳጳሳቱም ዝም ዳዊቱም ዝም ሆኗል። ሆኖም ግን በኛ በኩል የገጠሙንን ብዙ ፈተናዎች በእግዚአብሔር ቸርነት እስካሁን ተወጥተናል ወደፊትም የሚገጥሙንን ውጣ ውረዶች በእግዚአብሔር ኀይል እደምንወጣቸው አንጠራጠርም። ሆኖም ግን: ምንም ቁጥራችን ጥቂት ቢሆንምና ፈተናችንም ቢበዛም፥ ደማቸውን አፍስሰው፥ አጥንታቸውን ከሰክሰው፥ ቆዳ ፍቀው፥ ቅጠል ፈጭተው፥ በብራና ጽፈው ያቆዩልንን ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ሃይማኖት: በሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ ሲተካ ላለማየት: አንድ ቀን እንኳን ሳናርፍ: እስከ ግብጽ ኦርቶዶክስ ቤ/ክር ድረስ ያለማቋረጥ ጩኸታችንን አሰማን። የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይመሰገን: ይኸው መልሳችንን ከአኀት አብያተ ክርስቲያን አገኘን።

ታዲያ: እኛ ተራ ምእመናኖቹ ሳንሰለችና ተሰፋ ሳንቆርጥ ጸንተን በመቆም እንዲህ ሰንታገል: ምላቹህ ተገዝታቹህ ሃይማኖቱን ልትጠብቁና ልታሰጠብቁ ክህነቱ የተሰጣቹህ በውስጥም በውጭም ያላቹህ ካህናት በይበልጥም ብፁዐን አባቶች እንዴት ዝም አላቹህ።  ለዚሀ ቁርጥ ቀን ካልሆናቹህና ካልበቃቹህ ኸረ ለመቼ ልትሆኑ ነው። ለቅዳሴውና ለመዝሙሩ ብቻ ከሆነ ከህነታቹህ፥ ዘፋኞቹም አሳምረው ዘምረውታል፥ ቅዳሴውንም ቢሆን ምእመኑ በደንብ እያለው ነው። ሃይማኖት ነውና: ያለባቹህን ግዴታ ልትወጡ ይገባል እላለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ: በዚኽ ባለፉት ፭ አመታት ውስጥ: ከጎናችን ሳትለዩ አይዟቹህ እያላቹህ ያበረታታቹህን፥ በደብራችን ከየ እስቴቱ መጥታቹህ በክብረ በዓላቱ ላይ የተገኛቹህ የቁርጥ ቀን ካህናት፥ ስለእውነት ስትሉ እንደቆማቹህ: የእውነተ አምላክ እግዚአብሔር ይቁምላቹህ።

በመጨረሻም፥ መቼም ሰው ያለውን ከወረወረ ፈሪ አይባልምና: ከላይ እንደገለጽኩት በወቅቱ የዋሽንግተን ዲሲና አካባቢ የማህበረ ካህናቱ አባላት የነበራቹህ ስማቹህ ከዚህ በታች የሰፈረው: ካህናት ምነው አንድ ደብዳቤ ብቻ ልካቹህ ተሰፋ ቆረጣቹህ። ሃይማኖት ተፋልሶ: እንዴት ዝም ትላላቹህ። ሌላው ቢቀር እንኳን: እንዴት በየድሕረ ገጹ ላይ ለሚጻፈው ኑፋቄና ተረት: እውነቱን መመስከር   ተሳናቹህ። አሁንም በድጋሚ ከታላቅ አክብሮት ጋር ሰለ እውነቱ ሰትሉ ድምጻቹህን በየአዳባባዩ በድጋሚ አሰሙ።

፩. ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ኃይሌ
፪. ቆሞስ አባ መዓዛ በየነ
፫. ሊ/ማ/ዶ/ር አማረ ካሣዬ
፬. መጋቤ አእላፍ መክብብ አጥናው
፭. አባ ሠረቀ ብርሃን ወ/ሳሙኤል
፮. ሊቀ ኅሩያን ከፈለኝ ወ/ጊዮርጊስ

# ማጠቃለያ

እስካሁን የሃይማኖቱን መዛባት፥ የቤተክህነቱም ግዴለሽነት፥ የነ መሪጌታ ገብረ ሥላሴንም የሐሰት ምስክርነትና አሳዳጅነት፥ በሊቃውንቱ ላይም የሚደርሰውን ግፍ ከገለጽኩ በኋላ: ጽሑፌን እደመድማለሁ:: በመግቢያው ላይ እንዳልኩት፥ ቤተክርስቲያኗን በተመለከተ ተራ ምእመን ነኝ። ነገር ግን እንደሌላው ምእመን እኔም የእናቴና የአባቴ በማለት ብቻ በከንሳስ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በኮሚቴነት ተመርጬ በማገልገል ላይ ሳለሁ፥ እኔና ዲያቆን ሳሙኤል ባደረግነው የግል ውይይት ላይ የተፈጠረው አለመግባባት በቀሲስ አስተርአየና በኦርቶዶክሱ እምነታችን ላይ ያደረሰው ጫጫታ፥ ቀድሞም የነበረኝን የመጠየቅ፥ የማወቅና የመረዳት ፍላጎቴን እጅግ ቀሰቀሰብኝ:: እምነቱን ለማጥናት በማደርገው ጥረት አብሮ የተረዳሁት ነገር ቢኖር፥ እውነቱን በሚያሰተምሩት እንደ ቀሲስ አሰተርአየ ባሉት መምሕራንና በሃይማኖቱ ላይ የሚፈጸመው የሐሰት ተጽእኖ እስከፊና አሳዛኝ መሆኑን ታዝብያለሁ።

በጽሑፌ ላይ በሰፊው ላሳያው እንደሞከርኩት፥ ቤተ ክርስቲያናችን በብዙ ሊቃውንቶች ታፍራና ተከብራ የቆየች እንደነበረችና በዘመናችን ደግሞ ለነገረ ሃይማኖቱ መመዘኛ መጽሐፍት ምን ይላሉ የሚለው ቀርቶ፥ እከሌ ምን ይላል የሚሉት እየበዙ እንደመጡ አይተናል። ይህም ብቻ ሳይሆን፥ ሃይማኖቱን ጠብቀው ሊያሰጠብቁ፥ በቦታው የተሰየሙት አባቶች ነገረ ሃይማኖቱን ከጉዳይ ሳይቆጥሩ: ምድራዊ ለሆነው ገንዘብና አሰተዳደር እስከ ድብድብ ደርሰዋል። ይህ ድርጊታቸው እጅግ አሳዛኝ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. በክቡር ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ሰብሳቢነት የተሰየመው የሊቃውንት ጉባኤ የወሰነው ውሳኔና ክቡርነታቸውም ይኸንን ውሳኔ አሰከትሎ ባደረጉት የእምነት ለውጥ፥ ቀደም ብለው ከጻፋቸው ኦርቶዶክሳውያን መጻሕፍቶቻቸው ርቀው ባቀረቧቸው ሐሳቦች ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን ነገረ ሃይማኖት በተመለከተ ከአቻወቿ ከኦኅት አብያተ ክርስቲያናት እንደራቀችና ወደ ሮማ ካቶሊኮች እንዳዘነበለች ለማንም ግልጽ ነው። በተጨማሪም፥ በኦኅት አብያተ ክርስቲያናትና በሮማን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን መካከል፥ እንዲህ ያለውን ልዩነት ለይተው ያልተገነዘቡ: ከዲያቆን አንስቶ እስከ ጳጳሳ ድረስ ያሉ ካህናት: ቤተ ክርስቲያኗን እያጥለቀለቋት ለመሆኑ ከመሪ-ጌታ ገ/ሥላሴና ከብፁዕ አቡነ ማቲያስ ምሥክርነት የበለጠ በቂ ማሰረጃ አይገኝም። በተቃራኒው ደግሞ፥ ልዩነቱን አውቀው: ለዶክትሬት ድግሪያቸው ባዘጋጁት የጥናት ጽሑፍ (Dissertation) ላይ: በሚገባ ያሰፈሩትን ኦርቶዶክሳዊ እምነት፥ ዛሬ የቤተ ክርሰቲያኗ ፓትርያርክ በሆኑበት ወቅት: ሃይማኖት ሲፋለስ፥ ቤተ ክርስቲያን ያላግባብ ሲፈርስና ሕዝበ ክርስቲያን ሲታመሰ: ሾልኮ የገባውን የሮማ ካቶሊክ ኑፋቄ እንደማሰወጣትና እንደማስተካከል ፈንታ፥ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው እንደማያውቁትና እንዳልመሰከሩለት ዝም ብለው በማየት ላይ ያሉት ቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ ጳውሎስም፥ ከተጠያቂነት አይወርዱም። የቅዱስ ሲኖዶሱ አባላትም ቢሆኑ፥ ቅዱስ ፓትርያርኩ በጻፉት ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ "እመቤታችን ካለአዳም የውርስ ኃጢአት (ከላጥንተ አብሶ) ተወለደች አንልም"፥ ይኸንን የምትል፥ የሮማ ካቶሊክ ቤ/ክር ብቻ ነች ብለው የመሰከሩትን እያወቁ፥ ጉዳዩ በጉባኤ ታይቶ መፍትሄ እንዲያገኝ ከማድረግ ፋንታ፥ አንገታቸውን ቀብረው ምነው ዝም አሉ። ይህ ሁሉ ምስቅልቅልና ኃላፊነትን አለመወጣት መታረምና መሰተካከል አለበት። አለበለዚያ፥ እንደ መሪ-ጌታ ገ/ሥላሴ፥

- የግበጽ ኦርቶዶክሰ ቤተክርሰቲያንና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሚሥጥረ ሥላሴ ላይ ልዩነት አላቸው ብለው ሀሰት በሚናገሩ
- በሊቃውንት አባቶቻችን የተጻፉትን እንደ "መድሎተ አሚን" ያለን መጽሐፍት: እንዳልተጻፉና እንደሌሉ ለማድረግ በሚጥሩ ካህናትና ጳጳሳት: ቤተ ክርስቲያናችን ማሞላቷ አይቀርም።

ይህ እንዳይሆን ያለው አማራጭ: በውስጥና በውጭ ያለን ሕዝበ ክርስቲያን: በሕይወት ከሚገኙት እውነተኞች ሊቃውንት መምሕራን እምነቱን እያጠናን፥ ቅዱሳት መጽሐፍትን እያመሳከርን ለጥቅምና ለሹመት የሚታገሉትን እየታዘብንና እየመከርን፥ ከትክክለኞች መምሕራን ጋራ በመሰለፍ

እምነቱን ለመጠበቅ የወደቀብንን ከፍተኛ ኃላፊነት መወጣት አለብን:: እኔም ሆንኩኝ የደብረ ሣሕል መድኃኔ ዓለም የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክር አባላት: በአሜሪካ እንደሚኖረው እንደማንኛውም ሰው: የግል ኑሯችንን ለማሸነፍ በምናደርገው ሩጫ: ከሌለን ሰአት ላይ በመሻማት: ላለፉት አምስት አመታት ከቀሲስ አሰተርአየ ጽጌ ከሚፈሰው የእውቀት ጅረት፥ በማንኪያ ያህል ለመቅመስ እድሉን በማግኘታችን: ያለብንን ቤተ ሰባዊ የሃይማኖት ቅብብሎሽ ለማወቅና ለመመሰክር ለመቻል የግላችንን ድርሻ ለመወጣት ሞክረናል:: ይህን ጽሑፌን ከፖለቲካ፥ ከጎሳና ከማንኛውም ሥጋዊ ነገር ጋራ ሳተገናኙ አንብባችሁ የተረዳችሁ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ሁሉ፥ የእናትና የአባት እያልን ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዳችንን ሳናቋርጥ፥ ስለ ነገረ መለኮቱ አያገባንም የሚለውን የሞኝ አስተሳሰብ ወደጎን ትተን እምነታችንን አጣርተን እንወቀው::

ይህን የማናደርግ ከሆነ ግን እንደነ መሪጌታ ኀብረ ሥላሴ ያሉ ሰዎች ለሃይማኖታችን ያለንን ቅናት በመጠቀም በሃይማኖቱና በመምሕራኑ ላይ እንድንዘምት መሳሪያ ያደርጉናል:: በነገረ መለኮቱ አያገባንም የሚለው አባባል ሃይማኖቱን ለይተው ባወቁት ሊቃውንት አበው በነበሩበት በደጎች አባቶቻችን ዘመን መኖሩ ተገቢ ነበር:: አሁን ካለንበት ጀምሮ ወደፊት ለሚመጣው ትውልድ ግን ለቀጣፊዎችና ለግል ኑሯቸውን ለማዳበር ለሚጥሩ ግለሰቦች እንጅ ለምንም አይጠቅምም:: የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ሃይማኖት ከኛ ቀጥሎ ለሚመጣው ትውልድ ለማትረፍ፥ እምነቱን ጠልቀን በማወቅ ትክክለኞችን ካህናትና መምህራን ለይተን በማወቅ የተሳሳቱትን በግልጽ መገሰጽ መቻል አለብን:: ግብዝነት ያለበትን ፍርሐትና ሐፍረት ከሕሊናችን አስወግደን በተገቢው ፍቅርና አክብሮት ነገረ መለኮቱን ጠልቀው ከተማሩት ጋራ ተባብረን እንቁም:: ይህን ብናደርግ በየአካባቢያችን የሚፈጸብንን ችግር ተቋቁመን፥ ለሚመጣው ትውልድ እምነቱን ለማሸገር የምንችል መሆናችንን በማሳሰብ እሰናበታችኋለሁ::

በተረፈ በእውነት ለምትወረሰው መንግሥተ ሰማያት ወራሾች እንድንሆን እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን።